# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

ሰዋስው
ቃላት
መፃፍ
ሥነ-ጽሑፍ
መናገር
ማንበብ
ማዳመጥ

## 7ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## ውድ ተማሪዎች! ይህን መፅሐፍ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ፡፡

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክ ወይም በወረቀት ሸፍኑት፡፡

2. መጽሐፉን ሁልጊዜ በደረቅና በንጹህ ቦታ አስቀምጡ፡፡

3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፡፡

4 በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፡፡

5. በመጽሐፉ ገጾች መካከል ምልክት ለማድረግ ስትፈልጉ ብጣሽ ወረቀት፣ ክር ወይም ካርድ ተጠቀሙ፡፡

6.በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ወይም ገጾች በፍጹም አትቅደዱ፡፡

7.በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በማጣበቂያ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ አጣብቁ፡፡

8.መጽሐፉ ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

9.መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

10.መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀሙ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡ፡፡ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት፡፡

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

አዘጋጆች:-
ማንደፍሮት አድማሱ(ኤም.ኤ)
ደምሴ ኩራባቸው(ኤም.ኤ)
ታደለ ጉርሜሳ (ቢ.ኤ)

ገምጋሚዎች:-
ለዝና መንግስቴ(ቢ.ኢ.ዲ)
ነፃነት ጥጋቡ(ኤም.ኤ)
ይሻሙ ጌራወርቅ(ኤም.ኤ)

# ማውጫ


| ምዕራፍ | ገጽ |
|---|---|
| 1 ምዕራፍ አንድ፡-ሀገር በቀል ዕውቀትና ባህል | 1 |
| ማዳመጥ | 1 |
| መናገር | 4 |
| ማንበብ | 4 |
| ቃላት | 9 |
| ሰዋስው | 10 |
| 2 ምዕራፍሁለት፡- የህይወት ተሞክሮ | 13 |
| ማዳመጥ | 14 |
| መናገር | 17 |
| ማንበብ | 17 |
| መፃፍ | 22 |
| ስዋስው | 25 |
| ስነ ጽሑፍ | 28 |
| 3 ምዕራፍ ሶስት፡- ስርዓተ ፆታ | 32 |
| ማዳመጥ | 32 |
| መናገር | 34 |
| ማንበብ | 37 |
| መፃፍ | 33 |
| ቃላት | 42 |
| ሰዋስው | 48 |
| ስነ-ጽሑፍ | 53 |

4. ምዕራፍ አራት ፡ ሳይንስና ቴክኖሎጂ----------------------55
ማዳመጥ --------------------------------------------------56
መናገር----------------------------------------------------58
ማንበብ----------------------------------------------------60
መፃፍ------------------------------------------------------66
ቃላት------------------------------------------------------70
ሰዋስው--------------------------------------------------72
ስነ ፅሑፍ----------------------------------------------74
5 ምዕራፍ አምስት፡- የጊዜ አጠቃቀም----------------------77
ማዳመጥ -------------------------------------------------78
መናገር---------------------------------------------------79
ማንበብ---------------------------------------------------82
መፃፍ-----------------------------------------------------86
ቃላት-----------------------------------------------------88
ሰዋስው-------------------------------------------------89
ስነ ጽሑፍ---------------------------------------------93

6 ምዕራፍ ስድስት፡- የሀገር ፍቅር----------------------------96
ማዳመጥ --------------------------------------------------97
መናገር---------------------------------------------------99
ማንበብ---------------------------------------------------99
መፃፍ-----------------------------------------------------104
ሰዋስው-------------------------------------------------105
ስነ-ጽሑፍ--------------------------------------------109

7 ምዕራፍ ሰባት፡- ስነ ቃል------------------------------------112
ማዳመጥ ------------------------------------------------------113
መናገር------------------------------------------------------114
ማንበብ------------------------------------------------------114
መፃፍ--------------------------------------------------------120
ቃላት---------------------------------------------------------122
ሰዋስው-----------------------------------------------------123
ስነ ጽሑፍ--------------------------------------------------124
8 ምዕራፍ ስምንት፡-ጠንካራ የስራ ባህል-----------------------130
ማዳመጥ ------------------------------------------------------131
መናገር-------------------------------------------------------132
ማንበብ------------------------------------------------------132
መፃፍ--------------------------------------------------------135
ቃላት---------------------------------------------------------140
ስነ-ጽሑፍ ---------------------------------------------------141

## መግቢያ

ይህ መፅሐፍ የተዘጋጀው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ነው፡፡ መፅሐፉ ሲዘጋጅ መሰረት ያደረገው ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን (እንደ ሁለተኛ ቋንቋ) መርሀ ትምህርት ነው፡፡ ዋና አላማውም መርሀ ትምህርቱ ውስጥ ተማሪዎች ሊያውቋቸው ይገባል ተብለው የተካተቱትን መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎችና ተጓዳኝ እውቀቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡ የመማሪያ መፅሀፉ በውስጡ ስምንት ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን በእያንዳንዱ ምዕራፍ የማዳመጥ፣የመናገር፣የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን፣ እንዲሁም የስዋስውና የስነ ፅሑፍ ዕውቀቶችን ሊያዳብሩ የሚችሉ የትምህርት ይዘቶችን አካቷል፡፡ እነዚህን ይዘቶች ለማስተማር የሚያገለግሉ ምንባቦችና አጫጭር ማስታወሻዎች ከመልመጃዎች ጋር ተስማምተው ቀርበዋል፡፡ የቀረቡት ምንባቦችና አጫጭር ማስታዎሻዎች የቋንቋ ክሂላቱን እና ተያያዥ ዕውቀቶችን ለማዳበር ካላቸው ጥቅም ባሻገር አጠቃላይ የተማሪዎችን ማህበራዊ ግንዛቤ ያጎለብታሉ፡፡ በተጨማሪም አስተሳሰባቸው የሰላ እንዲሆን ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ሀገር በቀል ዕውቀትና ባህል

### የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች

- ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-
- ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በማዳመጥ ታነጣፃፅራላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ ስለሚገኙ ሀገር በቀል ዕውቀቶች መረጃ ሰብስበው ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- አንድን ቃል አንብበው አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ትርጉማቸውን ትሰጣላችሁ፡፡
- ቃላትን በመተንተን ግንድ ፣ቅድመ ግንድ ቅጥያና ድህረ ግንድ ቅጥያ በማለት ትለያላችሁ፡፡
- ምእላዶችን ከዋና ቃል (ግንድ) ጋር በማጣመርና በመነጠል የተለያዩ ቃላትን ትጽፋላችሁ፡፡

**ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ**

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ተግባር**

1./ ደቦ/ወንፈል በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ደቦ (ወንፈል) ማለት ምን ማለት ነው?
2. ደቦ በአካባቢያችሁ እንዴት ይተገበራል?

3. በእናንተ አመለካከት ደቦ ምን ዓይነት ማህበራዊ ጠቀሜታ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

የማዳመጥ ጊዜ

## ተግባር

1. ቀደም ሲል ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ተስማሚውን መርጣችሁ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. በምንባቡ መሰረት ስለ ደቦ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የሥራ ጫናን የሚቀንስ ባህላዊ የህብረት ሥራ ነዉ፡፡

ለ የመተጋገዝና የመደጋገፍ ባህልን ለማጎልበት ይጠቅማል፡፡

ሐ ከእርሻ ሥራ በተጨማሪ የመኖሪያ ቤትን ለመስራት የሚረዳ ባህላዊ ዘዴ ነው፡፡

መ. በቴክኖሎጂ በመታገዝ የሚከናወን የተናጠል ተግባር ነው፡፡

2. በምንባቡ ውስጥ ከተዘረዘሩት የእርሻ ተግባራት መካከል ያልተካተተው የቱነው?

ሀ. ማረስ ለ. መቃረም ሐ. ማጨድ መ. መዝራት.

3. በምንባቡ መሰረት የእርሻ ተግባራትን ማከናወን ከባድ የሚሆነው መቼ ነው?

ሀ. በዘመናዊ መሳሪያ በመታገዝ ሲሰራ ለ. በአንድ ቤተሰብ ሲሰራ

ሐ. በቡድን ሲሰራ መ. በአንድ ሰው ሲሰራ

4. በምንባቡ መሰረት ደቦ/ወንፈል አርሶ አደሩን የሚጠቅመው፣

ሀ. ሰብልን በአጭር ጊዜ ለመሰብሰብ

ለ.ወቅቱን ካልጠበቀ የዝናብ አደጋ ለመዳን

ሐ. የመተጋገዝና የአብሮነት ባህልን ለማዳበር

መ ሁሉም መልስ ይሆናሉ

2. ደቦ በምለው ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት በፅሑፍ መልስ ስጡ፡፡

1. ደቦ በአገራችን በሚገኘው በርካታ የገጠር አካባቢዎች የተለመደ የጋራ ሥራ ነው፡፡
2. የሀገራችን የግብርና ሥራ በአብዛኛው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ይሰራል፡፡
3. ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሰብሎችን ሊያበላሽ ይችላል፡፡
4. አርሶ አደሩ ምርቱን ቶሎ ለመሰብሰብ ደቦ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡
5. ደቦ የእርሻ ሥራን እንጂ ሌሎች ሥራዎችን አያካትትም፡፡

3. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ከታች የቀረቡትን ክፍት ቦታዎች በተገቢው ቃላትና ሀረጋት አሟሉ፡፡

1. ደቦ ሰዎች ተናጠላዊ የሥራ ------------------ የሚንቀሳቀሱበት --------------- ሥራ ነዉ፡፡
2. በሀገራችን የገጠር አካባቢዎች የግብርና ሥራ ----------- የታገዘ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ሰፋፊ የእርሻ ማሳን በአንድ ሰዉ ወይም በአንድ ቤተሰብ ሀይል --------------፣------------------፣------------------፣-------------------- እና ------------------ ከባድ ነው፡፡
3. ደቦ የተለያየ ---------------------- ያላቸዉን ሰዎች እንኳ ሳይቀር በጋራ የመሥራት ---------- እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡ በአጠቃላይ ደቦ የመተጋገዝና ---------------- ባህልን ያጎለብታል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ሀገር በቀል እውቀቶች መካከል አንዱን መርጣችሁ መረጃ በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. በምትኖሩበት አካባቢ በብዙዎች ዘንድ የሚዘወተሩ ባህላዊ ክንውኖች መካከል ጠቃሚና ጎጂ ያላችኋቸውን በመለየት በክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡

### ተግባር

## ክፍል ሦስት፡- ማንበብ

### ቅድመ ምንባብ

### ተግባር

1. የገዳ ሥርዓትን ከሌላው ስርዓት የሚለየው ምንድነው?
2. ሽምግልና ምንድነው?
3. በገዳ ስርዓት የዳኝነት ውሳኔ የሚሰጠው በማን ነው?

# የገዳ ሥርዓት

የገዳ ሥርዓት የኦሮሞ ባህል በብዛት የሚንፀባረቅበት ነው፡፡ የኦሮሞ ባህላዊ ገጽታዎችና ድርጊቶች በርካታ ናቸው፡፡ በጣም ጥቂት የሆኑትን ብቻ ወስደን በሚከተለው ሁኔታ እናቀርባለን፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ የተካተቱት ሽምግልና፣ ሲንቄ እርቅ፣ የሲንቄ ሀይል የሚሉት ናቸው፡፡ ሽምግልና ማለት በኦሮሞ አዛውንቶች የተደራጁ ጉዳዮችን በመስማትና በማየት ችግሮችን በእርቅ የሚፈታ ተቋም ነው፡፡

ሽምግልና በአካባቢው አዛውንትና በሠፈር ሽማግሌዎች የሚፈፀም ሲሆን በሠፈር ደረጃ መፈፀም ባሉባቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት የሚያስችል ነው፡፡ ሽምግልና በኦሮሞ ባህል በቤተሰብ፣ በጎረቤት፣ በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠሩትን ችግሮች የመጀመሪያ መፍትሔ ለመስጠት የሚያግዝና አሁንም ድረስ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የተፈጠረው ግጭት /አለመግባባት / በአካባቢው ሽማግሌዎች ሊፈታ ካልቻለ ወደ ጎሳው አለቃ ይተላለፋል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ይግባኝ በተበዳይ ወይም ውሳኔ ፈላጊ አካል ተጠይቆ በአገር ሽማግሌዎች ይሁንታን ካገኘ ነው፡፡

ይሁንታውን የሚሰጡት ግጭት ወይም ቅራኔው ላይ መስጠት ከአቅማቸው በላይ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ይግባኙን የሚመለከተው የበላይ አካል ውሳኔ ለመስጠት በሽማግሌዎች የተወሰኑትን ወይም የተሰጡትን ሐሳቦች

በጥልቀት ይመረምራል፡፡ ከዚያ በኋላ በሶስት ወይም በአምስት ሽማግሌዎች የታየውን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ከሽማግሌዎች ውሳኔ በላይ የሆኑ ጉዳዮች ወደ ጎሳ ይተላለፋሉ፡፡ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስቸግሩ ጉዳዮች ካልተፈጠሩ በስተ ቀር ጉዳዮች በሽማግሌዎች ብቻ እልባት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

መፍትሔ ላላገኙ ችግሮች ውሳኔ እንዲሰጡ የሚመረጡ ሽማግሌዎች ጉዳዩ እንዲታይላቸው በፈለጉ ሁለት ወገኖች ይመረጣሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አንዳንድ ሰው፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ሁለት ሁለት ሰዎች ይመረጣሉ፡፡ ከሁለቱም በኩል የተመረጡት ውክልና አለባቸው፡፡ የሚመረጡት ሽማግሌዎች በሁለቱም በኩል ዝምድና የሌላቸው መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ፍርድን እንዳያዛንፉ ታስቦ የተደረገ ነው፡፡ አድልኦ የሌለበት እና በጥንቃቄ ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያደርግ የኦሮሞ ባህላዊ ሽምግልና ተቋም አርአያነት ያለው የፍትህ አካል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሲንቄ የኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ከመሠረታቸው ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ከሴቶች መብትና ሥልጣን ጋር ከፍተኛ የሆነ ትስስር ያለው ሲሆን የሴቶችን መብት በማስከበር ረገድ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

ሆሮሩና ቦኩ የአባገዳ እና የአባቦኩ ሥልጣን አቅም እንደሚገልፁት ሲንቄም የሴቶችን ክብር እና ሥልጣን ይገልፃል፡፡ ሲንቄ አንዲት ሴት ልጅ በምትዳርበት ቀን በእናቷ የሚበረከትላት ዘንግ ነው፡፡ ይህ ስጦታ በኦሮሞ ባህል እናት ለልጅ የመዋለድ ወይም ወልዳ የመሳም እና የማቀፍ ምኞት መግለጫ ተምሳሌት ነው፡፡ ስለዚህም ጥሩ ኑሮ እንዲኖራት ምኞቷን የምትገልፅበት ነው፡፡ የምትዳረው ልጅ በሲንቄ በጋብቻዋ ዕለት ትማታበታለች፣ በዚህም በንብረቷ

ላይ ያላትን መብት ታስከብርበታለች፣ የወንዶችን ትምክህት የምትመከትበት እና መብቷን የምታስከብርበት ነው።

በሌላ በኩል ሲንቄ የበዓል ዘንግ ነው። የቡነ ቀላ ሥርዓትና እንደ ኢሬቻ በዓል ያሉት በሚከበሩበት ቀን ሴቶች ይዘው ወደ አደባባይ የሚወጡ የክብር ዘንግ ነው። ሲንቄ ከተለያዩና ከተመረጡ የእንጨት ዝርያዎች ተቆርጦ ለክብር ተምሳሌት የሚውል የባህል ዘንግ ነው። የሕግ ድጋፍም አለው።

ሲንቄ በኦሮሞ ባህል ትልቅ ሀይል አለው። ከፍተኛ ግጭት ተፈጥሮ ጦርነት ቢጀመር ሴቶች ተሰብስበው ሲንቄ ይዘው እልል እያሉ መሀል ቢገቡ ጦርነቱ ወዲያው ይቆማል። ሲንቄን ይዘው ሴቶች አለምንም ፍርሃት ጦርነት መካከል ቢሆን ይገባሉ። ከቦኩ እኩል ክብርና ሥልጣን አለው። ሲንቄን የያዙ ሴቶች ለምነው የማስታረቅ፣ ከሰው የማስቀጣት፣ ሥልጣንና መብት አላቸው።

(ምንጭ፦ የገዳ ሥርዓት፣የቱለማ ኦሮሞ ፖለቲካ ቅጽ አንድ ወደ አማርኛ አጥሮ ተተርጉሞ ለማስተማሪያነት የተወሰደ።)

## ተግባር

1.ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆነ አውነት ስህተት ከሆነ ሐሰት በማለት መልሱ።

1.በሽምግልና የማስታረቅ ባህል ጥንታዊ የኦሮሞ ባህል ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እየተሰራበት አይደለም።

2. በሽምግልና ቅሬታ ያለው አካል ይግባኝ መጠየቅ ይችላል።

3. በሽምግልና ያልተፈታ ጉዳይ ለመንግስት ፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡

4.መፍትሄ ላላገኙ ጉዳዮች ውሳኔ እንዲሰጡ የሚመረጡ ሽማግሌዎች ጉዳይ እንዲታይላቸው ከፈለጉ ሁለት ወገኖች ይመረጣሉ፡፡

5.ሲንቄ በገዳ ሥርአት ውስጥ ተቀባይነት የለውም ፡፡

2.በምንባቡ መሠረት ተክክለኛ የሆነውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡

1.በምንባቡ መሠረት የሽምግልና ሥርዓት የሚሰጠው በማንነው?

ሀ. በሽማግሌዎች ለ. በአዛውንቶች ሐ. በወጣቶች መ. ሀ እና ለ

2. በሽምግልና ያልተቻሉ ጉዳዮች በይግባኝ ለማን ይቀርባሉ?

ሀ. ለጎሳ አለቃ ለ. ለአቃቤ ሕግ ሐ. ለፍርድ ቤት መ. ለአዋቂ

3. ስንቄ ምንድነው?

ሀ. የክብር አለንጋ ለ. የክብር ዘንግ ሐ. የበአል ዘንግ መ. ለ እና ሐ

4. በገዳ ሥርዓት ውስጥ ሲንቄ ከ ---------------- ሥልጣን ጋር ከፍተኛ ትስስር አለው፡፡

ሀ. ሴቶች ለ. ወንዶች ሐ. ሽማግሌዎች መ. ወጣቶች

5.የሁለት ሰዎችን ጉዳይ ለመፍታት ሽማግሌዎች የሚመረጡት እንዴት ነው?

ሀ. ከተበዳይ ወገን ብቻ ነው　　ለ. ከበዳይ ወገን ብቻ

ሐ. ከተበዳይና ተበዳይ ወገን　　መ. ከዳኞች

3.ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: በእያንዳንዳቸው ዓረፍተነገር ሥሩባቸው::

ሀ. ዘንግ

ለ. መፍትሄ

ሐ. እርቅ

መ. ሀይል

ሠ. የተካተቱ

ረ. እልባት

ሰ. ግጭት

ሸ. መፍታት

ቀ. ገጽታ

በ. አካል

## ክፍል አራት:- ቃላት

### ተግባር

1. ቀጥሎ በምድብ ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን ቃላት በምድብ ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ውስጥ ትርጉም ናቸው ካላችኋቸው ቃላት ጋር አዛምዱ::

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
| --- | --- |
| 1. ህብረት | ሀ. አዲስ |

2. ስራ — ለ.ተግባር
3. እውነት — ሐ. ስኬት
4. ውጤት — መ.ደቦ
5. ዘመናዊ — ሠ.ሀቅ

2. ከታች ለቀረቡት ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ ፡- ገሰፀ- መከረ፣ ተቆጣ

1. ገሰፀ
2. ሰረጸ
3. ወደር
4. ችቦ
5. ችርቻሮ
6. ስር
7. ግርማ
8. ስርዓት
9. ግርማ
10. ጥምር

**ክፍክ አምስት፡-** ስዋሰው

ማስታወሻ

የቃል ግንድ ምንለው ቅጥያዎችን በመነሻና በመድረሻ ላይ በማስቀጠል ቃላትን ለማርባት ወይም አዳዲስ ቃላትን ለመመስረት የሚረዳን ቃል ነው፡፡

በአንድ ቃል (ግንድ) በመነሻ ላይ የሚቀጠሉ ቅጥያዎች ቅድመ ግንድ ቅጥዎች ይባላሉ፡፡ በቀሉ መጨረሻ ላይ የሚገኙትን ቅጥያዎች ደግሞ ድህረ ግንድ ቅጥያዎች እንላቸዋለን፡፡

ምሳሌ 1፡- አስደገመን

አስ፡-ቅድመ ግንድ ቅጥያ

ደገመ፡- ዋና ቃል(ግንድ)

ምሳሌ 2፡- ከሰው

ከ፡- ቅድመ ግንድ ቅጥያ

ሰው፡- ዋና ቃል(ግንድ)

ን፡- ድህረ ግንድ ቅጥያ

ምሳሌ 3፡- አጠበኝ

አጠበ ዋና ቃል (ግንድ)

ኝ፡- ድህረ ግንድ ቅጥያ

ምሳሌ 4፡- ወይኒቱ

ወይን፡- ዋና ቃል

ኢት፡- ድህረ ግንድ ቅጥያ

ኡ፡- ድህረ ግንድ ቅጥያ

ሌ 5፡- እንዳይገዛ

እንደ፡- ቅድመ ግንድ ቅጥያ

አይ፡- ቅድመ ግንድ ቅጥያ

ገዛ፡- ዋና ቃል

## ተግባር

1. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ ተመርኩዛችሁ ከታች ቀረበውን ሰንጠረዥ ሙሉ


| ተ.ቁ | ሙሉ ቃሉ | ቅድመ ግንድ ቅጥያ | ድንድ (ዋና ቃል) | ድህረ ግንድ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በሚስማር | | | |
| 2 | እርሳሱ | | | |
| 3 | ወገኔ | | | |
| 4 | ተሰረቀ | | | |
| 5 | እንደለመደው | | | |
| 6 | በየድንበሮቻቸው | | | |
| 7 | የአባቱ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 8 | ኢትዮጵያዊነት | | | |

2. የሚከተሉትን ቅድመና ድህረ ቅጥያዎች ከክብ ውስጥ በመጠቀም የተለያዩ ቃላትን ፃፉ፡፡

ምሳሌ - ኤ፡- ደብተር - ኤ ደብተሬ

1. ------------------ 6-------------------------------
2. -------------------- 7-------------------------------
3. ------------------- 8.-------------------------------
4. .---------------------- 9.----------------------------
5. ----------------------- 10.--------------------------



# ምዕራፍ ሁለት

## የህይወት ተሞክሮ

## የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ላዳመታችሁት ምንባብ የቃልና የፅሑፍ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- የጓደኞቻችሁን የህይወት ተሞክሮ ከራሳችሁ ጋር በማነፃፀር ግንዛቤ ትወስዳላችሁ፡፡
- በምትኖሩበት አካባቢ ስለምታውቋቸው ሰዎች የህይወት ተሞክሮ የሰበሰባችሁትን መረጃዎች በክፍል ውስጥ በማቅረብ ልምድ ትወስዳላችሁ፡፡
- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የቀረቡ ጥቄዎችን በመስራት የመናገር ክሂላችሁን ታዳብራላችሁ፡፡
- ስለ በጎ አድራጎት የቀረበላችሁን ምንባብ በማንበብ ስለጉዳዩ የሚኖራችሁን ግንዛቤ ታሰፋላችሁ፡፡
- በምታነቡት ፅሑፍ ላይ ለሚገኙ ቃላት አገባብአዊ ፍች ትፅፋላችሁ፡፡
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- የአያያዥ ቃላትና ሐረጋትን አይነትና አገልግሎት ታውቃላችሁ፡፡
- በፅሑፍ ውስጥ አያያዦችን በተገቢው ቦታ አስገብታቹ ትጠቀማላችሁ፡፡
- በግለ ታሪክና የግለሰብ የህይወት ታሪክ አጻፃፍ ስልቶች

ግለታሪክ ይፅፋሉ፡፡

- ስለቃል ክፍሎች አይነትና አገልግሎት ይናገራሉ፡፡
- የልቦለድ አላባውየንን ይገልፃሉ፡፡
- ልቦለድ አንብበው ዋና እና ንዑስ ገፀባህሪያትን ለይተው በፅሑፍ ያሳያሉ፡፡

## ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

#### ተግባር

1. የህይወት ልምድ ተሞክሮ ስንል ምን ማለታችን ነው?


2. የጓደኞቻችሁን የህይወት ተሞክሮ በማዳመጥ ከራሳችሁ የህይወት ተሞክሮ ጋር አነፃፅሩ፡፡

3.እናንተ አለን ብላችሁ የምታስቡት ወይም ሌሎች ሰዎች ያሏቸው ተሞክሮዎች ሁሉ ጠቃሚዎች ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

# ድህረ ማዳመጥ

## ተግባር

1. ካዳመጣችሁት ምንባብ በመነሳት ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩትን የህይወት ልምዶች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።



2. መምህራችሁ ያነበቡላችሁን ምንባብ መሰረት በማድረግ በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ጅምር ሀሳብ በ"ለ" ስር ከተዘረዘሩት ጋር በማዛመድ መልእክቱን አሟሉ፡፡

| ‹ ‹ ሀ › › | ‹ ‹ ለ ›› |
|---|---|
| 1. አልበርት አንስታይን<br>2. 80 በመቶ የሚሆኑት ሀብታሞች<br>3. ከ89 በመቶ በላይ ሚሊየነሮች<br>4. 76 በመቶ የሚሆኑት<br>5. ከ65 በመቶ በላይ ሚሊየነሮች<br>6. 88 በመቶ ባለሀብቶች<br>7. 50 በመቶ የሚሆኑባለሀብቶች<br>8. ቶም ኮርሌ<br>9. 15 እስከ 30 ደቂቃ<br>10.233 ባለፀጎችን | ሀ. የህይወት ልምዳቸውን ያጋሩ<br>ለ የጥሞና ጊዜ ይሰጣሉ<br>ሐ. በቀን 10 ሰዓት ያክል ይተኛል፡፡<br>መ. የራሳቸው ግብ አላቸው<br>ሠ. መፃሃፍትን ማንበብ ያዘወትራሉ<br>ረ. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያደርጋሉ<br>ሰ. የሒሳብና የገንዘብ እቅድ ባለሞያ<br>ሸ. ከሶስት በላይ ገቢ ምንጭ አላቸው<br>ቀ. በቀን ከ7 - 8 ሰዓት እንቅልፍ ይተኛሉ<br>በ. ከ3 ሰዓት በፊት ከእንቅልፋቸው ይነቃሉ |

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

### ተግባር

1. ከስር ለቀረቡት የመናገር ክሂል ትምህርትን የሚያሳልጡ ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው ምላሽ ስጡ

ሀ. በሀገር ደረጃ ወይም በአካባቢያችሁ አስተማሪ የሆነ የህይወት ተሞክሮ ካሏቸው ግለሰቦች መካከል አንዱን መርጣችሁ የግለሰቡን የህይወት ተሞክሮ ክፍል ውስጥ ተናገሩ ።

ለ. የግብር አሰባሰብን በተመለከተ ከገቢዎች መስሪያ ቤት ከተለያዩ ቦታዎች መረጃ በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ ።

ሐ. ግብር መክፈል ለሀገር እድገት የሚኖረውን አስተዋፅኦ ከምታውቋቸው ሰዎች የህይወት ተሞክሮ በመነሳት በቡድን ተወያዩ ።

## ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

### ቅድመ ምንባብ

### ተግባር

1. በጎ አድራጎት ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. በእናንተ አተያይ በጎ ሰው የምትሉት እንዴት ያለውን ነው?
3. በሀገር ደረጃ ወይም በአካባቢያችሁ የበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ በመሳተፍ ተሞክሮ ያላቸውን ሰዎች በመጥቀስ ከነሱ የተማራችሁትን ነገር ለክፍል ጓደኛችሁ ተናገሩ።

## ምንባብ

## የሺዎች እናት

የክብር ዶክተር አበበች ጎበና በዚያን ወቅት ሸዋ ተብሎ በሚጠራው ክፍለ ሃገር ሰላሌ አውራጃ ሸበል በምትባል የገጠር መንደር በእኛ አቆጣጠር 1931ዓ.ም ተወለዱ::

አበበች ጎበና ሕፃናት ክብካቤና ልማት ማሕበር (አጎሕልማ) ካሰፈረው የሕይወት ታሪካቸው እንደተገኘው አባታቸው ከጣልያን ጋር በነበረው ጦርነት የተገደሉ ሲሆን አበበች እስከ ዘጠኝ አመታቸው ያደጉት በአያቶቻቸው ቤት ነው::

በዘጠኝ አመታቸው በነበረው ባህል መሰረት ተገደው እንዲጋቡ ተደረጉ በወቅቱም ደስተኛ አልነበሩም ይባላል::

በኋላም በአዲስ አበባ መጥተው መሰረታዊ የሚባል ትምህርት የተከታተሉ ሲሆን በአንድ ኩባንያ ውስጥ በጥራት ተቆጣጣሪነት ስራ አገኙ::

አበበች ጎበና በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደምት የተባለውንና ሕፃናት ክብካቤና ልማት ማሕበር (አጎሕልማ) የተሰኘ ወላጅ አልባዎች ህፃናት ማሳደጊያ መስራች ናቸው::

ለዚህም መነሻ የሆነው ወሎ በሚገኘው የግሸን ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ለመሳለም ሃይማኖታዊ ጉዞ ባደረጉበት ወቅት ነው::

ቦታው በረሃብ ተጠቅቶ የነበረ ሲሆን ከጉዟቸው ሲመለሱም አንድ ህፃን ልጅ ከሞተችው እናቱ አጠገብ ተኝቶ አዩ::

ልጁንም አንስተው ወደ ቤታቸው ወሰዱት:: በዚህም አላበቃም

ቤታቸው ወሰዱ።

በአንድ አመት ውስጥም 21 ወላጅ አልባ ህፃናትን ለማሳደግ ወደቤታቸው ያመጡት አበበች ጎበና ፍቅርና ደግነታቸውም ለሶስት አስርት አመታት አብሯቸው ቀጠለ።

በራሳቸው ጥረት ብቻ የነበረው ሁኔታ ተቀይሮ ቀስ በቀስም እርዳታ ማግኘት የጀመሩት አበበች በአውሮፓውያኑ 1986 የወላጅ አልባ ህፃናት ማሳደጊያቸውን አስመዘገቡ።

የአበበች ጎበና ወላጅ አልባ ትምህርት ቤት በአዳሪነት 200 ተማሪዎችን እንዲሁም 482 ተመላላሽ ተማሪዎችን እንደሚያስተምር ከድርጅቱ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል።

ያሳደጓቸው ልጆች 'እዳዬ' ብለው ይጠሯቸዋል። ይህ ስም ዛሬ የሚሠሩትን እንደሚገልጽ እምነታቸው ነው፡፡፡፡

ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ ተጋላጭ ለሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ልጆች ድጋፍ መደረጉን አበበች ጎበና የመሰረቱት አበበች ጎበና ሕጻናት ክብካቤ ልማት ማኀበር ይገልጻል።

ለዚህ መልካም ተግባራቸው ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለአበበች ጎበና የክብር ዶክትሬት ዲግሪ መስጠቱ ይታወሳል።

የሺዎች እናት ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና በኮቪድ 19 (ኮሮና) ተይዘው ህክምና ሲከታተሉ ቢቆዩም በተወለዱ 82 አመታቸው ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል።

(ምንጭ፡ WWW.BBCAMHARIC.COM አበበች ጎበና ሕፃናት ክብካቤና ልማት ማሕበርን ዋቢ አድርጎ ካቀረበው ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ምንባብ ምንባብ

### ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቀዎች በምንባቡ መሰረት ከቀረቡት አራት አማራጮች ትክክለኛ የሆነውን መርጣችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. በምንባቡ መሰረት የአበበች ጎበና የትውልድ ስፍራ የት ነው?

ሀ. ወሎ ክፍለሀገር ሸበል የገጠር መንደር

ለ. ሰላሌ አውራጃ ሸበል የገጠር መንደር

ሐ አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለከተማ

መ. ሸዋ ክፍለሀገር ግሸን አምባ መንደር

2.ለአበበች ጎበና የበጎ አድራጎት ድርጅት መመስረት ምክንያት የነበረው ነገር ምንነበር ?

ሀ. የወሎ ረሀብ　　　　ሐ. መንግስታዊ ሀላፊነት

ለ. ሀይማኖታዊ ተልዕኮ　　　　መ. ሁሉም

3.የአበበች ጎበና የወላጅ አልባ ህፃናት ማሳደጊያ ህጋዊ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበው በስንት አመተ ምህረት ነበር?

ሀ. በአውሮፓውያን አቆጣጠር 1898 ዓ.ም

ለ. በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1898 ዓ.ም

ሐ. በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1986 ዓ.ም

መ. በአውሮፓውያን አቆጣጠር 1986ዓ.ም

4.በህፃናት ማሳደጊያ ውስጥ የሚያድጉ ልጆች አበበች ጎበናን የሚጠሯቸው ምን ብለው ነው?

ሀ. እማዬ　　ለ.እታዬ　　ሐ. አዳዬ　　መ. እማማዬ

5.በምንባቡ መሰረት የአበበች ጎበና የህጻናት ማሳደጊያ ውስጥ በአዳሪነት የሚያድጉ ህፃናት ጠቅላላ ቁጥር------ ነው፡፡

ሀ. 482 ለ. 200 ሐ. 400 መ 121

6. በምንባቡ መሰረት አበበች ጎበና የሞቱት በምን ምክንያት ነው?

ሀ. በእርጅና ሐ. በኮሮና ወረርሽኝ

ለ. በድንገተኛ አደጋ መ. በልብ ህመም

7.አበበች ጎበና ለሀይማኖታዊ ጉዞ በሄዱት ወቅት የተመለከቱት ነገር ምን ነበር?

ሀ. እናቱ አጠገብ የተኛ ህፃን

ለ.እናትና አባታቸው የሞቱባቸው ህፃናት

ሐ. የሞቱ ህፃናት አጠገብ የተኙ እናቶች

መ . ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

8. በምንባቡ መሰረት የአበበች ጎበና በጎአድራጎት ድርጅት ትክክለኛ መጠሪያ ስም ማን ይባላል?

ሀ. አበበች ጎበና ሕፃናት ክብካቤና ልማት ማሕበር

ለ. ዩኒሴፍ የህፃናት ማሳደጊያ

ሐ. አበበች ጎበና ሴቶችና ህጻናት መርጃ ማዕከል

መ. አበበች ጎበና በጎአድራጎት ድርጅት

9.እንደ ምንባቡ ገለፃ አበበች ጎበና የተዳሩት፣

ሀ.ለአቅመ ሄዋን ደርሰው ነው ለ. ገና በልጅነት አእድሜያቸው ነው

ሐ. በጠለፋ ነው መ. በግል ተነሳሽነት ነው

10. በምንባቡ መሰረት አበበች ጎበና በአያቶቻቸው ቤት ያደጉት ለምንድነው?
   ሀ. አባታቸው ሊድሯቸው በመሆኑ
   ለ. እናትና አባታቸው ስለተፋቱ
   ሐ. አያቶቻቸው ከተማ ስለሚኖሩ
   መ. አባታቸው በጣሊያን ጦርንት ስለሞቱባቸው

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላት አገባባዊ ፍቺ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. መነሻ
2. ተጠቅቶ
3. እርዳታ
4. ድጋፍ
5. ወላጅ አልባ
6. ሦስት አስርት
7. ቀደምት
8. ቦታ

## ክፍል አራት፡ መፃፍ

### ተግባር

1. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት በተገቢው ቦታ በማስገባት ክፍት ቦታዎችን አሟሉ፡፡

እንጂ ፣ ስለሆነም፣ ግን፣ ይሁንእንጂ፣ ነገርግን፣ ደግሞም፣ አለበለዚያ፣ ደገሞ፣

1. ተስፋዬ በጣም ጎበዝ ተማሪ ____________ ተባብሮ የመስራት ፍላጎቱ በጣም አናሳ ነው፡፡
2. ከሰበታ ወደ እህቴ ቤት እየሄድኩ ጓደኛዬን ከሩቅ አየሁት ____________ ፊቱን አዙሮ ስለነበር ሊያየኝ አልቻለም፡፡
3. ሁሉም ነገር በመቻቻልና በመከባበር ሊያልቅ ይችላል በሀገር ሉአላዊነት የመጣ ከሆነ____________ ድርድር አናውቅም፡፡
4. ቦንቱ ባልታወቀ ምክንያት የስድስተኛ ክፍል ትምህርቷን

አቋርጣለች፤ ____________ ለወላጆቿ ማሳወቅ ይገባናል።

5. ጀሚላ፣መሐመድና ብርትኳን የስነ ፅሑፍ ውድድሩ ላይ በመሥራት ትምህርት ቤታቸውን ለማስጠራት ተነስተዋል፤____________ እንሚያደርጉት አልጠራጠርም።
6. ጊዜ ይፈጃል ____________ አባይ ግድባችን ተጠናቆ እራትም መብራትም መሆኑ አይቀርም።
7. ሁሉም ተማሪ ለሀገሩ ሰላም ዘብ መቆም አለበት፤____________ የመጀመሪያ ተጎጂዎች እኛው ነን።
8. ____________ከሱም ብሶ ይቅርታ አልጠይቅም ማለቱ ምን ይባላል?

ማስታወሻ

የህይወት ታሪክ አጻጻፍ

የህይወት ታሪክ በሁለት መንገድ ሊጻፍ ይችላል። እነርሱም፦

1. የራስ የህይወት ታሪክ (ግለ ታሪክ) እና

2. የግለሰብ የህይወት ታሪክ ናቸው።

1. ግለ ታሪክ

ግለ ታሪክና የህይወት ታሪክ አጻጻፍ ፡-ግለ ታሪክ አንድ ግለሰብ በህይወት እያለ ከውልደቱ፣ በሕይወት እስከቆየበት ድረስ ለሰዎች ባካፍለው ያስተምራል በማለት ያመነበትን የህይወት ተሞክሮ ራሱ ወይም በሌላ ሰው የሚያፅፈው፣ የግለሰቡን ማንነት፣ የትውልድ ስፍራ የትምህርት ደረጃ፣ ዕውቀት፣ ክሂሎት፣ ውጣውረድ፣ ስኬት፣ የወደፊት እቅድና ምኞት የሚተርክበት ጽሑፍ ነው።

## 2. የግለሰብ የህይወት ታሪክ

የህይወት ታሪክ የአንድን ግለሰብ ታሪክ ይመለከታል። ይህ ጽሑፍ እውነት የሆኑ ነገሮች የሚቀርቡበት እንጂ ፈጠራ አይደለም።

ጽሑፉን የሚያዘጋጀው ሰው ስለባለታሪኩ አስተማማኝ መረጃዎችን መሰብሰብ አለበት። የሚጻፈው ታሪክ ከስሜት ውጭ የሆነ፣ በእውነት ላይ የተመሠረተ፣ በአንባቢያን ዘንድ ተቀባይነትና ተነባቢነት እንዲኖረው ይጠበቃል።

የህይወት ታሪክ የሚጻፍበት ዓላማ አለው። ከተጻፈው ታሪክ አንባቢያን ትምህርት በማግኘት የራሳቸውን ስብዕና ለመገንባት እንዲረዳቸው ታስቦ ይጻፋል። ለምሳሌ ባልቻ አባነፍሶ፣ የጃገማ ኬሎ፣ አበበ ቢቂላ፣ለማ ጉያ፣ የአብዲሳ አጋ ወ.ዘ.ተ የህይወት ታሪኮች በተለያዩ ፀሐፊዎች ተጽፈው ለንባብ ስለበቁ አስተማሪነታቸው የጎላ ነው።

የህይወት ታሪካቸው የሚጻፍላቸዉ ግለሰቦች ታሪካቸው ወጣቱን ትውልድ ለማስተማር ይረዳል የተባሉት ብቻ መሆን ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ በአንድ ሀገር የሚገኙ ስመጥር ያገር መሪዎች፣ እውቅ ተመራማሪዎች፣ሳይንቲስቶችና ጀግኖች የሀገሪቱ ሀብትና ቅርስ በመሆናቸው ታሪካቸው ተጽፎ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

2. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በምትኖሩበት ማህበረሰብ ወስጥ አርኣያነት ያለው ተግባር የሰራን የአንድ ግለሰብ የህይወት ታሪክ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

3. ስለራሳችሁ የምታውቁትን ነገር የግለ ታሪክ አፃፃፍ ዘዴን ተከትላችሁ አጭር ፅሑፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

## ክፍል አምስት፡ ሰዋስው

ማስታወሻ

የቃል ክፍሎች

በዘመናዊው የአማርኛ ሰዋስዋዊ ጥናት መሰረት የቃል ክፍሎች ስም፣ ቅፅል፣ግስ፣ ተውሳከ ግስ እና መስተዋድድ በመባል በአምስት ይከፈላሉ ፡፡ በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹን ሦስት የቃል ክፍሎች ለማየት እንሞክራለን፡፡

1 ስም - ምሳሌ፡- አያንቱ፣ ጨረቃ፣ አባት፣ ሀገር፣ አንተ፣ እሱ...

2. ቅፅል - ምሳሌ፡- ትንሽ፣ ትልቅ፣ቀጭን፣ ወፍራም፣ ነጭ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣...

3.ግስ - ምሳሌ  በላ፣ ጠጣ፣ ገደለ፣ ደበደበ፣ አበደ፣ ሆነ፣ ነው...

4.ተውሳከ ግስ-  ምሳሌ ቶሎ፣ ገና ፣ ክፉኛ፣ ምንኛ፣ ልገመኛ፣ እየሮጠ፣ ትናንትወዘተ...

5.መስተዋድድ  ምሳሌ፡- እንደ፣ አሰ፣ ስለ፣ ወደ፣ በ፣ ከ፣ ለ፣ የ እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

## ተግባር

1.ቀጥሎ የቃል ክፍሎችን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል ከተሰጡት አራት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

1. ሌንሳ እንደ አበባ ትዕግስት የላትም የተሰመረበት ቃል------ ነው፡፡

ሀ. መስተዋድድ ለ. ቅፅል ሐ. ግስ መ. ስም

2. ሰሚራ ጎበዝ ተማሪ ነች በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ቅፅሉ የቱ ነው?

ሀ. ሰሚራ ለ.ተማሪ ሐ. ጎበዝ መ. ነች

3. ጋዲሳ ብዙ ከብቶች ሊሸጥ ወደ ገበያ ሄደ፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ስንት ስሞች አሉ?

ሀ. ሦስት ለ. ስድስት ሐ. አራት መ. አንድ

4. ከሚከተሉት የስም አይነቶች የተፅዖ ስም ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. አልማዝ ለ. ወጨጫ ሐ. አዋሽ መ.ወታደር


5. የፊርዶሳ እናት በጣም ደግ ናቸው፡፡ በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለው ግስ--------- ነው፡፡

ሀ ናቸው ለ. በጣም ሐ. ደግ መ. እናት

6. ድሪባ ወደቤቱ እየሮጠ ሄደ፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተውሳከ ግስ ሚና ያለው ቃል/ ሐረግ የትኛው ነው?

ሀ. ሄደ ለ. እየሮጠ ሐ. ወደ መ. ድሪባ

2. ስለቃል ክፍል የተማራችሁትን መሰረት በማድረግ የሚከተለውን የቢጋር ክብ ሞልታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ




3. ከዚህ በታች በ ” ሀ “ ስር ለቀረቡት ቃላት አይነታቸውን ከ ” ለ “ ስር ፈልጋችሁ አዛምዱ::

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ጊቤ፣ጨኮ፣አርሲ | ሀ. ቅፅል |
| 2. እየ፣ በ፣ እንደ | ለ. ግስ |
| 3. ሄደ፣ መረገ፣አረሰ | ሐ. ተውሳከ ግስ |
| 4. ክፉኛ፣ ገና፣ ልግመኛ | መ. መስተዋድድ |
| 5. ታታሪ፣ክቡር፣ጠይም | ሠ. ስም |

## ክፍል ስድስት፡ ስነ-ፅሑፍ

1. ተማሪዎች! በስድስተኛ ክፍል ስለ ልብወለድ አላባውያን የተማራችሁትን በማስታወስ ቀጥሎ የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች በፅሑፍ መልሱ፡፡

ሀ. ከልብ ወለድ አላባውያን ውስጥ የምታውቋቸውን አምስት አላባዎች ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ለ. ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ተረት አንብባችሁ በታሪኩ ውስጥ የተካተቱትን ገፀ ባህሪያት አብይ እና ንዑሳን በማለት ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

### ሁለት መንገደኞች

በጥንት ዘመን ፍየልና በግ በጓደኝነት ይኖሩ ነበር፡፡ የሚኖሩበት ስፍራ ሳር የሞላበትና ንፁህ የወንዝ ውሃ የተትረፈረፈበት ስለነበር ለረዥም ጊዜ በደስታና በተድላ ኖሩ፡፡

ነገርግን አንድ ቀን ሳር ግጠውና የወንዝ ውሃ ጠጥተው አረፍ እንዳሉ ፍየል፣ ‹‹ የዚህን መንደር ውሃ መጠጣት ሰልችቶኛል፤ ስለዚህ ዛሬ የተለየ ውሃ መጠጣት ስላለብኝ ወደ ሆራ እንሂድ አለች፡፡ ›› ሆራ የምንጭ ስም ነው፤ ውሃውም በጣም ይጣፍጣል፡፡ ሆኖም እዚያ ለመድረስ በርካታ አራዊትን በማለፍ ሁለት ቀን ሙሉ መጓዝ ያስፈልጋል ፡፡

በዚህም ምክንያት ስጋት ያደረባት በግ፣ ‹‹አውሬ ካጋጠመንስ ምን እናደርጋለን ?›› ስትል ጠየቀቻት ፡፡‹‹መላ መፍጠሩን ለኔተይውና እንሂድ! ›› አለቻት ፍየል፡፡ ጫካውን እያቋረጡ ሲጓዙ ነብር አገኛቸው፡፡ ነብሩም አደን ውሎ ስላልቀናው ተስፋ

እግዜር እቤቱ ድረስ ስለላከለት አመስግኖ ቀረባቸው፡፡

በዚህን ጊዜ ፍየል ፈጠን ብላ፣ ‹‹ እሰይ! በጊዜ ቀናን ›› እያለች ፈጣሪዋን ታመሰግንና በደስታ ትፍለቀለቅ ጀመር፡፡

ነብሩም ግራ ተጋብቶ፣ ‹‹ ይህን ያህል የሚያስፈነድቅ ምን ነገር ተገኘ?›› ሲል እየተንቀባረረ ጠየቃት፡፡ ፍየሏም መልሳ፣ ‹‹ እግዜር ወዳንተ ልኮን እየፈለግንህ ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉ ስንፈልግህ ብንውልም አላገኘንህም፡፡ ስለዚህ ተስፋ ቆርጠን እያለ በመምጣትህ በጣም ተደሰትን፡፡ ለማንኛውም ተነስና እንሂድ ! ›› አለችው፡፡ ‹‹ ወዴት?›› ‹‹ ወደ ፈጣሪ ዘንድ ነዋ! ›› ‹‹ምንብሎ ነው የላካችሁ?›› ከገባበት ገብታችሁ አምጡት! ››ብሎ አዞናል፡፡ ነብሩም ጥቂት አሰብ ሲያደርግ ቆይቶ የበላው ከብት፣አንቆ የጠጣው የዱር እንስሳት ደም ከፊቱ ድቅን አለ፡፡ በልቡ ‹‹ሊቀጣኝ ነው የፈለገኝ ማለት ነው፡፡ ›› ብሎ ‹‹አላየነውም በሉት! ›› በማለት ወደዱሩ ተመልሶ ተሰወረ፡፡

ፍልና በግ እተሳሳቁ ጥቂት እንደተጓዙ አንበሳ አገኛቸው፡፡ እንደነብሩ ሁሉ ተደስቶ፣ ‹‹ እንዴት ያለ የተባረከ ቀን ነው!?አለ ሲጠጋቸው ፍየል ግን እንደልማዷ ሮጣ እጅ ነሳች፡፡ ያልጠበቀውን ድርጊት በማየቱ የተገረመው አንበሳ ‹‹ ምን ያስቅሻል;››አለ በቁጣ የቀሉ አይኖቹን እያጉረጠረጠ፡፡ ‹‹ ፈጣሪ ከገባህበት ገብተን ይዘንህ እንድንመጣ ስላዘዘን ቀኑን ሙሉ አንተን ፍለጋ ስንንከራተት ነው የዋልነው፡፡ በመሆኑም አሁን ስላገኘንህ ተደስቼ ነው፡፡ በል እንሂድ!›› አለችው፤ ፍየል በበኩሏ ተቀላጥፋ፡፡

አንበሳ ይህን ሲሰማ ፊቱን ቅጭም አድርጎ፣ ‹‹ አንድሽ አይተነዋል ብለሽ ብትተነፍሽ ወዮልሽ ›› ብሎ ተምዘግዝጎ ወደጫካው ገባ ፡፡

እግሬ አውጪኝ አለ፡፡

የዱር አራዊትን ሁሉ በዚህ መልክ እያሞኙ በሰላም ሆራ ደረሱ፡ ፡ ሆራ ጥቂት ቀናት እንደቆዩ ግን ፍየል አሁንም ሰለቻት፡፡ በግ በመመለሳቸው ባትስማማም ፍል አላስቆም አላስቀምጥ ስላለቻት የመልስ ጉዞ ጀመሩ፡፡ ሲመሽባቸው ዛፍ ላይ ወጥተው ተደበቁ፡፡ ባጋጣሚ ዛፉ ትልቅና አመቺ ስለነበረ የአውሬ አይነት ከትልቀቁ አስከ ትንሹ ከስሩ ተጠልሏል፡፡ በግና ፍየል ይህንን ሲያዩ

ፈጣሪያቸው ከዚህ መዓት እንዲጠብቃቸው
ፀለዩ፡፡ አራዊቱ ለአደን እንዲመቻቸው እስኪጨልምላቸው ድረስ የቀን ውሏችወውን እያነሱ ይጫወቱ ነበር፡፡

አብዛኛው ስላመለጧቸው እንስሳት ነበር የሚያወረሩት፡፡ መሬት እየቆፈሩና እየጮኹ ባንዲት ወፍራም ፍልና በአንዲት በግ በመታለላቸው የሚቆጩ ጥቂት አራዊትም ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ ግን ፈጣሪ ሆን ብሎ ፍየልና በግ አስመስሎ ከላካቸው አፋኞች በዘዴ ማምለጣቸውን ጨማምረው ተናገሩ፡፡

ይህንን ስትሰማ የተደናገጠችው በግ “ሽንቷ” መጣባት፡፡ በሹክሹክታ‹‹ ሽንቴ መጥቷል ምን ይሻለኛል?›› ስትል ጓደኛዋን ጠየቀቻት፡፡

ፍየል ‹‹ቀስ ብለሽ በጀርባሽ ተኚና በፀጉርሽ እንዲሰርግ በማድረግ ተነስተሽ ሽኚ›› አለቻት፡፡ ሆኖም በግ በጀርባዬ እተኛለሁ ስትል ተንሸራታ ወደቀች፡፡ ‹‹ጧ !›› ብላ ከመውደቋ ግን ፍየል ድምጿን ጎርነን አድርጋ ‹‹ አለቃቸውን ያዘው ! ያን የሚለፈልፈውን ፈጥነህ ያዝልኝ! እንዳያመልጥህ፤ቶሎ በል!›› ብላ አውሬዎቹ ላይ ስትጮህ ሁሉም ተደናግጠው እግራቸው ወደመራቸው አቅጣጫ

(ምንጭ፡-የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣አማርኛ ትምህርት፣ ደረጃ 2፣(ገፅ-87) በአ.ብ.ክ.መ.ት.ቢሮ እና በኖርዌይ ህፃናት አድን ድርጅት

**ሐ. ከተለያዩ መጽሀፎች፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች አጫጭር ልብወለዶችን ፈልጋችሁ በልብወለዱ ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያት ዋና እና ንዑስ ብላችሁ በመለየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡**

# ምዕራፍ ሶስት

## ሥርዓተ ፆታ

## የምዕራፉ ዋና ዋአላማዎች

ከዚህ መዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- አዳምጣችሁ ለተረዳችሁት ሐሳቦች የቃልና የጽሑፍ ምላሽ ትሰጣላችሁ፡፡
- በክፍል ውስጥ በሚተገበሩ የንግግርና የውይይት አውዶች ላይ የነቃ ተሳትፎ ታደርጋላችሁ፡፡
- ስዕሎችን በመመልከት የተረዳችሁትን ሐሳብ በቃል ትናገራላችሁ፡፡
- የቀረበውን ምንባብ በተራ ወጥታችሁ በማንበብ የተረዳችሁትን በቃልና በፅሑፍ ትመልሳላችሁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የአንቀጽ ቅርፆችን በመከተል አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡

**ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ**

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**ተግባር**

1. በፆታና በስርዓተ ፆታ መካከል ያሉ ልዩነቶች ምን ይመስሏችኂል?
2. በምትኖሩበት አካባቢ ማህበረሰቡ የሴቶችና የወንዶች እኩል ተሳታፊነት ላይ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

### ተግባር

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች "የሕይወት ተመክሮ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት በፅሑፍ መልስ ስጡ፡፡

1. ፆታ ማለት በተፈጥሮ ወንድ ወይም ሴት ሆኖ መወለድ ማለት ነው፡፡
2. የማህበረሰብ ባህል፣ ልማድ የአኗኗርና የኢኮኖሚ ሁኔታ የወንድና የሴትን ሚና ይወስናሉ፡፡
3. የስርአተ ፆታ አስተሳሰብ እድገት ማህበራዊ ጉዳይ በመሆኑ የሃይማኖት ተቋማት ምንም አስተዋፆኦ አያበረክቱም፡፡
4. የፆታ እኩልነት ማለት ሴቶችና ወንዶች እኩል መብት፣ ሃላፊነት እና እድል የማግኘት መብትን ይመለከታል፡፡
5. ስለ ስርዓተ ፆታ ያለውን የተዛባ አመለካከት በመቅረፍና እኩልነትን በማስፈን ሀገራዊ ልማትን ማፋጠን ይቻላል፡፡
6. ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ማህበረሰባችን በስርዓተ ፆታ እኩልነት ላይ ያለው አስተሳሰብ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የሚያስቀምጥ ነው

2.የሚከተሉት ቃላት ካዳመጣችሁት አጭር ምንባብ ውስጥ የተውጣጡ ናቸው፣ቃላቱ በገቡበት አውድ የሚሰጡትን ተመሳሳይ ፍች ፃፉ፡፡

1. ፆታ
2. ማንቁርት
3. ባህሪ
4. ስርዓተ ፆታ
5. በመቅረፍ
6. ትውልድ

7. አስተሳሰብ
8. ኋላቀር

## ክፍል ሁለት መናገር

ማስታወሻ

ውይይት

ውይይት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይተማክረው በመተማመን ወደ አንድ የጋራ ውሳኔ እንዲደርሱ የሚያደርግ የንግግር አይነት ነው፡፡

አንድ የውይይት መድረክ ሊቀመንበርና ፀሀፊ ያስፈልገዋል፡፡

1. የውይይት አቅራቢ በዝግጅት ወቅት ማወቅ የሚኖርበት አበይት ነጥቦች-
   - ርዕሰ ጉዳዩን በሚገባ ማወቅና መረጃ መሰብሰብ
   - የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ወቅታዊነትና ተቀባይነትን ማረጋገጥ
   - የተገኙትን መረጃዎች ቅደም ተከል ማስያዝ
   - የሚቀርቡት ነጥቦች ከአድማጭ ፍላጎት፣ልምድና ዕውቀት ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ማድረግ
   - አቀራረቡ ሁሉንም የውይይቱን አካላት የሚያሳትፍና የሚያነቃቃ ማድረግ
   - የሚቀርበው ሀሳብ የተለያዩ ጉዳዮችን የሚዳስስ እንዲሆን ማድረግ
2. ውይይት ለማካሄድ መድረክ ላይ ከመውጣት በፊትና ከወጡ በኋላ ሊተገበሩ የሚገባቸው ነጥቦች፡-

   2.1. መድረክ ላይ ከመውጣት በፊት

ሀ. ሰብዕናን ማስተካከል (ንፅህናን፣ አለባበስን፣ስነ ምግባርን ማስተካከል)

ለ. ዝግጅቶችን ማሟላትና መረጃዎችን መያዝ

2.2 መድረክ ላይ ከወጡ በኋላ

ሀ. የውይይቱን ርዕስና አላማ ማስተዋወቅ

ለ. ውይይቱን በመረጃዎች መሰረት በቅደም ተከተል ማቅረብ:: እነዚህም

- የድምፅ ምጣኔን ማስተካከልን
- የአይን አጣጣልን ማሳመር፣
- የቋንቋ ግልፅነትን መጠበቅ፣
- የጊዜ ገደብን ማክበር፣
- ለጥያቄና መልስ በቂ ጊዜ መስጠት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል::

ሐ. የውይይቱ መሪ ሳይፈቅድ/እድል ሳይሰጥ ማንኛውም ተሳታፊ ከመናገር መቆጠብ

መ. አቅራቢው በተፈቀደለት የሰአት ገደብ ንግግሩን ሲጨርስ የውይይቱን ተሳታፊዎች ወይም አድማጮች ማመስገን

## ተግባር

1. በአካባቢያችሁ በሥራ ስኬታማ በመሆን ለሌሎች ሰዎች እንደ አርኣያ ሊጠቀሱ የሚችሉ ሴቶችን ተግባራቸውን በመግለፅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

2. የሴቶች ተሳትፎን ለማሳደግ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን በቡድን ሆናችሁ በመዘርዘር ለክፍል ተማሪዎች በቃል ግለፁ::

3. በከተማችን የፆታ እኩልነት አሁን ካለበት ደረጃ ለማሳደግ ባለድርሻ ናቸው የምትሏቸውን በመግለፅ ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ምን ማድረግ ይገባቸዋል፤ በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ በተወካያችሁ በኩል ሀሳባችሁን አንጸባርቁ።

4.ከታች የቀረቡትን ሁለት ምስሎች በማነፃፀር ከስርዓተ ፆታ አንፃር የተረዳችሁትን በቃል ተናገሩ።





## ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

### የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

#### ተግባር

1. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ሀሳብ ስጡ፡፡

1. በአካባቢያችሁ የሴቶችና የወንዶች ተብለው የተለዩ የስራ ዘርፎች ካሉ በመለየት ትክክለኛነታቸው ላይ ያላችሁን የግል አስተያየት ተናገሩ፡፡
2. በተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች ለሀገራቸው አስዋፅዖ ያደረጉ ወይም እያደረጉ ያሉ ሴቶችን

3. በመጥቀስ ስራቸው ለሀገር እድገት የሚኖረውን ሚና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ

ምንባብ

ሰማይ ቀዛፊ እንስቶች

በአውሮፕላን ማብረሩ ዘርፍ ፋና ወጊ ከሆኑ እንስት አፍሪካውያን መካከል ቀዳሚ የነበሩት ኢትዮጵያዊቷ ወ/ሮ ሙሉእመቤት እምሩ ናቸው። በፋሺስት ወረራ ሳቢያ ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ከሚወዱት አውሮፕላን ማብረር እንደተለያዩ ይናገራሉ። ወ/ሮ ሙሉእመቤት በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የመኪና መንጃ ፍቃድ ያወጡ እንስትም ናቸው።

ከዛሬ 82 ዓመት በፊት በ1922 ዓ.ም በጅጅጋ ከተማ የመጀመሪያው የአውሮፕላን በረራ ት/ቤት በፈረንሳዊው ሙሴ ጋስቶን ቬርዲየር መምህርነት ሲቋቋም የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ አብራሪ ወ/ሮ ሙሉእመቤት እምሩ ነበሩ። ከትምህርት ቤቱ ምስረታ በኋላ ትምህርታቸውን በትጋት ተከታትለው በ1927 የመጀመሪያ የብቻ በረራ አድርገው አየሩን የቀዘፉት በ2008 ዓ/ም ከዚህ አለም የተለዩን ዘንካታዋ አብራሪ እመቤት ወ/ሮ ሙሉእመቤት እምሩ ነበሩ። በወቅቱ ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ብቸኛ አፍሪካዊ አብራሪና አስተማሪ ነበሩና ታሪካቸዉን በማንሳት ለሌሎች እንስቶች መማሪያ እንዲሆኑ ልንዘክራቸዉ ወደድን። በወቅቱ የአብራሪዋን ስኬት እና ትጋት የተመለከተው "ስናፒ ላንዲንግ ሌዲ" በሚል እ.ኤ.አ በ1935 የታተመው አንድ የአሜሪካን ጋዜጣ አድናቆት እንደቸራቸው ዝክረ ታሪካቸው ያስረዳል ።

አፍሪካዊት ነበሩ! እ.ኤ.አ በ1930ቹ የፋሺስት ጣሊያን የአምስት ዓመት ወረራ እንደተከሰተ ከሚወዱት አውሮፕላን ማብረር የተለያዩት ወ/ሮ ሙሉእመቤት በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የመኪና መንጃ ፍቃድ የነበራቸው ሴት እንደነበሩ ይጠቀሳል፡ ፡ ይህ የሆነው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት፣ ወይም ከዛሬ 82 ዓመት በፊት ነበር፡፡ ያኔ ሳውዲ አረቢያዎች ገና በሐገር ምስረታ ላይ ነበሩ፡፡ ያኔ አለም እንደ ዛሬው ስልጣኔ ሳይስፋፋባት ኢትዮጵያ ሴት አውሮፕላን አብራሪ ነበራት፡፡

ኢትዮጵያ ውብና ደረጃቸውን የጠበቁ የበረራ አስተናጋጅና በአየር መንገዱ ቁልፍ ቁልፍ ቦታ የነበራቸው እንስቶች እናት ናት! እትዮጵያ የአዋቂ ልጆች ድሃ ሆና አታውቅም፡፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የእስካሁን ታሪክ አየር መንገዱ ከስድስት የማያንሱ ሴት ፓይለቶችን እንዳፈራ ይነገራል፡፡ ከአብራሪዎች መካከል ሙሉመቤት እምሩ፣ አሰገደች አሰፋ፣ ሶፍያ ገዛኸኝ፣ ሃና ወልዴ እሌኒ ታደሰና ሰላም ተስፋዬ ሲሆኑ በአየር መንገዱ ታሪክ ወደ ሙሉ አብራሪ ካፒቴን ደረጃ ያደገችው የመጀመሪያዋ ሴት የበረራ ካፕቴን አምሳለ ጓሉ ትጠቀሳለች፡፡ በ2002 ዓ.ም የመጀመርያዋ ሴት ካፒቴን ዋና አብራሪ በመሆን ታላቅ ክብር የተቀናጀችው ካፒቴን አምሳለ የባንኮኩን በረራ የመራችና ስኬት በትጋት እንደሚገኝ ያሳየች የእኛ ትውልድ ኮከብ ናት ፡፡ ከዚህ ባሻገር ሐይማኖት ገብረማርያም ባሳየችው ትጋት ላቅ ወዳለ የተዋጊ አውሮፕላን አብራሪት ደረጃ መድረሷ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

(ምንጭ፡አዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ 2011 ድህረ ገፅ ለምንባብ ማስተመሪያነት እንዲሆን ተሻሽሎ የቀረበ )

## የድህረ ምንባብ ጥያቄዎች

### ተግባር

1.ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የአውሮፕላን በረራ ትምህርት ቤት የተከፈተው የት ነበር?

ለ. እንደ ምንባቡ ሀሳብ ወ/ሮ ሙሉእመቤት ያረፉት መቼ ነው?

ሐ. በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት አብራሪ የአብራሪነትን ሥልጠና የወሰዱት በማን ነበር?

መ. ወ/ሮ ሙሉእመቤት ከአብራሪነት በተጨማሪ የነበራቸውን ሙያ ተናገሩ?

ሠ.ከወ/ሮ ሙሉእመቤት በተጨማሪ ያሉትን እንስት አብራሪ ኢትዮጵያውያንን ስም ዘርዝሩ።

ሰ.ከቀረበው ምንባብ ምን ተረዳችሁ?

2.ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት የሆነውን ሐሰት በማለት በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. በአውሮፕላን አብራሪ አሠልጣኝነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ግለሰብ ዜግነታቸው አሜሪካዊ ነው፡፡

2. ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ከአረብ ሀገራት ትቀድም እንደነበር ታሪክ ያወሳል፡፡

3. ወ/ሮ ሙሉእመቤት ታምሩ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ ሀገራት ቀደምት ሴት አብራሪ ናቸው፡፡

4. ወ/ሮ ሙሉእመቤት የሀገራችን የመጀመሪያ እንስት የመኪና መንጃ ፈቃድ ያገኙ ናቸው፡፡

5. የፋሽስት ወረራ በወ/ሮ ሙሉእመቤት ሥራ ላይ ተጽዕኖ አላሳደረም፡፡

6. በምንባቡ ሀሳብ ወ/ሮ ሙሉእመቤት የተወለዱበት ጊዜ በትክክል ተገልጿል፡፡

7. እንደ ምንባቡ አገላለጽ በ2002 ዓ/ም ካሉት እንስት አብራሪ ኢትዮጵያውያን መካከል የካፕቴን ደረጃ የደረሰችው አምሳለ ጓሉ መሆኗን ያስረዳል፡፡

3.ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ በገቡበት ዐውድ መሠረት ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ፋሽስት

ለ. ፋናወጊ

ሐ. መቅዘፍ

መ. ትጋት

ሠ. እንስት

ረ. ካፐቴን

ሰ. ኮከብ

ሸ. ቁልፍ ቦታ

## ክፍል አራት መፃፍ

ማስታወሻ

አንቀፅ

አንድን ሀሳብ ከሚያብራሩ፣ ከሚተርኩ ወይም ከሚገልፁ ወዘተ… ዐረፍተ ነገሮች የተገነባ የራሱ የሆነ አንድነትና ጥምረት ያለው የድርሰት አነስተኛ ክፍል አንቀፅ ይባላል፡፡


በአንቀፁ ውስጥ ያለውን ሀሳብ አጠቃሎ የያዘ፣ በእሱ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሌሎች ዝርዝር ዐረፍተ ነገሮችን ያለፈ ዐረፍተ ነገር ሀይለ ቃል ወይም መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገር ይባላል፡፡

### የአንቀጽ አረጃጀቶች

ሀይለ ቃል በአንቀፅ ውስጥ በአራት የተለያዩ ስፍራዎች ሊገኝ ይችላል፡፡


1.ሀይለ ቃል በአንቀፅ መጀመሪያ

የሀሳብ አደረጃጀቱ በሀይለ ቃል ጀምሮ በማስከተል በዝርዝር የሚፃፍ የአንቀጽ አይነት ነው ፡፡



ምሳሌ፡ <u>ፍቅር በሁለት ደረጀዎች የተከፈለ ነው፡፡</u>
የመጀመሪያው የፍቅር አይነት ጥልቀት የሌለውና ወረታዊ ሲሆን ሌላው ደግሞ ስር ሰደድ ነው፡፡ የማይለወጥና ዘላቂነት ወይም ህያውነት ያለው ነው፡፡

ከላይ በቀረበው አንቀጽ የተሰመረበት ዐረፍተ ነገር ሀይለቃሉ ወይም መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገር ሲሆን ሌሎቹ ዐረፍተ ነገሮች በመንደርደሪያው ዐረፍተ ነገር የቀረበውን ሀሳብ የሚያብራሩና የበለጠ ግልፅ የሚያደርጉ ናቸው፡፡





ምሳሌ፡- ጋዲሴ ጫማ የላትም፣ እግሯ ግን እንሶስላ የሞቀች ይመስላል፡፡ ተረከዟ ያምራል፤ፀጉሯ ሽቶና ዘይት አያውቅም፤ በሳሙና ለመታጠብ እንኳን እድል አላገኘም፤ ሆኖም እየተዘናፈለ ወርዶ የተከበረ ትከሻዋን አጥለቅልቆታል፡፡ ዐይኖቿ ኩል ነከቷቸው ባያውቁም እንደንጋት ኮከብ የሚያበሩ ናቸው፡፡ ጥርሶቿ በየጊዜው በይፋቁም እኳን ብርሀን ያንፀባርቃሉ፡፡ ጥፍሮቿ ወለም አያውቁም፣ሆኖም

ውበታቸው እፁብ ድንቅ ነው፡፡ <u>ድህነትና ውበት በአንድ አካል ላይ እንዲህ ያለ ፍፁም ህብረት ሲኖራቸው ያስተዋልኩት በጋዲሴ ላይ ብቻ ነው፡፡</u>

የተሰመረበት ዐረፍተ ነገር የአንቀፁ ሀይለ ቃል ሲሆን፣ ሌሎቹ ዐረፍተ ነገሮች በሀይለቃሉ የተጠቀሰውን የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

3. ሀይለ ቃል በአንቀፅ መሀከል





የዚህ አይነቱ የአንቀጽ አደረጃጀት በዝርዝር አረፍተ ነገሮች ጀምረን ሀይለ ቃሉን መሀከል ላይ በማስገባትና የቀሩ ሀሳቦችን በመጨመር የምንጨርስበት ነው፡፡

ምሳሌ አባቶች ያገሪቱን አፈር በደማቸው አቡክተው ያቆዩልን ባለውለታ ናቸው፡፡ ወጣቶች ደግሞ ገንቢዎች፤ ትውልድ ሰንሰለት ነው፡፡ ሁሉም በአንዴ አያረጅም፤ ሁሉም በአንዴ ወጣት

አይሆንም፡፡ሁሉም በመፈራረቅ ቀስበቀስ የሚሳብ ሐረግ ነው፡፡

ከላይ በምሳሌው እንዳየነው ዋና ሀሳቡን የሚያጎላምሱ ዐረፍተ ነገሮች ተፅፈው፣ መሃል ላይ የተሰመረበት ዐረፍተ ነገር ሀይለ ቃሉ ሆኖ ከዚሁጋር የተገናኙ ቀሪ ሀሳቦች ሀይለ ቃሉን ተከትለው የተዘረዘሩ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

4. ሀይለ ቃል በአንቀጽ መጀመሪያ እና መጨረሻ



ይህኛው አደረጃጀት በሀይለቃል ጀምሮ ዝርዝር ሀሳቦችን ያስከትልና በመጨረሻም በመነሻ ላይ የተጠቀመውን መንደርደሪያ ሀሳብ በሌላ አገላለጽ በመድገም ሀሳቡ ትኩረት እንዲያገኝ ጥረት የሚደርግ ነው፡፡

ምሳሌ፡- በገጠር የሚኖረው አብዛኛው ህዝብ አቅሙም ዕውቀቱም ስለሌለው እርሻው በትናንሽ ማሳዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሁለትና ሶስት ጥማድ ማሳ ትንሽ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው በትራክተር የሚያርሱ የዘመናዊ ገበሬዎችን የእርሻ መሬት ስፋት ማወቅ ስንችል ነው፡፡ ይህን ካላወቅን ግን አንድ ወይም ሁለት ሄክታር እርሻ ሰፊ ይመስለናል፡፡ ከዚሁ ላይ የሚገኘውን ሁለትና ሶስት ኩንታል ምርትም በዙ ነው እንላለን፡፡ እንዲያውም ዘንድሮ እህል ለጉድ ነው ብለን እናጋንናለን፡፡ ይህን የምንለው ከዘመናዊ የእርሻመሬት ላይ የሚታፈሰውን የምርት መጠን ስለማናቀው ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ችግር ምንጭ የገበሬው ዕውቀትና ሀብት ማጣት በመሆኑ ከትንንሽ እርሻ በላይ ሊኖረው አልቻለም፡፡

## ተግባር

1. ቀጥሎ ለቀረቡየአንቀፅ ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ትከክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

   1. አንቀፅ የሀሳብ አንድነትና ጥምረት ባላቸው ዐረፈተ ነገሮች የሚገነባ የድርሰት አነስተኛ ክፍል ነው፡፡
   2. ⌧ ይህ ቅርፅ በዝርዝር አረፍተ ነገሮች ጀምሮ ሀይለ ቃሉን በማስገባት በመጨረሻ የቀሩ ሀሳቦችን በማከል የሚፃፍ የአንቀፅ አደረጃጀትን ይወክላል፡፡

3. △ሀይለቃሉን በመጨረሻ በመጥቀስ በዝርዝር ሀሳቦች የሚጀምር የአንቀፅ ውቅር እንዲህ አይነት ቅርፅ ይይዛል፡፡
4. ▽ ከአንቀጽ አቀነጃጀት መንገዶች መካከል በሀይለቃል በመጀመር በዝርዝር ሀሳብ የሚቋጭ አንቀፅ ይህን ይመስላል፡፡
5. ◇ የዚህ አይነቱ ቅርፅ መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገሩን በመነሻነና በመጨረሻ ላይ ጠቅሶ መሀል ላይ ዝርዝር ሀሳቦችን በመግለፅ የሚጻፍ የአንቀጽ አይነት ነው፡፡
6. አንቀፁ የተፃፈበትን ዋና ሀሳብ የሚይዝ የዐረፍተ ነገር አይነት መዘርዝረ ሀሳብ ወይም አረፍተ ነገር ይባላል፡፡

2. የሚከተሉትን አጫጭር አንቀፆች አንብባችሁ የአደረጃጀት ቅርፃቸውን በስዕል ግለፁ፡፡

አንቀፅ አንድ

ሰዎች የህይወት ለዛና ጣዕም ጥኋቸው እንዳይሸሽ ወይም ከአድማስ ርቆ እንዳይጠፋባቸው የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ ይስተዋላሉ፡፡ ብዙዎቹ ቁሳዊ ነገሮችን እንደ መድሀኒት ስለሚመለከቱ ብዙ ሀብትና ንብረት ለማግበስበስ ይሯሯጣሉ፡፡ ሀብት ማፍራት የሚደገፍ ቢሆንም ብቻውን የደስታ ምንጭ አይሆንም፡፡ ሌሎች ደግሞ ፊታቸውን ወደመዝናኛ በማዞር ኢ- ስነምግባራዊ ተግባራትን ሳይቀር ፈጽመው በአዲስ ስሜት ስለሚሞሉ የህይወትን መልካም ጣዕም እንዳጣጣሙ ይቆጥራሉ፡፡ በዚህ አይነቱ ድርጊት የሚገኝ ደስታ ቅፅበታዊ ከመሆኑም ባሻገር ለፀፀት ይዳርጋል፡፡

አንቀፅ ሁለት

ማህበራዊ ድረ ገፆች ለመረጃ ልውውጥና ለተለያዩ ሀራት ህዝቦች መቀራረብ ያላቸው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በአንፃሩ ለአላስፈላጊ ያታዊ ትንኮሳ ለማይጠቅሙ ምስሎችና መረጃዎች ልውውጥ እንዲሁም ለማይጠቅሙ ሀይማኖታዊና ፖለቲካዊ መልዕክቶች የተመቹ በመሆናቸው ስጋትን መፍጠራቸው አይቀርም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፌስቡክን የሚጠቀሙ ሰዎች ጊዜና ገንዘባቸውን በከንቱ እያባከኑ መሆናቸውን ተረድተው ለአጠቃቀማቸው ገደብ እያበጁ ነው፡፡ አንዳንዶቹ እንዲያውም ሙሉበሙሉ እየተዉ መጠተዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ ማህበራዊ ድረገፆች ዘርፈብዙ ጉዳትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በማሰብ አጠቃቀማችንን ልናስብበት ይገባል፡፡

አንቀፅ ሦስት

የሰው ልጅ አካላዊ እንቅስቃሴና አዕምሯዊ ብቃት እስካልተገታ ድረስ በየጊዘው አዳዲስ ግኝቶች መፈጠራቸው አይቀርም ትናንት በሳይንሳዊ ምርምር አድናቆትን ያተረፉ ግኝቶች ዛሬ በሌላ ተሻሽለዋል፡፡ ይህ ሂደት ከሰው ልጅ የለውጥ ፈላጎት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ሰው በባህሪው በአንድ ነገር ላይ ረግቶ አይቀመጥም፡፡ የጓጓለትን ነገር ሲያገኝ ሌላ የጓጓለትን ነረር መሻቱ ተፈጥሯዊ ነው፡፡

አንቀፅ አራት

“ሰላም የልማትና የብልፅግና በመሆኗ ልንጠብቃት ይገባል፡፡ ክቡራን አድማጮቼ በማንኛዉም የዕለት ተዕለት ዕንቅስቃሴዎች ሰላም ከሌለ ሕይወትን በአግባቡ መምራት አንችልም፤ ሰላም ከሌለ መማር አንችልም፤ሰላም ከሌለ መስራት አንችልም፤ ሰላም ከሌለ ሀገር መገንባት አንችልም፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ለሰላም ዘብ መቆም አለብን፡

3. የሚከተሉትን መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገሮች በመጠቀም ከላይ በቀረበው የአንቀፅ አደረጃጀት መሰረት አጫጭር አንቀፆች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. ትምህርት የዕድገት መሰረት ነው፡፡
2. የአካባቢያችንን ንፅህና በመጠበቅ ከተላላፊ በሽታዎች የፀዳች ሀገር ለቀጣይ ትውልድ እናስተላልፍ፡፡
3. በጎ የሆኑ ባህሎችና ለማዶች እንዳሉ ሁሉ ጠቃሚ ያልሆኑ ባህሎችና ልማዶችም አሉ፡፡
4. የኤች.አይ. ቪ. ኤድስ በሽታ እንደመጀመሪያው ትኩረት በመነፈጉ የሀገሪቷን አምራች ዜጋ ባጭሩ እያስቀረ ይገኛል፡፡

ክፍል አምስት ስዋስው

ማስታዎሻ

ሀረግ

ተማሪዎች ቀደም ባለው ምዕራፍ ስለ ቃልክፍሎች ተምራችኋል በዘህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሐረግ ትማራላችሁ፡፡

ሐረግ ማለት የቃላት ስብስብ ሆኖ ሙሉ ሀሳብ ወይም ስሜት የማይሰጥ ነው፡፡ ሐረግ ማለት ቃላት እርስበእርስ እንደ ሰንሰለት ተያይዘው የቋንቋዋው ተናጋሪ ሀብረተሰብ በልማድ የተቀበለውን ጅምር ሀሳብ የሚያስተላልፍ የቃሎች ድርድር ነው፡፡

ዋና ዋና የሐረግ አይነቶች አምስት ናቸው፤ እነርሱም፣

1. ስማዊ ሐረግ

ስምን መሪው አድርጎ የሚመሰረት የሐረግ አይነት ስማዊ ሐረግ ይባላል፡፡

ምሳሌ፡-

- ቀይ ቦርሳ
- የፍቅር ሀገር
- ቆንጆ ልጅ

1. ግሳዊ ሐረግ

ግስና የግስ ገለጮች አንድላይ በመሆን የሚመሰርቱት የሐረግ አይነት ነው፡፡

- ሁል ጊዜ ያጠናል
- ክፉኛ ታመመ
- ትናንት መጣ

2. ቅጽላዊ ሐረግ

የቀኝ መሪውን ቅጽል አድርጎ ከሌሎች አጎላማሽ ቃሎችና ሐረጎች የሚዋቀርን የሐረግ አይነት ቅጽላዊ ሀረግ እንለዋለን፡፡

ምሳሌ -

- በጣም ቁይ
- እጅግ ሲበዛ ደግ
- እንደ አባቷ ረዥም

3. ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ

ተውሳከ ግስን መሪ ዐድርጎ የሚመሰረት ሀረግ ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ ይባላል፡፡

ምሳሌ

- በጣም ቶሎ
- እንደ አባቱ ፈጥኖ
- ጠዋት ትናንት

4. መስተዋድዳዊ ሐረግ

መስተዋድድ ከሌሎች የቃል ክፍሎች ጋር ሲመጣ መስተዋድዳዊ

ሀረግ ይመሰርታል፡፡

ምሳሌ፡-


- ወደ ገበያ
- ከ ተማሪ ጋር
- ስለ ሀገር
- መጽሐፉ ላይ


ማሳሰቢያ፡- በሐረጋት ቅንጅት ከመስተዋድዳዊ ሐረግ በስተቀር ቀኝ መሪ( መሪያቸው በስተቀኝ የሆነ ) ሲሆኑ መስተዋድዳዊ ሐረግ ግን መሪውን በግራና በቀኝ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

ተግባር

1. የሚከተሉትን በ ክብ ‹‹ ሀ ›› ስር የተዘረዘሩ ቃላት በ ክብ ‹‹ ለ ›› ስር ካሉት ቃላት ጋር በማጣመር ሀረጎችን መስርቱ፡፡

‹‹ሀ›› ‹‹ለ››



1. ስማዊ ሀረግ 3. ቅጽላዊ ሐረግ 5. መስተዋድዳዊ ሐረግ

------------------------- ------------------------- -------------------------

------------------------- ------------------------- -------------------------

2. ግሳዊ ሀረግ 4. ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ

---------------------- ----------------------

---------------------- ----------------------

2. ቀጥሎ ሐረግን መሰረት አድርገው ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አራት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መርጣችሁ በጽሁፍ መልሱ።

1.ልጁ ግድግዳ ላይ ይፅፋል። የተሰመረበት የሐረግ አይነት -----------ነው።

ሀ. መስተዋድዳዊ ሐረግ ለ. ስማዊ ሐረግ

ሐ.ቅጽላዊ ሐረግ መ. ግሳዊበሐረግ

2.ለእህቱ ውድ ሽቶ ገዛላት በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ሐረግ ምን አይነት ሐረግ ነው?

ሀ. ግሳዊ ሐረግ ሐ.ቅጽላዊ ሐረግ

ለ. ስማዊ ሐረግ መ.ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ

3.የሴና መምጣት አስገረመኝ። በሚል ዐረፍተነገር ውስጥ ያለው ግሳዊ ሐረግ የትኛው ነው?

ሀ.የሴና መምጣት ለ. አስገረመኝ

ሐ. መምጣት መ. መምጣት አስገረመኝ

4. ከሚከተሉት ሐረጎች መካካል ስማዊ ሐረግ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. እጅግ መልካም ለ. እናት ሀገር

ሐ. ህይወቱ አለፈ መ. ዛሬ ገና

5. ያሳደገው ውሻ ስለሞተበት ክፉኛ አዝኗል። በዘህ ዐረፍተ ነገር ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ የሚሆነው ----- ነው።

ሀ. ክፉኛ ለ ክፉኛ አዘነ

ሐ. ስለሞተበት ክፉኛ መ ያሳደገው ውሻ

6. ስምን መሪ አድርጎ የሚዋቀር የሐረግ አይነት ምን ይባላል?

ሀ.ስማዊ ሐረግ ለ. ግሳዊ ሐረግ

ሐ. መስተዋድዳዊ ሐረግ መ ቅጽላዊ ሐረግ

7. የመስተዋድዳዊ ሐረግ መዋቅር ከሌሎቹ የሚለየው በምንድን ነው?

ሀ. የግስ ገላጭ ሆኖ መግባቱ

ለ የስም አጎላማሽ በመኖኑ

ሐ. መሪው በግራም በቀኝም መቀመጥ መቻሉ

መ ቀኝ መሪ በመሆኑ

8. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ግሳዊሐረግ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. እየሮጠ መጣ ለ. ከምሳ በኋላ

ሐ ወድቆ ተሰበረ መ. በአቋማቸው ጸኑ

3. የሐረግ አደረጃጀት መመሪያን ተከትላችሁ ለእያንዳንዳቸው ሁለት፣ሁለት ምሳሌዎችን ጽፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል ስድስት ስነ ጽሑፍ

### ተግባር

1. የሚከተሉትን ጅምር ልቦለዳዊ ገለፃዎች ካነበባችሁ በኋላ በቡድን ተወያዩና መቼቱን በጽሑፍ ግለፁ፡፡

ምሳሌ፡ ዝናቡ ሳያቋርጥ ይዘንባል፡፡ አልፎ አልፎ እዚህም እዚያም ከሚታዩት ጎጆ ቤቶች አናት ላይ ጭስ እየተጥመለመለ ሲወጣ ይታያል፡፡ ከቤቶቹ ማዶ፣ እተራራው ግርጌ ያለችው ጀንበር "ጠለኩ፣ ጠለኩ" በሚል ማስፈራሪያ አየነት በግማሽ ትታያለች፡፡እረኞች ከብቶቻቸውን ከአረንጓዴው የመስክ ግጦሽ አውለው እያፏጩ ወደ ቤት ይነዷቸዋል፡፡ …

መቼት

ቦታው - ገጠር አካባቢ

ወቅቱ - ክረምት( ዝናባማ ወቅት)

ሰአቱ- አመሻሽ ላይ (በግምት 12 ሰአት አካባቢ)

የመልክአ ምድሩ ሁኔታ - ለምለም ( አረንጓዴ መስክ) ወዘተ..

1. የዘንድሮ የበልግ ዝናብ እንደአምናው ቀጠሮ ጠብቆ በሰአቱ ባለመድረሱ የሱጼ ሜዳዎች፣ ተራሮችና ሸንተረሮች አንበጣ እንደመታው መራቆት ጀምሯል፡፡
2. የብርጭቆና የጠርሙስ ቻቻታ፣ የጡሩምባ ኡኡታ፣ የህዝቡ

ጋጋታና ግፊያ፣ ከመጠጥ ሽታና ጉም ከመሰለው የሲጃራ ጢስ ጋራ ተደባልቀው የገነት ሆቴልን የዳንስ አዳራሽ ምድራዊ ገሀነም አስመስለውታል፡፡

3. ከቤት ውስጥ ከሚነድው ፋኖስ እየተነነ የሚመጣው ጋዝ ከቀዝቃዛው የምሽት አየር ጋር እየተዋሀደ አንዳንዴ መጥቶ አፍንጫውን ይወጋዋል፡፡ ስለለመደው አያስጨንቀውም፡፡ እንደፈርጥ በሚንቦገቦጉ ከዋክብት የታጀበች ብርማ ግማሽ ጨረቃ በቀዝቃዛው ብርሀኗ ሜዳውን፣ ቤቱን፣ ዛፉንና ቁጥቋጦውን ጥቁር ግራጫ ቀለም እየቀባች ታዥጎረጉረዋለች፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ሳይንስና ቴክኖሎጂ

### የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች�: -

- ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተኮር ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- መምህሩ የሚያነቡላችሁን አጭር ግጥም በጥሞና አዳምጣችሁ በድህረ ማዳመጥ የቀረቡ የቃልና የፅሑፍ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የውይይትን አቀራረብ ስርአትን በመጠበቅ በተሰጧችሁ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትወያያላችሁ፡፡
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ ስዕሎችን በመመልከት በሰዎች ላይ የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለጓደኞቻችሁ ታብብራራላችሁ፡፡
- የክርክር አቀራረብ ደንቦችን ተከትላችሁ ክርክር ታደርጋላችሁ፡፡
- የቀረበውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ ለድህረ ምንባብ ጥያቄዎች የቃልና የፅሁፍ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- የስርዓተ ነጥብ አገልግሎቶችን በመረዳት በፅሑፍ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- ከተለያዩ ቃላት ሌሎች ቃላትን ትመሰርታላችሁ፡፡
- ነጠላ ቃላትን በማቀናጀት ድርብ ቃላትን መመስረት ትችላላችሁ፡፡

- ነጠላና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ለይታችሁ ትፅፋላችሁ
- ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ትሰጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

1. ስልጣኔ ከሳይንስ ጋር ያለውን ቁርኝት እንዴት ታዩታላችሁ ?
2. የሳይንስና ቴክኖሎክኖሎጂ ተሞክሮዎችን ካደጉ ሀገራት በውስት( በኩረጃ መውሰድ) ያለውን ጥቅምና ጉዳት ተናገሩ፡፡

3. ሰዎች ዕውቀታቸውን ቢያጋሯችሁ ይሻላችኋል፤ ወይስ ብርና አላቂ ቁሳቁሶች ቢረዷችሁ? ለምን? ምክንያታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. ቀጥሎ ያዳመጣችሁትን አጭር ግጥም መሰረት አድርጋችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡
   ሀ. ገጣሚው የጠቀሳቸው ሀገራት የሚወክሉት ማንን ነው?
   ለ. ግጥሙ እስያን፡ አፍሪካንና ቬትናምን የጠቀሰው ለምን ይመስለችኋል?
   ሐ. ገጣሚው “በአፍንጫዬ ይውጣ አልፈልግም ብሩን” ያለበት ምክንያት ምን ፈልጎ ነው?
   መ. በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰው የፉጂ ተራራ የማን ንብረት ነው?
   ሠ. ግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድ ነው?

2. ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች ካዳመጣችሁት ግጥም የወጡ ናቸው፤ ቃሎቹ ግጥሙ ውስጥ በገቡበት አውድ የሚሰጡትን ፍች ፅፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ሀ.ተማፀንኩሽ

ለ. ምትነኸው

ሐ.በአፍንጫዬ ይውጣ

መ. ምስጢረ ጥበብ

ረ. ምን ልፍጠር

ሠ. አብዳር፣ አውጋር

3. ከዚህ በታች መምህሩ/ሯ ካነበቡላችሁ ግጥም ውስጥ የተውጣጡ ጅምር ሐረጎችን እና ስንኞችን ባዳመጣችሁት መሰረት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. አሜሪካም አምጪ ምንድነው ምስጢሩ፣

-----------------------------------------፡፡

ለ. -------------------- ለእስያ የምትነገርው፣

---------------------- ብሩን ብሩን አገኘሽው?

ሐ .---------------------- ትንሽ ሀገር፣

ለዓለም የከፈትሽዉ የእንዱስትሪን በር፡፡

መ. ጃፓንም ንገሪኝ የሩቅ ምስራቅ ሀገር፣

-------------------------ምንላድርግ ምን ልፍጠር?

ሠ. ንገሪኝ አዉሮፓ በእግዜር ተማፀንኩሽ፣

አንድ ሳትደብቂ -------------------------?

ረ. አስጠንቁለሽ ነዉ ወይ ----------------------፣

---------------------- ለፉጂ ተራራ፡፡

## ክፍል ሁለት መናገር

1. የሚከተሉትን ምስሎች ተመልክታችሁ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቅምና ጉዳት አንፃር በቡድን ተወያይታችሁ ሀሳባችሁን በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች አጋሩ።









2. በምዕራፍ ሁለት ስለውይይት የቀረበውን ማስታወሻ በማስታወስ ከታች በተሰጧችሁ መነሻ ሐሳቦች ላይ ውይይት አድርጉ።

ሀ. ማህበራዊ ድረ ገፆች ስንጠቀም ከጥፋት ይልቅ ለሀገር ልማት ለማዋል ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

ለ. ግብርናን በተክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ ከአርሶ አደሩ ጀምሮ እስከ ሀገር ድረስ ያለው ፋይዳ ምንድነው?

ማስታወሻ

ክርክር

ክርክር ሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች አከራካሪ በሆነ ጉዳይ ላይ ተመስርተው የየበኩላቸውን እምነትና አስተያየት ይዘው በመደገፍና በመቃወም አሸናፊ ሆነው ለመገኘት የሚያካሂዱት ስርዓት ያለው የሙግት ሂደት ነው።

የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ

ክርክር ስታቀርቡ መከተል የሚገባችሁ የዝግጅትና አቀራረብ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

1. በመረጣችሁት/ በተሰጣችሁ / ርዕስ ላይ ለመዘጋጀት

_ ርዕሱን በሚመለከት ከአዋቂ ሰዎች/ባለሙያዎች/ እና ከልዩ ልዩ መጽሐፍት  ጠቃሚ ነጥቦችን መሰብሰብ፤

_ ነጥቦቹ በቅደም ተከተል አስተካክሎ መጻፍ፤

_ ክርክሩን ለአድማጭ ከማቅረብ በፊት በቂ ልምምድ ማድረግ፤ ክርክሩን ስታቀርቡ ደግሞ የመከራከሪያ ርዕሱን ለአድማጭ ማስተዋወቅ፤

_ ክርክሩን ስታቀርቡ ረጋ ባለ መንፈስ ሳትፈሩ መቅረብና በመረጃ የተደገፈ ሀሳብ  ማቅረብ፤

_ ከተቃዋሚ ወገን የሚሠጠውን ሀሳብ በትክክል እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝና የቀረበውን ሀሳብ የሚያፈርስ ሀሳብ ማዘጋጀት፤

_ ለክርክር የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ማክበር፤ ሲጠናቀቅ አድማጮችን በትዕግስትና በሥነ ሥርዓት ስላዳመጡ ማመስገን ናቸው፡፡

*በአጠቃላይ ክርክር ለማካሄድ የሚያስፈልጉ፦

- ሊቀ መንበር/ ሰብሳቢ
- ዳኞች
- ተከራካሪዎች
- ታዳሚዎች
- የመከራከሪያ ርዕሶች ወዘተ ናቸው፡፡

1. ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን የመከራከሪያ ነጥብ በማድረግ በቡድን ተከፍላችሁ ክርክር አድርጉ/ ተከራከሩ፡፡

ምሳሌ፡-

- ተማሪዎች የሞባይል ስልክ ትምህርት ቤት ውስጥ መጠቀም የለባቸውም ወይስ አለባቸው?
- ሁሉም የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጠቃሚ ናቸው ወይስ አይደሉም?

## ክፍል ሶስት ማንበብ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ተግባር

1. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በሳይንስ እና በቴክኖሎጂ መካከል ልዩነቶች አሉ ብላችሁ

ታስባላችሁ? ካሉ ምንምን ናቸው?

3. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች አለማችን ላይ ያሳደሩትን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ዘርዝሩ።

ምንባብ

ሣይንስና ቴክኖሎጂ

የሰው ልጅ ስለተፈጥሮ ምንነት ለማወቅ ያደረገው የዘመናት ትግል ለበለጠ ዕውቀት ራሱን እያበቃ ካለንበት ዘመን ላይ ደርሷል። ዕውቀት በሣይንሳዊ ዘዴ በምልከታ ወይም በሙከራ ተለክቶ የሚገኝ ነው። በምልከታ ወይም በሙከራ የተገኘ ዕውቀት ይበልጥ ተደራጊ እንዲሆን ለማስቻል የቴክኖሎጂ ፈጠራ ዕውን ሆኗል። ሣይንስና ቴክኖሎጂ የማይነጣጠሉ የነባሩ ዓለም መገንዘቢያና የተጠቃሚነት መግለጫ መሣሪያዎች ናቸው። ሣይንስና ቴክኖሎጂ ያላቸውን ግንኙነት ከማየታችን በፊት በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ትርጉማቸውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል።

ሣይንስ ስልታዊ አደረጃጀት ያለው አጽናፈ ዓለምን መፈተሽ፣ ማብራሪያና ግምቶችን በመፍጠር፣ማደራጀትና በሣይንሳዊ ዘዴ ሙከራና ምርምር ተመስርቶ ዕውቀት ማዳበር የሚያስችል የተደራጀ ሥርዓት ነው።

ሣይንስ የተፈጥሮ ክስተቶችን ለማስረዳት ምልከታና ሙከራ በማካሄድ የዳበረ ዕውቀትን ያመለክታል። ሣይንስ ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት ዕውቀት የሚያተርፉበት የተደራጀ ሥርዓት ነው። የሳይንስ መስኮች በአራት ዋና ዋና ዘርፎች የተመደቡ ናቸው። እነዚህም፡-

1.የተፈጥሮ ሣይንስ ቁሳዊ ዓለምን ወይም አጠቃላይ ስለ ስነ ህይወት የሚያጠና ነው

2. ማሕበራዊ ሣይንስ ስለሰዎችና ስለማኅበራዊ ጉዳዮች የሚያጠና ዘርፍ ነው፡፡

3. መደበኛ ሳይንስ መደበኛ ሥርዐትን ተከትሎ የሚያጠና እንደ ሎጂክ፣ሂሣብ፣ ስታቲስቲክስ፣ ኮምፒዩውተር ሳይንስ፣ ኢንፎርሜሽን ቲዮሪና ኢኮኖሚክስ የመሳሰሉትን የሚመለከት የሣይንስ ዘርፍ ነው

4. ተግባራዊ ሣይንስ ነባር ሣይንሳዊ ዕውቀትን በመጠቀም እንደ ቴክኖሎጂና ፈጠራዎች የመሳሰሉትን ተግባራዊ አፕሊኬሽኖችን በመጠቀም ሌሎች ሣይንሶችን ማልማት የሚያስችል የሣይንስ ዘርፍ (ኢንጂነሪግና ሜዲሲን) ነው፡፡

ቴክኖሎጂ ማለት፡- የቴክኒክ፣የክህሎትና የአሠራር ዘዴዎች ስብስብ የሆኑ፤ ምርቶችን፣ አገልግሎቶችን፣ የሣይንሳዊ ምርምሮችን ዓላማ ማስፈጸም የሚያስችል መሣሪያ ነው፣ የዕውቀት ቴክኒክና ሂደት ሲሆን ማሽኖችን፣ኮምፒዩተሮችን፣መሣሪያዎችን፣በፋብሪካ ውስጥ ያሉ መሣሪያዎችን፣ ሲስተሞችንና ቴክኒካዊ ዘዴዎችን እንዲሁም በአጠቃላይ ወይም በተወሰኑ አካባቢዎች ሊተገበር የሚችል (የግንባታ ቴክኖሎጂ፣ የህክምና ቴክኖሎጂ ወዘተ) ተግባሮችን ያካትታል፣ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሃብቶችን ወደ ቀላል መሣሪያዎች ለውጦ መጠቀም ከጀመረበት ጊዜ በተለይም የእሳት መፈጠር፣ምግብን ድንጋይ ላይ አብስሎ መጠቀም፣ለመጓጓዣ ጋሪ በመጠቀሙ በፍጥነት ተጉዞ አካባቢውን መቆጣጠር በመቻሉ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ ቀስ በቀስ የህትመት መሣሪያዎች ስልክ፣ ኢንተርኔት መፈጠር በቴክኖሎጅ የመጠቀም ፍላጎትና ዕድገት እየጨመረ መጣ፡፡ ቴክኖሎጂ የሚለው ቃል ካለፉት 200 ዓመታት ጀምሮ የመጣ ነው፡፡ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ቴክኖሎጂ የሚለው ቃል የማይታወቅና

እንዲያውም "ጠቃሚ ጥበባት" በመባል ይታወቅ ነበር፡፡

ቴክኖሎጂ የሚለው ቃል በ20ኛው ክፍለ ዘመን ከሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ጋር የተፈጠረ ነው፡፡ በ1930 ዎቹ ቴክኖሎጂ የኢንዱስትሪ ጥበባትን ማጥናት ብቻ ሳይሆን እራሱ የኢንዱስትሪ ጥበባት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ቴክኖሎጂ ባህልን የለወጠ ተግባር ነው ተብሎ ሊታይ ይችላል፡፡ ቴክኖሎጂ ሂሳብ፣ሣይንስና ጥበብን መሠረት አድርጎ የህይወትን ጠቀሜታ ያረጋገጠ ነው፡፡ ለአብነትም መገናኛ ቴክኖሎጂ የግንኙነት እንቅፋቶችን በማስወገድ የሰዎችን መቀራረብ በኢንተርኔትና ኮምፒዩተር ላይ ተመስርቶ ለአዲስ የሳይበር ባህል መፈጠር ግኝት ነው፡፡

ቴክኖሎጂ አብዛኛውን ጊዜ በመተካካት ጥቅም ላይ ይውላሉ፤ ነገር ግን የሣይንስ ግብ ዕውቀት ማሳደድ ሲሆን የቴክኖሎጂ ግብ ደግሞ ችግሮችን ለመፍታት ምርት መፍጠርና ለሰው ልጆች ህይወት መሻሻል ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በአጭር አነጋገር ቴክኖሎጂ የሣይንስ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ነው፡፡

ሣይንስ በምልከታ ወይም በሙከራ የተደረሰበት የሰው ልጅ ዕውቀት ነው፡፡ መረጃ ውስብስብ እየሆነ መምጣት ምርምሮች በተሻሉ መሣሪያዎችና ተመራማሪዎች በቡድን ሥራ እንዲመሠረት አድርጎታል፡፡ ቴክኖሎጂ የቴክኒክና የክህሎት ጥምረት ላይ ተመስርቶ ሣይንሳዊ ምርምሮችን ማግኛ መሣሪያ በመሆኑ ምክንያታዊ ንድፈ ሃሳብን ፈልጎ በማግኘት የተገኘውን ዕውቀት በቴክኖሎጂ ወደ ተግባር መለወጥ ጊዜው የጠየቀው ግኝት መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡

በመሆኑም ሣይንስና ቴክኖሎጂን አጣምሮ መጠቀም ለሰው ልጅ ልማትና ዕድገት ወሳኝ መሣሪያዎች በመሆናቸው ሁለቱንም

ማወቅ፣መተግበርና መጠቀም ብሎም የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተደራሽነቱን ማስፋትና የህዝብን ግንዛቤ የማሻሻል ነገር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

(ምንጭ፡- አዲስ አበባ ቴክነኖሎጂ፣ "ኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን (2007) ድረገጽ ላይ፣ ለንባብ ትምህርት ተሻሽሎ የቀረበ)

## ድህረ ንባብ ተግባር

1. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

    1. ሳይንስ በምልከታ ወይም በሙከራ የተደረሰበት የሰው ልጅ ዕውቀት ነው ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
    2. ቴክኖሎጂ የሳይንስ ማስፈፀሚያ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
    3. በምንባቡ መሰረት የሳይንስ ዘርፎች ስንት ናቸው? ዘርዝሯቸው፡፡
    4. በምንባቡ መሰረት ተክኖሎጂ ማለት ምን ማለት ነው?
    5. እንደ ምንባቡ ገለፃ የሰው ልጅ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ እንዲያውል ያደረገው ምክንያት ምንድነው?
    6. በምንባቡ መሰረት ቴክኖሎጂ ባህልን የቀየረው እንዴት ነው?
    7. ቴክኖሎጂ የሚለው ቃል ከመታወቁ በፊት መጠሪያው ምን ነበር?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት በፅሁፍ መልስ ስጡ፡፡

1. ቴክኖሎጂ ባህልን የለወጠ ተግባር ነው ተብሎ ሊታሰብ ይችላል፡፡
2. የሰው ልጅ ስለተፈጥሮ ምንነት ለማወቅ ያደረገው የዘመን ትግል ራሱን እንዲያበቃ አላገዘውም፡፡
3. ቴክኖሎጂ የሚለው ቃል በ20ኛው ክፍለ ዘመን ከሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ጋር የተፈጠረ ነው፡፡
4. የምንባቡ ማጠቃለያ ሐሳብ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በጥምረት የመጠቀም ግንዛቤ ህብረተሰቡ ላይ ስለመፍጠር አስፈላጊነት ነው፡፡

3. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ክፍት ቦታዎችን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

1. ---------------------- የአሠራር ዘዴዎች ስብስብ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማስፈፀም የሚውል መሳሪያ ነው፡፡

2. ---------------------------------- ሲሆን የቴክኖሎጂ ግብ ደግሞ ችግሮችን ለመፍታት ምርት መፍጠርና ለሰው ልጆች ህይወት መሻሻል ላይ ያተኮረ ነው፡፡

3. ---------------------------- ቁሳዊ ዓለምን ወይም አጠቃላይ ስለ ስነ ህይወት የሚያጠና ሳይንስ ነው፡፡

4. ---------------------------- ነባር ሣይንሳዊ ዕውቀትን የሚጠቀም ሌሎች ሣይንሶችን ማልማት የሚያስችል የሣይንስ ዘርፍ ነው፡፡

5. የተፈጥሮ ክስተቶችን ለማስረዳት ምልከታና ሙከራ በማካሄድ የዳበረ ዕውቀትን የሚያመለክት የተደራጀ ስርአት ------------------------ ይባላል ።

6. ----------------------------- እንደ ሎጂክ፣ሂሣብ፣ ስታቲስቲክስ፣ ኮምፒዩውተር ሳይንስ፣ ኢኮኖሚክስና የመሳሰሉትን ያካተተ የሣይንስ ዘርፍ ነው፡፡

7. ቴክኖሎጂ የሚለው ቃል ------------------------ ጀምሮ የመጣ ነው፡፡

4. የሚከተሉትን በ ‹‹ሀ›› ስር የተዘረዘሩ ቃላት በምንባቡ የገቡበትን ትርጉም በ ምድብ ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት በመውሰድ አዛምዱ

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
| --- | --- |
| 1. ዕድገት | ሀ. ለመፍታት አዳጋች የሆነ ነገር |
| 2. መሣሪያ | ለ. ችሎታ |
| 3. ማወቅ | ሐ. መተግበሪያ ወይም መገልገያ ቁስ |
| 4. ክህሎት | መ.ንድፈ ሐሳብ |
| 5. ውስብስብ | ሠ. አገልግሎት ወይም ፋይዳ |
| 6. ቲዮሪ | ረ. መረዳት ወይም መገንዘብ |
| 7. ጥቅም | ሰ. ለውጥ ወይም መሻሻል |

## ክፍል አራት፡ መፃፍ

ማስታወሻ

ስርዓተ ነጥቦችና አገልግሎታቸው

ስርዓተ ነጥቦች በፅሁፍ ውስጥ ማስተላለፍ የተፈለገውን ሃሳብ በትክክል መረዳት የሚያስችሉ የጋራ መግባቢያ ምልክቶች ናቸው፡፡

በቃል ንግግር ጊዜ ድምፃችንን ከፍ ዝቅ በማድረግና እጃችንን በማንቀሳቀስ የአነጋገር ሁኔታችንንና ስሜታችንን መግለጽ እንችላለን:: በጽሁፍ ጊዜ እነዚህን ስሜቶችና የአነጋገር ስልቶች የሚገልፁ ነገሮች የሉም:: በመሆኑም የሚተላለፈው ሃሳብ ለአንባቢ ይበልጥ ግልፅ እንዲሆን በስርዓተ ነጥቦች እየታገዙ መጻፍ ጠቃሚ ነው::

በአብዛኛው በአገልግሎት ላይ ካሉት ስርዓተ ነጥቦች ውስጥ ለዚህ ክፍል ደረጃ የሚመጥኑትን ሁለት ስርዓተ ነጥቦችና ተግባራቸውን እንመልከት::

ምሳሌ:- ሰውዬው ሌሊትና ቀን ይለፋል፤ ሁሌም ይማስናል፤ በጣም

ለ. ቅንፍ ( )

1. በዐረፍተነገር ውስጥ የሚገቡ ተጨማሪ የቃላት ፍቺንና መረጃዎችን ለማመልከት ይገባል::

ምሳሌ:- ቢጋር ( አስተዋጽዖ ) ድርሰት ለመጻፍ ይረዳል::

ሠ.ትምህርተ ስላቅ (¡)

በጽሑፍ ውስጥ ከምፀት፣ከአሽሙርና ከማሾፍ ጋር የተዛመዱ አነጋገሮችና ተዛማጅ ስሜቶች መኖራቸውን ለማመልከት ይገባል::

ምሳሌ:- 1. ስጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ ¡

2.ደራርቱም አምሮብሽ ሞተሻል ¡

3. ወጡን ዝቀህ ዝቀህ ብላ የድስቱም ይገለበጥልሃል ¡

## ተግባር

1. ከዚህ በታች ለቀረቡት ሐረጎችና አረፍተ ነገሮች ትክክለኛውን ስርዓተ ነጥብ በማስገባት ሀሳቡን አሟሉ።የኮሮና ወረርሺኝ በሽታ ዘር______ቀለም_______ሀይማኖት______እድሜ እና ፆታ የማይለይ አደገኛ በሽታ ነው።

1. አቤት ስታምር ________ ሽኮኮ አይደል እንዴ የምትመስለው________
2. ለሀገራችን ሰላምና እድገት ሁላችንም ታጥቀን መነሳት አለብን______
3. አንጋሳ በጠዋት ይነሳል______ቁርሱን ይበላል______ደብተሩን ይይዛል______ከዚያም እየሮጠ ወደ ት/ቤት ይሄዳል።
4. አላርፍ ያለች ጣት_______ጠንቁላ ትወጣለች
5. በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ 110,000000 ከ አንድ መቶ አስር ሚሊዮን በላይ እንደሆነ ይገመታል።
6. የሀገራችን ቋንቋዎች በአራት ዋናዋና ቤተሰቦች ስር ይመደባሉ እነዚህም______ ሴማዊ፣ኩሻዊ፣ኦሟዊና አባይ ሰሀራዊ ይባላሉ።

2. ከታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ሊያሟሉ ይችላሉ ተብለው ከቀረቡት አማራጭ ስርዓተ ነጥቦች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. “.ድንቄም ጉብዝና______“ እያለች በማላገጥ አይነት ስለሰነፉ ተማሪ ስትናገር ነበር።

   ሀ.! ለ. ¡ ሐ. ፣
   
   መ. ፧

2. ገና በጠዋቱ ድካም ተሰምቶኛል______ሆዴም ታውኳል።

   ሀ. ፧ ለ. ( ) ሐ. ፡- መ. ¡

3. ከገበያ የገዛሁትን ሽንኩርት______ ድንችና ቃሪያ ለእናቴ ሰጠኋት።

   ሀ. ፧ ለ. ! ሐ. … መ ፣

4. ኡኡ______ ወይኔ______ የሰውያለህ______ ድረሱልኝ______

   ሀ. ! ለ. ¡ ሐ. ፦ መ. …

5. ሀኪሞቹ የታመመውን ሰውዬ የእንቅልፍ መርፌ ማደንዘዣ ወጉት።

   ሀ. ፦ ለ. ፧ ሐ. ( ) መ. ፣

ለምሳሌ______ ገብስ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ በአካባቢያችን ባህላዊ መጠጦችን ለማዘጋጀት ያገለግላሉ።

   ሀ. ( ) ለ. ፦ ሐ. ፣ መ. ፧

6. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት።

   ሀ. … ለ. ! ሐ. ¡ መ. ፦

7. የአስተዳዳሪው መኖሪያ ቤት ፈረስ ያስጋልባል ______

   ሀ. ፧ ለ. ! ሐ. መ. ¡

# ክፍል አምስት፡ ቃላት

## ከቃላት ሌሎች ቃላትን መመስረት

### ተግባር

1.ቀጥሎ የተሰጡትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ከቀኝ ወደግራ በማንበብ ሌሎች ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፦ ‘ዶማ’ የሚለው ቃል ከቀኝ ወደግራ ሲፃፍ ‘ማዶ’ የሚል ቃል ይሰጣል፡፡

ሀ. ዳነ

ለ. ጠበቀ

ሐ. ፈለጠ

መ. ዳረ

ሠ. ሰባ

ረ. ለጋ

ሰ. ደራ

ሸ. ገለባ

ቀ. ልብ

በ. ራሰ

ተ. ማለ

ቸ. ታማ

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሠረት ሌሎች ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- መስመር ከሚለው ቃል መመርመር፣ መርመስመስ፣ ስር … የመሳሰሉት ቃላት ሊመሰረቱ ይችላሉ፡፡

1. መነጠረ፡-
2. ሰባበረ፡-
3. ቀራረበ፡-
4. ተላለቀ፡-
5. ፈራረሰ፡-
6. ደረሰ፡-
7. ገመጠ፡-

ማስታወሻ

ድርብ ቃላት

ድርብ ቃል ማለት ሁለት የተለያየ ፍቺ ያላቸው ቃላት አንድ ላይ ተጣምረው ሁለት የነበሩት እንደ አንድ ቃል እና አዲስ የተለየ ፍቺ የሚሰጡበት ሂደት ነው፡፡

ምሳሌ፡- አየር - ወለድ = አየርወለድ

ቤተ - መንግስት = ቤተመንግስት

ፍርድ - ቤት =ፍርድቤት

## ተግባር

1. ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት አምስት ድርብ ቃላትን በመመስረት ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________
4. ______________________
5. ______________________
6. ______________________

## ክፍል አምሰት ስዋስው ተግባር

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ።

1.ከሚከተሉት መካከል አንድ ዐረፍተነገር የግድ መያዝ ያለበት የቱ ነው?

ሀ. ገላጭና ግስ  ለ. ባለቤትና የባለቤት ገላጭ
ሐ. ባለቤትና ግስ  መ. ግስና የግስ ገላጭ

1. በውስጡ ሁለትና ከሁለት በላይ ግሶችን የሚይዘው ዓረፍተነገር የቱ ነው?

ሀ. ተራ ዓረፍተነገር  ለ. ውስብስብ ዓረፍተነገር

ሐ. ተራ ውስብስብ ዓረፍተነገር  መ. ውስብስብ ተራዓረፍተነገር

1. ከሚከተሉት ነጠላ ዐ/ነገር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በጣም ታታሪው ተማሪ ከትምህርት ቤቱ ትልቁን ሽልማት ተሸለመ፡፡

ለ. ራሱን የወደደ ሌሎችን ይወዳል፡፡

ሐ. ሕይወትን እንድታሸነፍ መታገል ያስፈልጋል፡፡

መ. ከቤት ሲመጣ ይህንን ስጪዉ፡፡

3. ከሚከተሉት መካከል ነጠላ ዓረፍተነገር የቱ ነው?

ሀ. ከጠናህ ታልፋለህ

ለ. አስተዋዩና ጎበዙ ተማሪ መጽሐፍ ተሸለመ፡፡

ሐ. ብዙ ያነበበ ብዙ ዕውቀት ያገኛል፡፡

መ. ምሳውን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

4. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ለዉስብስብ ዐረፍተነገር ምሳሌ ነው፡፡የቱ?

ሀ. ለፈተና አዳራሹ ዉስጥ በርካታ ተፈታኞች አሉ

ለ. በፈተና አዳራሹ ውስጥ ያሉትን ተፈታኞች ስለ በዙ ክፍሉ ተጨናንቋል፡፡

ሐ. በፈተና አዳራሹ ውስጥ ተፈታኞች በረድፍ በረድፍ ተቀምጠዋል፡፡

መ. የመፈተኛ አዳራሹ በተፈታኞች ተጨናንቋል፡፡

## ክፍል ሰባት፡- ስነ ፅሑፍ

### ፈሊጣዊ አነጋገር

ፈሊጣዊ አነጋገሮች ሀሳብን በቀጥታ ለመግለጽ ወይም በመደበኛ አገላለጽ ከማስተላለፍ በተለየና ትኩረት በሚስብ መልኩ ክብደትና ውበት ሰጥተን የምናስተላልፍበት ዋነኛ ስልት ነው፡፡

ስለዚህ በንግግራችን ውስጥ ፈሊጣዊ አነጋገርን ጣልጣል ማድረግ ሀሳባችን ውበትና ለዛ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

ፈሊጣዊ አነጋገሮች በአብዛኛው ከሁለት ቃላት ጥምረት የሚገኙ ቢሆኑም ከአንዳንድ ነጠላ ቃላት የተሰሩ ፈሊጦች አይጠፉም፡፡
ምሳሌ፡-

ጅብ - ሆዳም፣ የማይጠግብ፣ የማይረካ

እባብ- ተንኮለኛ

ውሻ - የሚልከሰከስ የሚለማመጥ

ቆቅ- ብልጥ ወዘተ..

ከጥምር ቃላት የሚመሰረቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች የሁለቱ ቃላት ፍቺ ድምር አይደለም፣ ይልቁንስ ሌላ አዲስ ፍች ወይም እሳቤ ይሰጠናል፡፡

ለምሳሌ ሁለት ምላስ ብንል ትርጉሙ ሁለት ምላሶች አሉት ማለት ሳይሆን ውሸታም ማለት ነው፡፡

ፈሊጣዊ አነጋገሮች
ትርጉማቸው

1. ሀሞተ ቢስ — ፈሪ
2. ሁለት ልብ — ወላዋይ
3. ሆደ መጋዝ — ክፉ ሰው፣ መሰሪ
4. ልባም — አስተዋይ
5. መላ ቢስ — ግራ የገባው
6. መስከረም ጠባ — አዲስ አመት ገባ
7. መሸጦ — በጣም ጥቁር
8. ንፉግ — ስስታም ገብጋባ (ያለውን የማያከፍል)
9. ነፍሰ ጡር — እርጉዝ
10. ቀኝ እጅ — መልካም ወዳጅ ወዘተ…

1. ከዚህ ቀጥሎ በምድብ ‹‹ሀ››ስር ለቀረቡት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ትርጉማቸውን በምድብ ‹‹ለ›› ካሉት መርጣችሁ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አመድ አፋሽ | ሀ. አዳላ |
| 2. በለስ ቀናው | ለ. መሰሪ |
| 3. የህልም ሩጫ | ሐ. ትዕቢተኛ |
| 4. ሰርግና ምላሽ | መ. አርቆ አሳቢ |
| 5. የውሻ አፍንጫ የማይመለስለት | ሠ. ውለታው |
| 6. ታጥቦ ጭቃ | ረ. ረዥም |
| 7. ልበ ተራራ | ሰ. ተሳካለት |
| 8. የጭቃ እሾህ | ሸ የማይሻሻል |
| 9. ብቅል አውራጅ | ቀ. ከንቱ ሀሳብ |
| 10.ሰው ለየ | በ. ታላቅ ደስታ |

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት የሚያስረዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሞተ፡- አረፈ፣ ፍግም አለ ፣ህይወቱን አጣ…

1. አስተዋይ ሆነ
2. ሞተ
3. ተደሰተ
4. ታታሪ
5. ጨካኝ
6. ቶሎ የሚድን ቁስል
7. ያልተማረ
8. እድል የሌለው
9. ቆንጆ
10. ስነ ምግባር የጎደለው

3. ቀጥሎ ለቀረቡት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆኗቸውን ቃላትና ሀረጋት ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. አዕምሮው ተመለሰ
2. ሹክ አለ
3. ቤቱ ፈረሰ
4. በዋል ፈሰስ
5. ስመ ጥር
6. ወፈፌ
7. ሰኔና ሰኞ

# ምዕራፍ አምስት
## የጊዜ አጠቃቀም

### የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስለጊዜ አጠቃቀም የቀረበውን ምንባብ አዳምጣችሁ ለጥያቄዎች የቃልና የፅሑፍ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- ከትምህርት መልስ ያላችሁ የሰአት አጠቃቀም ምን እንደሚመስል በቅደም ተከትል ለጓደኞቻችሁ ታብራራላችሁ፡፡
- የጊዜ አጠቃቀምን በእቅድ መምራት ያለውን ጠቀሜታ በቡድን ተወያይታችሁ ሪፖርት ታቀርባላችሁ፡፡
- የጭውውትን መሰረታዊ ስርአት ተከትላችሁ በተሰጣችሁ ርዕሰ ጉዳይ ጭውውት ታቀርባላችሁ፡፡
- ሞኙ ተላሌ በሚል ርዕስ የቀረበውን የግጥም ምንባብ አንብባችሁ ጥያቄዎችን በአግባቡ ትመልሳላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፈቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለአመዛዛኝ ድርሰት ማስፋፊያ ሊሆኑ የሚችሉ መንደርደሪያ ሀሳቦችን ለይታችሁ ታሳያላችሁ፡፡
- የቀረበላችሁ ማስታወሻና ምሳሌ ላይ ተመርኩዛችሁ አመዛዛኝ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- የተዛቡ የአረፍተ ነገር አደረጃጀቶችን አስተካክላችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- ለምሳሌያዊ አነጋገሮች ተመሳሳያቸውን ትጽፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የቅድመ ማዳመጥ ተግባር

1. ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የቃል መልስ ስጡ፡፡

    1. የጊዜ አጠቃቀም ልምዳችሁ ምን ይመስላል?
    2. "ካልተሳፈሩበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ"፡-ከዚህ አባባል ምን ተገነዘባችሁ? ከላይ ካቀረባችሁት የመንደርደሪያ ሀሳብ በመነሳት የምታዳምጡት ምንባብ ምን ላይ የሚያተኩር ይመስለችኋል?

### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

    1. አንድን ስራ ከመስራታችን በፊት ምን ማድረግ አለብን?
    2. በምንባቡ መሰረት የጊዜ አጠቃቀም ዋና አላማ ምንድነው?
    3. "ጥሩ እቅድ ማቀድ የስራውን ሀምሳ በመቶ እንደማከናወን ይቆጠራል ይባላል" ሲል ምን ማለቱ ነው?
    4. በምንባቡ መሰረት ስራን መርጠን መስራት አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
    5. ምንባቡ የተሰጠንን ስራ በወቅቱ ማጠናቀቅ እንዳለብን ከእናንተ ጋር ያስተሳሰረው በምን መንገድ ነው?
    6. "የስራ ለነገዬ ይጥላል የምግብ ለነገዬ ያሻግራል" የሚለው

## አባባል በምንባቡ መሰረት ምን ያስረዳል?

## ክፍል ሁለት፡- መናገር ተግባር

1. ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ከተመለሳችሁ በኋላ የምታከናውኗቸውን ተግባራት በቅደም ተከተል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

2.ጊዜን በእቀድ ከፋፍሎ መተግበር ያለውን ፋይዳ በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን በተወካያችሁ አማካኝነት አቅርቡ፡፡

**ማስታወሻ**

**ጭውውት**

ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አንድ ርእሰ ጉዳይ አንስተው የመፍትሄ ሀሳብ ላይ ለመድረስ የሚያደርጉት የሀሳብ ልውውጥ ነው፡፡

እንደ ሌሎች የንግግር ዘዴዎች ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና ዳኛ የማይፈልግ ቢሆንም፣ በጭውውቱ ተሳታፊዎች ዘንድ ግን እርስበርስ መደማመጥ ሊኖር ይገባል፡፡

ጭውውት በመደበኛነት በሁሉም ሀብረተሰብ የዕለት ተዕለት ግንኙነት ውስጥ የሚከወን ተግባር ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሀሳቦችን ለማስተማሪያነት፣ ለመምከር ለመቀስቀስ እና ለማዝናናት በደራሲያን ተቀምሮ በተዋንያን አማካኝነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡-

የቤተሰብ ጭውውት

የጭውውቱ ተሳታፊዎች

| | |
|---|---|
| አቶ ሆርዶፋ | አባት |
| ወ /ሮ ረጋቱ | እናት |
| ጫላ | ተማሪ (ልጅ) |

አቶ ሆርዶፋ.................. ረጋቱ ! ይኽ ልጅ ምነው ዘገየ? ሰዓቱ አልፎ የለ?

ወ /ሮ ረጋቱ.................... ከጓደኞቹ ጋር እየተጫወተ ቀስ ብሎ እየመጣ ይሆናል !

አቶ ሆርዶፋ.................... አንች ደግሞ እንደዚህ የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየደረደርሽ ነው ይህንን ልጅ የሚታቃብጭው ዋ! ኋላ

ዱርዬ ሆኖ እንዳይቀርልሽ!

ወ / ሮ ረጋቱ................ እኔ ምን ብዬ አቀብጠዋለሁ? እርስዎ ደግሞ አፍዎ ላይ የሚመጣው ክፉ፣ ክፉ ነገር ነው ።

አቶ ሆርዶፋ.................... ኳስ ጨዋታውን ይዞ ይሆናል እንጂ?

ወ / ሮ ረጋቱ.................አሁን በምሳ ሰዓት ኳስ ይጫወታል ብለው ነው?

አሁን ይመጣል እስቲ ለትንሽ ጊዜ ታገሱ።

ተማሪ ጫላ......................... እንደምን ዋልክ አባዬ ?

አቶ ሆርዶፋ.......................የት ቆይተህ ነው አንተ? እስከዚህ ሰዓት ድረስ?

ጓደኞችህ ከመጡ ቆይተዋል ። ኸረ

አንተ ልጅ እባክህ ተመከር!

ጫላ................................ አስተማሪያችን አቀይቶን ነው ።
የጀመርኩትን ካልጨረስኩ አትሄዱም ብሎ ።

ወ / ሮ ረጋቱ...................... አሁን ተውት ምሳውን ይብላ በባዶ
አንጀቱ አታስለፍልፉት ።

አቶ ሆርዶፋ...................... እኮ! አንችማ ምን አለ? እንደዚህ
እየተከላከልሽ ነው ይህንን ልጅ ያበላሸሽው ።

ጫላ ................................ አባቴ እኔ ምንም ጥፋት የለኝም ።
አስተማሪው አቀይቶን ለመሆኑ ሌሎቹን የክፍል ጓደኞቼን

መጠየቅ ትችላለህ ። ት/ቤት ሄደህ ማረጋገጥም ትችላለህ ።

3. ከሁለት እስከ ሶስት ተማሪዎችን የሚያሳትፍ ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት የሚያስረዳ አጭር ጭውውት አዘጋጅታችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ምንባብ

ሞኙ ተላሌ

በአራት እግሩ ሲሄድ ሲቆም በሁለቱ፣
ሲያጌጥ ሲለባብስ የሰው ልጅ ኩራቱ፡፡
የኖረ ይመስለዋል አለም እዲህ ጣፍጣ፣
ወዙ ሲያብለጨልጭ ፈገግታው ሲበራ፣
ሰው እኔ ነኝ አኮ ማን አለ ጠንካራ፣
ብሎ ሲደነፋ ቆሞ ሲንጠራራ፡፡
ፍፁም አያስብም ሰአቱ ሲቆጥር፣
ነገ ዛሬ ሆኖ ወደትናንት ሲዞር፡፡
ቀድሞ አይሰማውም ደቂቃው ማለፉ፣
ቀኑ መሽቶ ነግቶ ሲለፈልፍ ወፉ፡፡
ዛሬ እኮ ዛሬ ነው ነገም ቢሆን እሱ፣
ከዕድሜው ላይ አንድ ቀን ሁለት መቀነሱ፡፡
“ይህ እርጅና አይደለም ዛሬ ጤናማ ነኝ፣”
“ተመልከት ጡንቻዬን ዝለል ብረር ሲለኝ!”
ነገ ሃያ ዘጠኝ በዓመቱ ሠላሳ፣
“አበድክ ጤናም የለህ ገና ነኝ ጎልማሳ!”

ሦላሳውም አልፎ አርባ ዓመት ሲሆነው፣

ቁጭ በል ተጫወት ይቅርብህ ሩጫው፣

“ማሞ መስታዎቱን እስቲ ወዲህ ስጠኝ፣”

“ከሸበቴ በቀር አሁንም ወጣት ነኝ!”

አምሳም ስድሳም አልፎ ዘጠና ቢሞላ፣

ሞኝ ነው የሰው ልጅ ማሞዬ ተላላ፡፡

እድሜ እያሳቀቀው እርጅና ቤት ገብቶ፣

ዞር ብሎ ሲያስተውል ያንን ዳገት ወጥቶ፣

መርበትበት መደንገጥ ያኔነው ሀዘኑ፣

ይገርማል ይደንቃ ልጄ እንዴት ሄደ ቀኑ፡፡

ሁሉም አዲስ ነገር አይቶ የማውቀው፣

ከቶ ምን ልብስ ነው ሳያውቅ ያጠለቀው፡፡

ውሀ ውስጥ ቆይቶ በሳት የተቆላ፣

ቆዳው ተጨማዶ ሲመስል በቁላ፣

ጅማቱ ሲታሰር እግሩ መሄድ ሲተው፣

እጁ ሲንቀጠቀጥ መጨበጥ ሲያቅተው፣

አይኑ እየደከመው ጆሮው ሲያወላውል፣

አንሱኝ ብድግ አርጉኝ ያዙኝ አቀፉኝ ሲል፣

እንዳያፍር ሲባል እንዳይወድቅ ሲጠገን፣

ህልም እየሆነበት የበረረው ዘመን፣

ለጽድቅ ነው ብሎ ሞት መጥቶ ሲያነሳው፣

ሰው ያብዳል ይጮሀል ያለቅሳል በሬሳው፡፡

(ፊቃደ አዘዘ፣የገጣሚና ሰዓሊ ገ/ክርስቶስ ደስታ የግጥም ስብስቦች (1947

1. በቀረበው የግጥም ምንባብ መሰረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ተስማሚውን መርጣችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. በግጥሙ ላይ የተጠቀሰው ፀጉሩ ቢሸብትም ገና ወጣት እንደሆነ የሚናገርው በስንት አመቱ ነው?

ሀ. በሰላሳ ለ. በዘጠና ሐ በአርባ መ. በሀያ

2. ጅማቱ ሲታሰር እግሩ መሄድ ሲተው፣ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. እርጅና ሲጫጫነው ሐ. የእግሩ ጅማት ሲበጠስ

ለ የጅማት በሽታ ሲይዘው መ .እገሩ በጅማት ክር ሲታሰር

3. በግጥሙ ውስጥ “ተመልከት ጡንቻዬን ዝለል ብረር ሲለኝ፡፡” የሚለው ሀሳብ፣

ሀ የግል አስተያየት ነው ሐ. እውነታ ላይ የተመሰረተ ነው

ለ. የሐሰት ወሬ ነው መ. ሀእና ለ መልስ ናቸው

4. በግጥሙ መሰረት ማሞዬ ተላላ የሚለው ሀረግ

የሚወክለው ----- ነው፡፡

ሀ. ባህሪን ለ. ቁመናን ሐ. ያታን መ. መጠሪያን

5. የግጥሙ አንኳር መልዕክት ምንድ ነው?

ሀ. የሰውልጅ ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም አለበት፡፡

ለ. እርጅና ሲይዘን ከመርበትበት በወጣትነት እድሜያችን

መስራት ይገባናል፡፡

ሐ ጊዜ እንደ ውሀ ጅረት ነው ካልተጠቀምንበት ጠርጎን ይሄዳል

መ.ሁሉም መልስ ይሆናሉ፡፡

2. በምንባቡ መሰረት በ ምድብ ‹‹ሀ›› ስር ያሉትን ቃላትና ሐረጋት በ ምድብ ‹‹ለ›› ስር ካሉት አውዳዊ ትርጉማቸውን ፈልጋችሁ አዛምዱ

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ሲያብለጨልጭ | ሀ. ሲዋብ |
| 2. ሲደነፋ | ለ. መፍራት |
| 3. ማሞዬ | ሐ. ህፃን ልጅ |
| 4. ሲያጌጥ | መ. ሲፎክር፤ሲያቅራራ |
| 5. መርበትበት | ሠ.ሲያንፀባርቅ፣ሲያበራ |

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### ማስታወሻ

### ድርሰት

የድርሰት ጥሬ ትርጉም ፅሑፍ ማለት ነው፡፡ ድርሰት እንደ ደራሲው ፍላጎት የሀሳብ ትስስር ባላቸው አንቀፆች የሚዋቀር የፅሑፍ አይነት ነው

ድርሰት በስርዓት በተሰደሩ የተመረጡ ቃላት፣ ሀረጋትንና ዐረፍተ ነገሮች እያቀናጁ ሀሳብን አሟልተው የሚገልፁ አንቀፆችን የመፃፍ ሂደት ነው፡፡

የድርሰት አይነቶች ተራኪ፣ አስረጅ(ገላጭ)፣ ሥዕላዊ እና አመዛዛኝ በመባል በአራት ይከፈላሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ አመዛዛኝ ድርሰትን እንመለከታለን፡፡

### አመዛዛኝ ድርሰት

አመዛዛኝ ድርሰት አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚጽፍ፣ አንባቢውን( አድማጩን) ስለአንድ ጉዳይ እውነትነት ወይም ሐሰትነት ለማሳመን የሚጥርበት፣ ደራሲው ለአንድ ወገን ቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ በቻ ለመቃወም ወይም ለመደገፍ ሊፅፍ የሚችልበት ወይም

ለሁለቱም አከራካሪ ሀሳቦች የቆመ ለመምሰል ጉዳዩን በመቀበልና በመቃወም አቅርቦ በመጨረሻም ማስረጃው ያዳላበትን አጠናክሮ በመተቸት ሌላኛውን በመደገፍ ወደ አንድ ውሳኔ እንዲደርስ ለማሳመን የሚጥርበት የድርሰት አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡-

ብዙ የስነ ትምህርት ምሁራን ማስተማር ሳይንስ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ጥበብ ነው ይላሉ፡፡ ጥበብ ነው የሚሉት፣ የመማር ማስተማር ዘዴ ምንም ህግ የለውም ይላሉ፡፡ ጥሩ አስተማሪነት የሚመነጨው ከሰውየው ችሎታ እንጂ ከሚገኘው ስልጠና አይደለም የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡

ሳይንስ ነው የሚሉት ተመራማሪዎች በበኩላቸው አስተማሪ ህጎችን ተንቅቆ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በክሂሎትና በአመለካከትም በኩል ያሉትን ህጎች የሚገነዘብ መሆን አለበት፡፡ በዚህም መሰረት ሁሉም መምህራን በስነ ትምህርት ሳይንስ ሊሰለጥኑ ይገባል በማለት ይሞግታሉ፡፡

በኛ እምነት መማርና ማስተማር ሁለት የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው፡፡ ማስተማር መማርን እንዲያስከትል በመጀመሪያ የመማር ማስተማር ህጎችን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም መምህራን የስነ ትምህርት ዘዴ ሳይንስን በሚገባ ማጥናት ይኖርባቸዋል

## ተግባር

1. ለሚከተሉት መንደርሪያ ሀሳቦች ለአመዛዛኝ ድርሰት ማስፋፊያ የሚሆኑትን በቡድን በመሆን ለይታችሁ የመረጣችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1 ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል፡፡

2. የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን የጀመረው አስራ አንድ አመቱን ካገባደደ ነበር፡፡

3. የ ሁለቱንም ተማሪዎች ችሎታ ባደንቅም ደሚቱ ከጋዲሳ የምትለይበት በርካታ ነገሮች እንዳሉ ግን ግልጽ ነው፡፡

4. ዘንድሮ ባሳለፍነው አመት ያጋጠመንን ፈተና የካሰን አመት ነው፡፡

5. አቶ በየነ ገመዳ ጠይም መልከ መልካም ሰው ናቸው፡፡

6.አንድን ሻማ አቀጣጥለን ሲበራ ብናየው በመጀመሪያ ሰሙ ይቀልጣል፤

7. አሮጌው አመት አልፎ በአዲሱ ሲተካ ሁሉም ያቀደውን ለማሳካት ደፋ ቀና ይላል፡፡ ግማሹ የትምህርት ደረጃን ለማሻሻል፣ ለላው ትዳር

ለመያዝ አንዳንዱ ደግሞ ለለመሰደድ ሽር ጉዱ ይጦፋል…

2. በመረጣችሁት ርዕስ ከሦስት ባልበለጡ አንቀፆች የተደራጀ አንድ አመዛዛኝ ድርሰት ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል አምስት ቃላት ተግባር

1. ለሚከተሉት ቃላት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተቃራኒ ፍቺያቸውን በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡

1. ማግባት፦ ሀ. መግባባት ለ. መጣላት ሐ. መፍታት መ. ፍርሀት
2. አቀበት፦ ሀ. ዳገት ለ. ቁልቁለት ሐ. ጠመዝማዛ መ. ወጣገባ
3. መንቀፍ፦ ሀ.መዘለፍ ለ. ማንቋሸሽ ሐ. ማወደስ መ. መውደድ
4. ጥንታዊ፦ ሀ.ታሪካዊ ለ. ድሮ ሐ. አሮጌ መ. ዘመናዊ
5. ፈጣን፦ ሀ. ከባድ ለ. ችኩል ሐ. ንቁ መ. ቀርፋፋ
6. ታገደ ፦ ሀ. ተከለከለ ለ. ተፈቀደ ሐ. ተወነጀለ መ.ተገደበ
7. ማለደ ፦ ሀ. ፈጠነ ለ. አረፈደ ሐ. ገሰገሰ መ. ለመነ

8.ምስጢር፦ ሀ. ግልጽ ለ. ድብቅ ሐ.ስውር መ.ብልጥ

9.አዝናኝ ፦ ሀ.ማራኪ ለ. ጋባዥ ሐ. አስጨናቂ መ. አስደሳች

10. ብርሃን ፦ ሀ. ጨረቃ ለ . ሰማይ ሐ. ፍርሀት መ. ጨለማ

2. ለሚከተሉት ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ተቃራኒ ፍቺያቸውን በደብተር ላይ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፦ ሀብታም = ድኻ ሰነፍ = ጎበዝ

ረጅም = አጭር

ሀ. በተነ = ረ. ተከለ =

ለ. ብዙ = ሰ. መረቀ =

ሐ. ዘጋ = ሸ. ደስታ =

መ. ደማቅ = ቀ. ሩቅ =

ሠ. ቋጠረ = በ. ፈሪ =

ክፍል ስድስት ስዋስው ተግባር

2. የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች የዐረፍተ ነገር መዋቅር ቅደም ተከተልን ያልጠበቁ ናቸው፤ዐረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡- ይታወቃል በመርዳት የተቸገሩትን የቶልቻ ቤተሰብ - (ስህተት)

**የቶልቻ ቤተሰብ የተቸገሩትን በመርዳት ይታወቃል። (ተስተካክሎ ሲፃፍ)**

1. የህዳሴ ግድብ/ ነው/ እና/ እድገት/ ብልፅግና/ ለኢትዮጵያ/ መሰረት

______________________________________________::

2. ሰው/ ሙሉ/ ያደርጋል/ ማንበብ

______________________________________________::

3. አከበረ /ታታሪው/ ተማሪ/ የትምህርት ቤታችን/ ልደቱን/ በረሶ

______________________________________________::

4. ተምረን /ጠንክረን/ እናሳድጋለን/ ሀገራችንን

______________________________________________::

5. ወጥታ/ ፀሀይ/ በምእራብ/ በምስራቅ/ ትገባለች

______________________________________________::

**ማስታወሻ**

**ባለፈው ምዕራፍ አረፍተ ነገሮችን ከሚይዙት የግስ ብዛት አንፃር ነጠላ እና ውስብስብ ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ አይተናል። በተመሳሳይ ከአገልግሎታቸው አኳያ ዐረፍተ ነገሮች**

**በአራትይከፈላሉ። እነርሱም፡-**

1. ሐተታዊ ዓረፍተነገር

በዘወትር የሀሳብ ልውውጣችን ውስጥ የማይጠፋ በአራት ነጥብ የሚጨርስ የዐረፍተ ነገር ዐይነት ነው፡፡ ሀ ተታዊ ዐረፍተነገሮች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ደብሪቱ የቡራዩ ከተማ ነዋሪ ነች፡፡ ( አዎንታዊ ዐ.ነገር)

ሰቦቃ ወደ ትምህርት ቤት አልመጣም፡፡ ( አሉታዊ ዐ.ነገር)

2. መጠይቃዊ ዐረፍተ ነገር

ከርዕሱ እንደምንረዳው በጥያቄ መልክ የሚቀርብ የዐረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡ ምሳሌ፡- ወደ ሀገርህ የምትመለሰው መቼ ነው?

አባቴ አስከፋህ አይደል?

ጥሬ ነገር መብላት ትወዳለህ?

3. ትዕዛዛዊ ዐረፍተ ነገር

አንድ ነገር እንዲፈፀም ወይም እንዳይፈፀም ትዕዛዝ የሚተላለፍበት የዐረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- በአቸኳይ ቢሮ እንድትቀርብ !

ደብተሩን መልስ!

4. አጋናኝ ዐረፍተ ነገር

እንደ መደነቅ፣ መደሰት፣ መውደድ ወይም መጥላት ወዘተ… የመሳሰሉትን ስሜቶች ለመግለጽ የሚያገለግል የዐረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡፡

ምሳሌ፡- እሰይ! ዛሬ ውጤቴን አየሁ ትምህርቴን አጠናቀቅሁ!

ተግባር

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች ሀተታዊ መጠይቃዊ ትዕዛዛዊና አጋናኝ ዐረፍተ ነገሮች በማለት ለዩ።

1. ገርማሜ ሀገሩን ይወዳል።
2. የሁለተኛው ክፍለ ጊዜ የሚጀምረው መቼ ነው?
3. በፍጥነት ከአልጋው ላይ ውረድ!
4 ይገርማል! ጊዜው ሳይታወቀን ነጎደ።
5. አለባበሷ ልዕልት አስመስሏታል!
6. እኔ ነገ በጠዋት አልመጣም።
7. በትምህርቴ ጥሩ ደረጃ እንድደርስ ምን ላድርግ?
8. ወደ ቤት ና!

## ክፍል ሰባት ስነ ፅሑፍ

ማስታወሻ

ምሳሌያዊ አነጋገር በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሰረት የሚፈጠር በቁጥብና በምርጥ ቃላት በአጭሩ የተጨመቀ ጥልቅ ሀሳብን የያዘ የስነቃል አይነት ነው፡፡

ስነቃል በርካታ ማህበራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል ሰዎች ደስታና ሐዘናቸውን፣ ድልና ሽንፈታቸውን፣ የወደፊት ምኞታቸውን፣ በአጠቃላይ ለህይወት ያላቸውን አመለካከት ይገልጹበታል፡፡

ምሳሌ፡-

ሳይሰሩ ማግኘት ሳይጸድቁ ገነት

ትንሽ ቆሎ ይዘህ ካሻሮ ተጠጋ

ጨዋ ሎሌውን ባለጌ ጌታውን ይወዳል

አረምን መንቀል ስር ሳይሰድ ነው

ሀምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሀምሳ ሰው ግን ጌጡ

## ተግባር

1. የሚከተሉትን በምድብ ‹‹ሀ›› ስር የተዘረዘሩ ምሳሌያዊ አንጋገሮች ተመሳሳያቸውን ከ ‹‹ለ›› ስርበመፈለግ አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.ሊጣላ የመጣ ሰበብ አያጣም | ሀ. በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት |
| 2.ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ | ለ.ብልጥ ለብልጥ አይን ብልጥጥ |
| 3.አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ | ሐ.ካንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ |
| 4.ስራ ለሰሪው አሾህ ላጣሪው | መ.ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ |
| 5.እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ | ሠ. ደባ ራሱን ስለት ድግሱን |
| 6.የተቸገረ ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል | ረ. የቸገረው እርጉዝ ያገባል |
| 7.እሷው ሞታ እሷው መርዶ ጠርታ | ሰ. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል |
| 8. የአባይን ልጅ ውሀ ጠማው | ሸ. የላጭን ልጅ ቅማል በላው |
| 9. ድር በያብር አንበሳ ያስር | ቀ. ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮኻል |
| 10.በአባቱ ከተማ ልጁ ተቀማ | በ. ደባልና ሹመት ያለምክንያት አይጠፋም |

2.ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን

በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡

1.ቃል አባይ፡-

ሀ . ዳተኛ ለ .ዋሾ ሐ. መሰሪ መ. ወስዋሳ

2.የሰሚ ሰሚ፡-

ሀ. ቀን በቀን ለ. ፊትለፊት ሐ. ዐይንባይን መ. የወሬ ወሬ

3. ሳር ቅጠሉ፡-

ሀ. ዘመድ አዝማዱ ለ.ወንዛወንዙ ሐ. ሀገርምድሩ መ. ሜዳ ተራራው

4.የእርጎ ዝምብ፡-

ሀ. በማያገባው የሚገባ ለ. እርጎ አፍቃሪ ሐ. ቀዥቃዣ መ. እራስ ወዳድ

5. ሁነኛ፡-

ሀ. ተመራማሪ ለ. ታማኝ ሐ. ሁለተኛ መ. ተወዳጅ

6. መንገድ አሳበረ

ሀ. መንገድ አቋረጠ ለ መንገድ ቀየሰ ሐ.መንገድ አበላሸ መ ሀሳብ አጠረው

# ምዕራፍ ስድስት

## የሀገር ፍቅር

### የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የቀረበውን ምንባብ አዳምጣችሁ ለጥያቄዎች የቃልና የፅሑፍ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- የሀገር ፍቅር መለኪያ መስፈርት ምን እንደ ሆነ የግል አመለካካታችሁን በቃል ትናገራላችሁ፡፡
- የጥንትም ሆነ የአሁን የኢትዮጵያ አርበኞችን ጠቅሳችሁ ለሀገራቸው ያበረከቱትን አስተዋፅዖ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ታብራራላችሁ፡፡
- ስለ ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ የሚያወሳ ምንባብ አንብባችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃልና በጽሑፍ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- የሀገር ባለውለታ ናቸው ከምትሏቸው ግለሰቦች መሀል የአንዱን የሕይወት ታሪክ ፅፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች በንባብ ታቀርባላችሁ፡፡
- ስዕሎችን ተመልክታችሁ ስለተሰማችሁ ነገር ባለ ሁለት ወይም ባለ ሦስት አንቀጽ ድርሰት ፅፋችሁ ክፍል ውስጥ ታነባላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

1. ፍትሀዊ ዳኝነት ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ማለት ነው?

2.ፍርድ እንዳይዛባና ፍትህ እንዳይጓደል ምን ማድረግ ይገባል ብላችሁ ታስባላችሁ?

### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1.“አመካኝተው በሏት” በሚል ርእስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. በምንባቡ መሠረት ሀጢአታቸውን የተናዘዙት አራዊቶች እነማን ናቸው?

2. ዳኞች የፈረዱት በማን ላይ ነው?

3. አራዊቱ ሲናዘዙ ምን ምን በልተናል አሉ?

4.ሀጢአታችንን እንናዘዝ ያለው ማነው? ለምን?

5.ዳኞች የሰጡት ፍርድ ትክክል ነው ትላላችሁ? አብራርታችሁ አስረዱ፡፡

6. ከምንባቡ ሀሳብ ምን ተገነዘባችሁ?

2. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሐሰት በማለት በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. አራዊቶቹ ምግብ በማጣታቸው ሀጢአታቸውን ለመናዘዝ ወሰኑ፡፡

2.አንበሳ ከእረኛ ያመለጠ ፍየል ጫካ ውስጥ አግኝቶ በላ፡፡

3. አራዊቶቹ ምግብ ያጡት ሀጢአት ስላበዙ ነው፡፡

4. ጅብ ሽክም ያቃታትን አህያ በመብላቱ ሀጢአተኛ ሆኖ ተፈረደበት፡፡

5. ያለ  አቅሟ ጓደኝነትን የመሠረተች አህያ ናት፡፡

3. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. አንድነት
2. ተንከራተቱ
3. መናዘዝ
4.ፍርድ
5.መንጨት
6. መጋዣ
7. ወጠጤ
8. ማመካኘት
9.እረኛ
10.መሲና

## ክፍል ሁለት የመናገር ተግባር

1. በእናንተ አመለካከት ሀገርን የመውደድ መለኪያ መስፈርት ምንድነው በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፡፡
2. ኢትዮጵያን ከቀድሞው ትውልድ ለአሁኑ እንድትሻገር አስተዋጽዖ ካበረከቱ ጀግኖች አንዱን መርጣችሁ የፈጸመውን ገድል ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ፡፡
3. “የሀገር ፍቅር ማለት ሀገር ስትወረር ከጠላት ለመከላከል መዝመት ብቻ ነው፡፡” በዚህ ሀሳብ ትስማማላችሁ? መልሳችሁ አልስማማም ከሆነ ሌሎች የሀገር ፍቅር መግለጫ ተግባራትን ግለሰቦችን ምሳሌ በማድረግ በቃል አብራሩ፡፡

## ክፍል ሶስት ማንበብ

### ቅድመ ምንባብ

1. አንድ ሰው የሀገር ፍቅር አለው የሚባለው ምን ሲያደርግ ነው?
2. ሀገራቸውን የማይወዱ ሰዎች በምን ይለያሉ?
3. ለመሆኑ፣ እናንተ ሀገራችሁን ትወዳላችሁ? እንዴት?

## ምንባብ

### ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ

አትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ የተወለዱት በ1909 ዓ.ም በቀድመሞው ሸዋ ክፍለ አገር በመናገሻ አውራጃ በሱሉልታ ወረዳ በአካኮና መናበቹ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው፡፡ ፓስፖርታቸው ላይ የተመዘገበው የእድሜ መረጃ እና ሌሎች ሰነዶች እንደሚናገሩት ከሆነ አሁን መቶን ተሻግረዋል፡፡ በሩጫ መድረክ ላይ የነገሱትን ዋሚ ቢራቱ ወደ ዚህች ምድር ያመጧቸው እናታቸው ወይዘሮ ወርቄ አያና እና አባታቸው ቢራቱ በራቄ ናቸው፡፡ ዋሚ ጠንከር እያሉ ሲመጡ በመንደራቸው ላይ ቤተሰባቸውን ከብት በመጠበቅ እንዲሁም አንዳንድ የእርሻ ስራዎችን በማከናወን ይረዱ ነበር፡፡ ተሮጦ ዝነኛ እንደሚኮን እንዲሁም ሰዎችን ሌሎች ተፎካካሪዎችን መብለጥ እንደሚችሉ ያወቁት ባጋጣሚ ነበር፡፡ በሩጫ አገር ማስጠራት እንደሚቻልም እንደዚሁ፡፡ አጋጣሚውን የፈጠሩት ደግሞ እናታቸው ናቸው፡፡ ወይዘሮ ወርቄ አንዳንድ ነገሮች ለመሸማመት ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፡፡ አስፈላጊውን ሁሉ ካከናወኑ በኋላም ወደ ቀዬአቸው ይመለሳሉ፡፡ ልጅ ዋሚ ደግሞ እናታቸው ሸክፈው የመጡትን እቃ ተቀብለው ወደ ቤት ይገባሉ፡፡ በዚህ እቃ ተጠቅልሎበት የመጣ ጋዜጣ እጃቸው ላይ ይገባል፡፡ ጋዜጣው የአንድ ሯጭ ምስልን ይዟል፡፡ ዋሚ ደግሞ በመንደራቸው ጋራ ተራራውን፣ ቁልቁለት ዳገቱን በሩጫ ሲቦርቁ ነው የሚውሉት፡፡ ሩጫ ስፖርት መሆኑን ተገንዝበውም እርሳቸው ጥሩ ሯጭ መሆን እንደሚችሉ በማመናቸው ልባቸው ይህን ማድረግ ይመኝ ጀመር፡፡ ይህ ከሆነ ከ 2ዓመት በኋላ ወንድማቸውን ሊጠይቁ ወደ አዲስ አበባ ጎራ አሉ፡፡

በዚያች ገጠመኝም አዲስ ወታደሮች ሲመለመሉ ተመለከቱ። ምልመላውን ቆመው ሲመለከቱ አንድ ሃምሳ አለቃም ዋሚን ለምን አትገባም ብሎ ጥያቄ አቀረቡላቸው። ከመስከረም 5 ቀን 1945 ዓ.ም ጀምሮ ወታደር ሆነው ተቀጠሩ። ስልጠናቸው ሲጨርሱ ዋሚ ሁለተኛ ክፍለ ጦር ተመድበው ወደ አስመራ ሄዱ። በወቅቱ ምልመላ ወታደሮችና ነባሮች በህብረት ሩጫ ይወዳደሩ ነበር ።

በ10 ኪ.ሜ ዋ ሚ አንደኛ ሆነው ማሸነፍ ቻሉ ። ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ በተለያዩ የሩጫ መድረኮች ላይ አገራቸውን ያስጠሩበት ድል አስመዝግበዋል። ከነዚህ መካከል በ1ሺ500፣ 3ሺ፣ 5ሺ፣ 10ሺ፣ 21ኪ.ሜ፣25ኪ.ሜ፣ በ32ኪ.ሜ በአገር አቋራጭ እና የተለያዩ የማራቶን ውድድሮች ላይ በመሳተፍ 51 የወርቅ፣ 44 የብር እና 30 የነሀስ ሜዳሊያዎችን ማግኘት ችለዋል። ከዚህም ሌላ 21 ሰርተፍኬት፣ 4 ዲፕሎማ እና ከ40 በላይ ዋንጫዎችን ወስደዋል። በተለያየ ወቅትም የኢትዮጵያ ባንዲራ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ አስችለዋል። የሶምሶማ እሩጫ በአገራችን እንዲለመድ ለማድረግ ጥረት ያደረጉ መሆናቸውም ይነገርላቸዋል። እኚህ አንጋፋ አትሌት ምንም እንኳን እድሜያቸው ቢገፋም በተለያየ ጊዜ ውድድሮችን እና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ይታወቃሉ። ለጠንካራ ተክለ ሰውነታቸው እና በጤንነት ረጅም እድሜ መቆየታቸው ደግሞ በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች መሳተፋቸው ያመጣው ውጤት እንደሆነ ይነገራል። ከዚህ ጥንካሬያቸው መካከልም በእርጅና እንደ አበበ ቢቂላ ላሉ ብርቅዬ አትሌቶች አርአያ የሆኑ ድንቅ የሀገር ሀብት ናቸው።

ዘመናቸው በታላቁ ሩጫ ላይ ተሳታፊ ሆነው ያለምንም ከዚያን ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ለአገራችን ድልን በማስመዝገብ

ችግር ማጠናቀቃቸው ነው፡፡ ሻለቃ ባሻ ዋሚ  እድሜያቸው 104 አመት ሞልቷል ግን አሁንም አልበገሬው ኢትዮጵያዊ ወኔ ፊታቸው ላይ ፍንትው ብሎ ይታያል፡፡ ጀግናው ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ በአትሌቲክሱ ላይ ደግሞ ለ64 አመት ነግሰውበታል፡፡

(https://am.wikipedia.org/ ዋሚ ቢራቱ በሚል 2016 ለንባብ ማስተማሪያ ተቀንጭቦ የቀረበ)

## ድህረ ምንበባብ ተግባር

1. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. የሻለቃ ዋሚ ቢራቱ የትውልድ ስፍራ የት ነው?
2. ለሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ የሩጫ ህይወት መነሻ የሆነችው አጋጣሚ የተፈጠረችው እንዴት ነው?
3. ዋሚ በልጅነታቸው ቤተሰባቸውን በምን በምን ያግዙ ነበር ?
4. ዋሚ አዲስ አበባ የመጡት  ለምን ጉዳይ ነበር ?
5. ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ  በሩጫ ህይወታቸው  በአጠቃላይ ስንት የሜዳልያ ሽልማት ለሀገራቸው አስገኙ ?
6. ዋሚ በዕርጅና ዘመናቸው የተሳተፉበት የሩጫ መድረክ ምን ይባላል ?

2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ  አገር በመናገሻ አውራጃ በሱሉልታ ወረዳ በቀርሳና  ገብረ ጉራቻ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው፡፡
2. ዋሚ ቢራቱ  በሩጫ  ዝነኛ እንደሚኮን እንዲሁም ሰዎችን ሌሎች ተፎካካሪዎችን መብለጥ እንደሚችሉ ድሮውንም ያውቁት ነበር ፡፡
3. ዋሚ ጥሩ ሯጭ መሆን እንደሚችሉ ያመኑት በመንደራቸው ጋራ ተራራውን፣ ቁልቁለት ዳገቱን በሩጫ ሲቦርቁ ማደጋቸው ነው፡፡
4. ዋሚ ወታደር ሆነው የተቀጠሩት የቅጥር ማስታወቂያ ባነበቡበት አጋጣሚ ነው ፡፡
5. ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ በመጀመሪያው የሩጫ ውድድር በ10 ኪ.ሜ አንደኛ ሆነው  ወጥተዋል፡፡
6.  ጀግናው ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ በአትሌቲክሱ ላይ  ለስድሳ አራት  አመት ነግሰውበታል፡፡

ክፍል አራት መፃፍ ተግባር 1.

ለሀገር ባለውለታ ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱ ሀገር ወዳድ ግለሰቦች መካካል  ስለአንዱ  መረጃ  ከመፅሐፍ  መፅሔት፣ጋዜጣና  ሬዲዮ ወዘተ በመሰብሰብ አጭር  የህይወት ታሪክ ፅፋችሁ ለተማሪዎች አንብቡላቸው፡፡

2 ቀጥሎ የቀረቡትን ምስሎች ተመልከታችሁ የተሰማችሁን ነገር ከሁለት ባልበለጡ አንቀፆች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ ፡፡


## ክፍል አራት የመፃፍ

### ተግባር 2.1.

ለሀገር ባለውለታ ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱ ሀገር ወዳድ ግለሰቦች መካካል ስለአንዱ መረጃ ከመፅሐፍ፣ መፅሔት፣ጋዜጣና ሬዲዮ ወዘተ በመሰብሰብ አጭር የህይወት ታሪክ ፅፋችሁ ለተማሪዎች አንብቡላቸው።

2 ቀጥሎ የቀረቡትን ምስሎች ተመልከታችሁ የተሰማችሁን ነገር ከሁለት ባልበለጡ አንቀፆች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ ።



ማስታወሻ

ሰዋስዋዊ ግድፈቶች (ስህተቶች)

በአንድ ዓረፍተነገር መዋቅር ውስጥ በባለቤትና በማሠሪያ አንቀጽ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከሚገቡ ቃላት መካከል የሚፈጠር የአገባብ (የመዋቅር ስህተት) ሰዋስዋዊ ግድፈቶች ይባላሉ:: በዓረፍተነገር ውስጥ ብዙ ዓይነት ሰዋሰዋዊ ግድፈቶች ቢኖሩም የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው::

1. የቁጥር አለመስማማት ችግር

በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ያሉ ባለቤቶችና ግሶች የቁጥር ስህተት ሲነኖርባቸው ማለትም ባለቤቱ ነጠላ ቁጥር ሆኖ ግሱ ብዙ ቁጥር ወይም ባለቤቱ ብዙ ቁጥር ሆኖ ግሱ ነጠላ ቁጥር ከሆነ የቁጥር አለመስማማት ችግር ይባላል::

ምሳሌ፦ 1. ለሜሳ እየሮጠ ወደ ቤቱ መጡ:: ባለቤቱ ለሜሳ ነጠላ ቁጥር ሲሆን ግሱ ግን መጡ ብዙ ቁጥር ሆነ::

2. ልጆቹ በህብረት ትልቅ ዝማሬ አሰማ::

3.ሰአዳ ብዙ መጽሐፎች ገዙ::

2. የፆታ አለመስማማት ችግር

በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ባሉ ባለቤትና ግሶች (ማሠሪያ አንቀጽ) መሀል የፆታ አለመስማማት ችግር ሲከሰት ማለትም ባለቤቱ ወንድ/ ተባዕት ፆታ ሆኖ ማሠሪያ አንቀጹ ሴት ( እንስት ) ፆታ ሲሆን

ወይም እንስት ፆታ ሆኖ ማሠሪያ አንቀጹ ወንድ (ተባዕት ) ፆታ ሲሆን የሚፈጠር ችግር የፆታ አለመስማማት ችግር ይባላል።

ምሳሌ፦ 1.ልጅቷ ደብተሮቹን በደንብ አዘጋጀ። ባለቤቷ ሴት ፆታ ስትሆን አዘጋጀ ግሱ ደግሞ ወንድ ፆታ ነው።

2. ትልቁ ዛፍ በመጥረቢያ ዛሬ ተቆረረጠች።

3. ውድድሩን ያሸነፈው ተማሪ ሽልማት ልትቀበል መጣች።

3. የመደብ አለመስማማት ችግር

በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ያሉ ባለቤትና ማሠሪያ አንቀፆች የቁጥር ችግር ሳይኖርባቸው የመደብ ችግር ሲፈጠር የሚከሰት ነው።

| መደብ | ነጠላ ቁጥር | ብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| 1ኛ መደብ | እኔ | እኛ |
| 2ኛ መደብ | አንተ/አንቺ | እናንተ |
| 3ኛ መደብ | እሱ/እሷ | እነርሱ |

የመደብ ችግር ምሳሌ

1. እነርሱ ሁል ጊዜ በደንብ ታጠናላችሁ። ባለቤቱ እነርሱ ሦስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሲሆን ግሱ ታጠነናላችሁ ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሆነ።

2. አንተ ዛሬ በደንብ እተኛለሁ።

4.የጊዜ አለመስማማት ችግር

በዓረፍተነገር ውስጥ ያሉ ድርጊቶች የሚከናወኑበት ወቅት ተመሳሳይ

ወይም ተያያዥ ሳይኖረው ሲቀር የሚፈጠር ችግር የጊዜ አለመስማማት ችግር ይባላል።

ምሳሌ ፦1.የሩጫ ውድድሩ ትናንት ይካሄዳል። ትናንት ሀላፊ ጊዜ ሲሆን ይካሄዳል ደግሞ የወደፊት ጊዜ ነው።

2.ቶለሳ ውጤቱን ወደፊት አሻሻለ።

## ተግባር

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ትክክለኛውን ምረጡ

ድሪባ ወደቤት መጣች። የዚህ ዐረፍተ ነገር ሰዋስዋዊ ግድፈት ---- ነው።

ሀ. የመደብ አለመስማማት ለ. የፆታ አለመስማማት

ሐ.የቁጥር አለመስማማት መ. የተሳቢ አለመስማማት

2. እናንተ ምን ልትሰሩ መጡ። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት ምንጩ ምንድነው?

ሀ. የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ በቁጥር አለመስማማት

ለ. የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ በጊዜ አለመስማማት

ሐ. የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ በፆታ አለመስማማት

መ. የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ መደብ አለመስማማት

3.እናቴና አባቴ ከገበያ መጣ። የዚህ ዐረፍተ ነገር ሰዋስዋዊ ስህተት ምንድነው?

ሀ. የቁጥር ለ የመደብ ሐ. የፆታ መ. የጊዜ

4. ደቻሳ የሚመጣው አመት ጥሩ ውጤት አመጣ። አረፍተ ነገሩ ያስተናገደው ስዋስዋዊ ስህተት ----- ነው።

ሀ. የጊዜ አለመስማማት ለ.የቁጥር አለመስማማት

ሐ. የጊዜ አለመስማማት መ. የመደብ አለመስማማት

5. ከሚከተሉት ውስጥ ባለቤቱ ከማሰሪያ አንቀፁ ጋር በፆታ የማይስማማ ዐረፍተ ነገር የትኛው ነው።

ሀ. አበዲሳ የናርዶስን መፅሐፍ አልመለሰለትም።

ለ. አማረች ለሌሊሴ የቤት ስራ አስረዳችሽ።

ሐ አንተ! የምትሄዱት ወዴት ነው?

መ. እሱ ትናንትና ይመጣል።

6. ከበደ እና ኢብሳ ሸገር ባስ ላይ ተሳፈርን ይህ ዐረፍተ ነገር የሚታይበት ሰወስዋዊ ግድፈት ----- ነው።

ሀ. የባለቤት ከማሰሪያ አንቀጽ ጋር በቁጠር አለመስማማት

ለ. የባለቤት ከማሰሪያ አንቀጽ ጋር በጊዜ አለመስማማት

ሐ. የባለቤት ከማሰሪያ አንቀጽ ጋር በፆታ አለመስማማት

መ. የባለቤት ከማሰሪያ አንቀጽ ጋር በመደብ አለመስማማት

# ክፍል ስድስት ስነ ፅሑፍ

## ማስታወሻ

### ዘይቤያዊ አነጋገር

ዘይቤ አንድን አጉልቶ ለማሳየት የምንጠቀምበት የአገላለጽ ዘዴ ነው:: ሀሳባችንን በቃልም ሆነ በጽሁፍ በምናስተላልፍበት ወቅት እኛ የተረዳነውን ያህል አድማጮቻችን ወይም መልዕክት ተቀባዮቻችን እንዲረዱልን ለማድረግ እንጠቀምበታለን:: ዘይቤ ሁለት ነገሮችን መሠረት አድርጎ ይዋቀራል:: አንደኛው ቀደም ሲል በውል የሚታወቅ ፣ በባህሪው የሚለይ በአጠቃላይ በሰዎች አእምሮ የተቀረፀና የተቀመጠ ነገር ነው:: ሁለተኛው ደግሞ አዲስ የሚገለፀው ነገር ወይም ሀሳብ ነው:: አዲሱ በውል አይታወቅም፣ ባህሪው ተለይቶ አልተንፀባረቀም:: መልዕክት ተቀባዩ ወይም አድማጩ ገና ወደፊት ሲነገረው ወይም ሲተላለፍለት የሚገነዘበው ነው:: ዘይቤ በውል በሚታወቀውና በአዲሱ ሀሳብ መካከል ንጽጽር፣ውድድር፣ መመሳሰል፣መቃረን፣ መመጣጠን፣ መወራረስ፣ ወዘተ ልንመሠርት እንችላለን::በዚህ መንገድ አዲሱ ሀሳብ በታዋቂው ነባር መግለጫ አማካይነት ጎልቶ እንዲታይ የምናደርግበት የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ዘይቤያዊ አነጋገር ተብሎ ይጠራል::በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ አብዛኛው የቋንቋው ተገልጋይ በዕለት ተዕለት ከሚጠቀምባቸው ዘይቤዎች ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. ሰውኛ ዘይቤ

ሰውኛ ስያሜው ራሱ እንደሚያመለክተው የሰው መሆን ማለት ነው:: ህይወት የሌላቸውን ነገሮችና ከሰው ውጭ የሆኑ ፍጥረታትን እንዲሁም እፅዋትን የሰው ባህሪይ፣ አኗኗር ወዘተ በማላበስ በታዋቂው ሰው አማካይነት የሌላው ተገላጭ ሀሳብ ጎልቶ እንዲታይ ማድረጊያ ነው::

ምሳሌ፦ ጨለማው ጥርሱን አገጠጠ::

- እንኳን ሰው ሳር ቅጠሉም ብሶቱን እየገለፀ ነው::

2. አነጻጻሪ ዘይቤ

እንደ፣ ይመስላል፣ ያህላል፣ ይፎካከራል የሚሉ የማነጻጸሪያ ቃላትን በመጠቀም የሚፈጠር ዘይቤ አነጻጻሪ ዘይቤ ይባላል::

ምሳሌ ፦ እንደደራሽ ውሃ ድንገት ከተፍ አለች::

- ፊቱ ተነቅሎ የተጣለ የአረም ቅጠል ይመስላል::

3.ተለዋጭ ዘይቤ

የአንዱን ባህሪ ለሌላ በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ ዓይነት ተለዋጭ ዘይቤ ይባላል::

ምሳሌ፦ ጓደኛዬ የቀን ጅብ ነው::

- አባወራው ሸንቁር ጋን ናቸው::

## ክፍል ስድስት ስነ ፅሑፍ

የሚከተሉትን ዘይቤያዊ አነጋገር አነፃፃሪ ፣ተለዋጭ እና ሰውኛ በማለት ለዩ።

1. የታደሉ አይን እንደ ኮከብ ያበራል።

2. ድርቤ አራስ ነብር ነች።

3 ለሰው ሞት አነሰው አለች ቀበሮ።

4. ሲቲና እንደነብር ጮኸች።

5. እንደ ቅቤ እቃ የወዛው ፊቷ

6. መሬት ተቀዳ ስሰፋ አለች ጦጣ

7. በድመት ጥፍሩ አንቆ ያዘው

8.ሰውየው የቀን ጅብ ነው።

9. ድፍረት የሌላት ብዕር

10. ቀን ሲሆን ከዋክብት ያሽልባሉ።

# ምዕራፍ ሰባት

## ስነ ቃል

### የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- መምህሩ የሚያነቡላችሁን ግጥም አዳምጣችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃልና በፅሁፍ ትመልሳላችሁ፡፡
- ሰለ ስነቃል ምንነት ትናገራላችሁ፡፡
- ስነቃል ማህበረሰብን አንፃ ከትውልድ ትውልድ ለማሻገር ስላለው ፋይዳ የቡድን ውይይት ታደርጋላችሁ፡፡ የቀረበላችሁን ምንባብ በማንበብ በድህረ ምንባብ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደ አቀራረባቸው ትመልሳላችሁ፡፡
- በቃላት አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- በተሰጣችሁ ወይም በመረጣችሁት ርዕሰ ላይ አስተዋፅዖ/ ቢጋር ትነድፋላችሁ፡፡
- ዐረፍተ ነገሮችን በምክንያትና ውጤት ትለያላችሁ፡፡
- በምትኖሩበት አካባቢ ስለምታውቋቸው ሰዎች የህይወት ተመክሮ የሰበሰባችሁትን መረጃዎች በክፍል ውስጥ በማቅረብ ልምድ ትለዋወጣላችሁ፡፡
- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የቀረቡ ጥቄዎችን በመስራት የመናገር ገር ክሂላችሁን ታዳብራላችሁ፡፡
- ስለ በጎ አድራጎት የቀረበላችሁን ምንባብ በማንበብ ግንዛቤያችሁን ታሰፋላችሁ፡፡
- የግጥም አላባውያንን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ጅምር ስንኞችንና የተጎረዱ ሀረጋትን አሟልታችሁ ትፅፋላችሁ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር

1. ያለ አባት በእናት ብቻ ማደግ ምን አይነት ተጽዕኖ ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

2.በአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ያለአባት የሚያድጉ ልጆችን እንዴት ያያቸዋል?

3.በሴት ያደጉ ልጆች ሁሉ ስነ ምግባር የጎደላቸው ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

## ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን እውነት ወይም ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. በምንባቡ መሰረት የግጥሙ ባለታሪክ ፆታ ሴት ነው?
2. በምንባቡ መሰረት ባለታሪኩ የሰዎችን ስድብ አምኖ ተቀብሏል?
3. በግጥሙ መሰረት እናት ልጇን አይዞህ በማለት አበረታትታለች፡፡
4. የግጥሙ ባለታሪክ የሴት ልጅ በመባሉ ተናዷል፡፡
5. እናትዬዉ ለልጇ ምግብ ለማብሰል ደፋ ቀና ስትል ነበር፡፡
6. ተሳዳቢው ስድብና ሙገሳን መለየት ይችላል፡፡
7. በግጥሙ ሐሳብ መሰረት እናት ልጇ ወደ ክፉ እንዳይሄድ ትመክረዉ ነበር፡፡
8. የግጥሙ ባለታሪክ አባትና እናት አብረዉ ይኖራሉ፡፡

2. ቀጥሎ ካዳመጣችሁት ግጥም የቀረቡት ጅምር ስንኞች በግጥሙ

ውስጥ እንዳላቸው ቅደም ተከተል አልተቀመጡም፣ ቅደም ተከተላቸውን አስተካክላችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አንብቡላቸው፡፡

1. ስድብ ከመሰለህ ደጋግመህ ስደበኝ፣

   አልቀየምህም በስሚ ስትጠራኝ፣

   እውነቱን ልንገርህ አዎን የሴት ልጅ ነኝ፡፡

2. ተደፍታ ስታነድ ምግቡን ለማብሰል፣

   እንጀራ ስትጋግር ፊቷ መስሎ ከሰል፡፡

3. አዎን የሴት ልጅ ነኝ ያውም የጀግናዋ፣

   ዘጠኝ ወር ሳልከፍል በሆዷ ተኝቼ፣

4. በጀርባዋ አዝላ እስክሄድ በእግሮቼ፡፡

   ጎንበሰስ ቀና ብላ ለልጇ ኗሪዋ፡፡

5. የሴት ልጅ ይለኛል የሰደበኝ መስሎት፣

   ስድብ እና ሙገሳ መለየት ተስኖት፡፡

## ክፍል ሁለት፡ የመናገር ተግባር

1. ስነ ቃል የአንድን ማህበረሰብ ትውልድ አንፃ ከማሻገር አንጻር ያለውን ፋይዳ ቡድን መስርታችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ለክፍል ተማሪዎች በቃል ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሦስት ማንበብ

### ቅድመ ምንባብ

## ተግባር

1. ስነ ቃል ምንድ ነው?
2. ከስነ ቃል አይነቶች በአካባቢያችሁ አዘውትሮ ጥቅም ላይ የሚውሉት የትኞቹ ናቸው?
3. ስነቃሎች በጥቅሉ ጠቃሚዎች ብቻ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል? እንዴት?

### ምንባብ

### ስነ ቃል

ባህል የአንድ ሕዝብ ንብርብር የዕውቀት፣ የልማድ፣ የእምነቶች፣ የእሴቶች፣የአመለካከቶች ለህይወት የሚሰጡ ትርጉሞች በማህበረሰቡ የዕድሜ እርከን ተዋረድ መሠረት መከባበርና መደማመጥ የሚስተዋልበት ጨዋታዎች የሚገልፁበት፣ ቁንጅና የሚወደስበት የሃይማኖቶች ለህይወት የሚሰጡ ትርጉሞች በማህበረሰቡ የዕድሜ እርከን ተዋረድ መሠረት መከባበርና መደማመጥ የሚስተዋሉበት ጨዋታዎች የሚገልፁበት ቁንጅና የሚወደስበት የሃይማኖቶች ትውፊቶችና አስተምህሮቶች የተካተተበት ስለግብርናና ንግድ፣ ስለተፈጥሮና ስለቁሳዊ ሀብት ገላጭ ጥበቦች ወዘተ የተከማቹበት ህዝባዊ እውቀት ካዝና ነው።

ባህል ከትውልድ ትውልድ ከህብረተሰብ ህብረተሰብ ስሸጋገር በቅብብሎሽ የሚያስተላልፋቸው እጅግ በርካታ ጠቃሚ ጉዳዮች አሉ።

ለምሳሌ፦ ቁሳዊ ባልሆኑት መግለጫዎች አማካይነት ጥበባዊ

ባህል ከትውልድ ትውልድ ከህብረተሰብ ህብረተሰብ ሲሸጋገር በቅብብሎሽ የሚያስተላልፋቸው እጅግ በርካታ ጠቃሚ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ፦ ቁሳዊ ባልሆኑት መግለጫዎች አማካይነት ጥበባዊ

አገላለፆች፣ ምክሮች፣ ወጎች፣ ልማማዶች፣ ሥነ ምግባር የተባሉ የዕለት ተዕለት የአነጋገር ለዛዎች ለሌላው ርህራሄ እንድናሳይነና በጎ ተግባራት እንድናከናውን ማህበረሰቡ አታድርግ /አታድርጊ ብሎ የሚያዛቸውና የማይይፈቅዳቸውን ድርጊቶች እንዳንፈፅም በአንፃሩ ህብረተሰቡ አድርግ / አድርጊ

በማለት በአክብሮት የተቀበላቸውን መልካም አእሴቶች እንድናስቀጥል የባህል አንዱ አካል የሆኑ ስነቃሎች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ለግብርናም ሆነ ለሌሎች እሴታዊ ተግባሮቻችን ስኬትና የተቀላጠፈ ክንውን ከፍ ሲልም ሀገር በወራሪ ጠላት እንዳትጠቃ ወረራ ከተፈፀመም ህዝቡ በጀግንነት እንዲመክት ስነቃል ትልቅ ሚና ይጫወታል።

ስነቃሎች ለተፈጠሩበት ማህበረሰብ የሚሠጡት ጠቁሜታ ከፍ ያለ ነው። በተለይም ማህበረሰቡ ‘ደግና ክፉ ‘ ‘ጨዋና ያልታረመ ‘ ‘ብርቱና ሰነፍ ‘ ‘ለጋስና ንፉግ ‘ ጀግናና ፈሪ ቆንጆና መልከጥፉ ወዘተ በማለት በንፅፅር የሚገልፃቸውንና እንደመርህ የሚቀበላቸው እሴቶች ነባሩንም ሆነ መጪውን ትውልድ ለማስተማርና ለማስተላለፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።

የወታደራዊ ግዳጅ ድሎችንና በመንግስትና በአካባቢ አስተዳደሮች መዋቅር ውስጥ መልካም የፍትህ ሥርዓት እንዲሰፍን ብልሹ የተሰኙ አሠራሮች እንዲታረሙ፣ ሀይማኖታዊ የሆኑ ልማዳዊ

ስርዓቶች ወግና ልማዶች ከትውልድ ትውልድ ተከብረው እንዲተላለፉና እንዲሰነብቱ ፣በቁምነገር ሆነ በቀልድ ወይም በጫወታ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ባህላዊ የስነ ቃል ቅርፆች ከዕለት ተዕለት ጠቄሜታቸው ባሻገር የተፈጠሩበትን ህብረተሰብ የኑሮ ዘይቤ የሩቁ ዘመን ታሪክ፣ ወቅታዊ ፖለቲካ፣ ትምህርት ፣ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን፣ መግለጻቸው ቢታወቅም አንዳንዴ ግን የተዛባ መልእክት ማስተላለፋቸው አይቀርም፡፡ ለምሳሌ ፆታ ላይ ልዩነት የሚያደርጉ፣ የህፃናት መብትን የሚጋፉ፣ ሰብዐዊነትን የሚዳፈሩ፣ የገዢዎችን ጭቆና የሚያበረታቱ፣ በህብረተሰቡ መካከል መቃቃርና መከፋፈል የሚፈጥሩ ወዘተ አባባሎች፣ተረቶችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣የህጻናት ጨዋታዎች፣ እንቆቅልሾች፣ ፉከራና ቀረርቶዎች ጥሩ ያልሆነ መልዕክት ይዘው ሊገኙ ይችላሉ፡፡

ድህረ ምንባብ ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ተስማሚውን መርጣችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. ስነቃሎች በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ከዋሉ እለታዊና ታሪካዊ ፋዳቸው የላቀ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ. አገልግሎታቸው ጥቅም ላይ በተነገሩበት የተወሰነ ነው፡፡

ለ. ፋይዳቸው ዘመን ተሻጋሪ ነው፡፡

ሐ. የማህበረሰቡን ገፅታ የሚያሳዩት አንዴ ነው

መ. ያሁን አኗኗራችንን ሳይሆን ያለፈ ታሪካችን ይወክላሉ፡፡

2. በምንባቡ መሰረት የስነ ቃል ዋነኛ ጠቀሜታ የማይሆነው፣

ሀ. ትውልድን ማስተማር ለ. ሰዎችን መገሰፅ

ሐ. ማህበረሰብን በስነ ምግባር ማነፅ መ. ግለኝነትን ማስፈን

3. ከሚከተሉት ውስጥ የስነ ቃል አይነት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ተረቶች ለ. እንቆቅልሾች ሐ. የገዢዎች ታሪክ መ.አፈታሪኮች

4. በምንባቡ መሰረት ማህበረሰቡ በንፅፅር የሚገልፃቸውና እንደመርህ የተቀበላቸው እሴቶች ጠቀሜታቸው ምንድነው?

ሀ. ሰውን የተማረ እና ያልተማረ ብሎ ማለት መለየት፡፡

ለ. ማህበረሰቡን ማስተማርና ትውልድን ማሻገር፡፡

ሐ የመንግስትን የበላይነት ማንፀባረቅ፡፡

መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ፡፡

5. ከሚከተሉት መካከል ስለስነቃል ጥቅም ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የማህበረሰቡን ባህልና ወግ ለማስተዋወቅ ይረዳል፡፡

ለ. በህብተሰብ መካከል ግጭት እንዲቀሰቀስ ምክንያት ይሆናል፡፡

ሐ. ከማዝናናትና ከማስደሰት ውጪ ብዙም ፋይዳ የለውም፡፡

መ. ለህጻናትና ለታዳጊዎች ካልሆነ ለአዋቂዎች አያገለግልም፡፡

2. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺያቸውን በመፈለግ ከምንባቡ የወጡ ቃላት አገባባዊ/አውዳዊ ፍቻቸውን

ምሳሌ፡-

| ቃል | | አውዳዊ ፍች |
|---|---|---|
| እርከን | - | ደረጃ |
| | | - ሁንዴሳ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ነው፡፡ |
| | | - የፎቁ ደረጃ ስለፈረሰ ለመውጣት ያሰጋል፡፡ |

1. ንብርብር
2. ካዝና
3. ርህራሄ
4. ጨዋ
5. ለጋስ
6. ዘይቤ
7. መዋቅር
8. ሚና
9. ገፅታ
10. የላቀ

## ክፍል አራት መፃፍ

ማስታወሻ

አስተዋፅዖ/ ቢጋር መንደፍ


አንድን ስራ ከማከናወናችን በፊት የምናስቀምጠው ንድፍ ቢጋር ወይም አስተዋፅዖ ይባላል፡፡

አስተዋጽዖ አንድ ጽሑፍ ከመዘጋጀቱ በፊት ሊካተቱ የሚፈለጉ ዋናዋና ጉዳዮች እና በእርነሱ ስር የሚካተቱ ንዑሳን ሀሳቦች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚደረደሩበት ንድፍ ነው፡፡

አስተዋጽዖ ሀሳቦች እንዳይምታቱና ድግግሞሽ እንዳይኖር አንቀፁም በሚገባ እንዲከፋፈል ይረዳል፡፡

ቢጋር ስንነድፍ እንደ ሰንጠረዥና ክብ ያሉ የተለያዩ ቅርፆችን መጠቀም እንችላለን

ምሳሌ 1- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ



ምሳሌ 2 - የስነ ቃል ምንነትና አይነቶች

1. የስነቃል ምንነት

1.1 በቃል የሚተላለፍ የስነ ጽሑፍ ዘር

1.2 ሀሳቦችን በወግ በጨዋታ መልክ ይቀርብበታል

1.2.1 በተረት

1.2.2 በንካ ሰላንትያ

1.2.3 በእንቆቅልሽ

2. የስነቃል አይነቶች

2.1 በግጥም የሚቀርቡ

2.1.1 የሰርግ ዘፈኖች

2.1.2 ሽለላና ቀረርቶ…

2.2 በዝርው የሚቀርቡ

2.2.1 አፈታሪክ

## ተግባር

1. ከላይ የቀረቡትን የቢጋር አነዳደፍ መሰረት አድርጋችሁ በቀረበላችሁ ርዕሰ ጉዳይ አስተዋፅዖ ነድፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ርዕስ

1. ኮሮና ቫይረስና መተላለፊያ መንገዶቹ
2. የትምህርት ቤት ደንቦችን ማክበር

2. ከላይ መርጣችሁ ባዘጋጃችሁት ቢጋር አንድ ወይም ሁለት አንቀጾችን ፅፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡላቸው፡፡

**ክፍል አምስት ቃላት**

**ቀጥሎ በ'ሀ' ረድፍ ለተሰጡት ቃላት በ'ለ' ሥር ከተዘረዘሩት ተመሳሳይ ፍቺ በመፈለግ አዛምዱ፡፡**

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. አከናወነ | ሀ. መረዘ |
| 2. ፍንጭ | ለ. ትልቅ |
| 3. ዘዴ | ሐ. ሰጠ |
| 4. ግዙፍ | መ. ቀጠፈ |
| 5. ችግር | ሠ. ብልሃት |
| 6. በከለ | ረ . ቀባጠረ |
| 7. ለገሰ | ሰ. ምልክት |
| 8. ቆረጠ | ሸ. አስታወሰ |
| 9. ዘላበደ | ቀ. ሰራ |
| 10. ዘከረ | በ. መከራ |

## ክፍል ስድስት ሰዋስው

### ተግባር

1. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ምክንያትና ውጤት በማለት ለይታችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡-

1 እግሩን ስለታመመ ወደ ትምህርት ቤት አልመጣም፡፡

የእግሩ መታመም - ምክንያት/መንስኤ

ወደ ትምህርት ቤት አለመምጣት - ውጤት

2. ሰውየው የአልኮል መጠጥ ስለሚያበዛ የጉበት በሽተኛ ሆነ፡፡

የአልኮል መጠጥ ማብዛት - ምክንያት/መንስኤ

የጉበት በሽተኛ መሆን - ውጤት

1. ዝናብ ስለዘነበበት ልብሱ በሰበሰ፡፡

_____________________ ምክንያት

_____________________ ውጤት

2. በሰአቱ ባለመድረሷ አውቶብሱ አመለጣት፡፡

_____________________ ምክንያት

_____________________ ውጤት

3. አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ፡፡

_____________________ ምክንያት

______________________ ውጤት

4 የግል ንፅህናን አለመጠበቅ ለተላለፊ በሽታ ይዳርጋል፡፡

_____________________ ምክንያት

_____________________ ውጤት

5. የሀኪሞችን ምክር ባለመስማቱ በኮሮና ቫይረስ ተያዘ፡፡

_____________________ ምክንያት

______________________ ውጤት

## ክፍል ሰባት ስነ ፅሑፍ

ማስታወሻ

የግጥም ፍሬ ነገሮች ( አላባውያን )

ግጥም

ግጥም በስንኞች እየተመጠነ የሚቀርብ ጽሁፍ ሲሆን ሙዚቃዊ ቃና ስላለው አንባቢን ወይም አዳማጭን የመሳብ ሀይሉ ከፍ ያለ ነው፡፡ አንድ ግጥም ቢያንስ ሁለት ስንኞችን ይዞ የሚዋቀር ሲሆን ቤት በመምታትና በመድፋት ሙሉ ስሜት ሲጥቶ ግጥም ይሆናል፡፡

በግጥም ውስጥ በተደጋጋሚ ከሚጠሩት ቃላት
ውስጥ የሚከተሉትን እንመልከት።

ሆሄ፦ በግጥም ውስጥ ተፅፎ የሚገኝ የፊደል ቅርጽ ሁሉ ሆሄ ይባላል።

ሐረግ፦ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ የስንኝ አካል ነው።

ስንኝ፦ የግጥም አንድ መስመር ሲሆን አንድ ግጥም ቢያንስ ሁለት ስንኞች ይኖሩታል።

ቤት፦ በግጥም ስንኞች መጨረሻ ላይ የሚገኝ ሆሄ ወይም ፊደል ነው።

ቤት መታ፦ ግጥም ቢያንስ ሁለት ስንኞች ስላሉት የመጀመሪያው ስንኝ ተሳክቶ ሲያልቅ ቤት መታ ይባላል። ምናልባት ግጥሙ ባለሦስት ስንኝ ከሆነ ሁለተኛውም ቤት መታ ይባላል።

ቤት ደፋ፦ ባለ ሁለት ስንኞች ባለሦስት ወይም ከዚያ በላይ ስንኞች የሰሩት ግጥም ተሳክቶ ሲያልቅ በአራት ነጥብ የሚዘጋበት የመጨረሻው ስንኝ ቤት ደፋ ይባላል።

ቤቱ ፈረሰ፦ ቤት መምቻና ቤት መድፊያ ስንኞች ቤታቸው ሲለያይ ነው።

አርኬ፦ ስለ አንድ ጉዳይ ብቻ የሚያቀርብ የግጥም አንቀጽ ነው።

ከላይ ያየናቸውን ቃላት በምሳሌ እንመልከት፦

አርኬ 1 ማን እንደ ገበሬ ይጠቅማል ላገሩ፣
ማምረቱ ሳያንሰው ደግሞ መገበሩ፣
በርታ ተበራታ ያገሬ ገበሬ፣

ምስጋና ይድረስህ ባንተ በመኖሬ።

አርኬ 2 ሊቁ መምህር አንተ ምንስ ይሳንሃል፣

ሐኪም መሃንዲሱን ሁሉንም ቀርፀሃል።

ምን ይሆን ወሮታህ ምን ይከፈልሃል፣

አምላክ ዕድሜ ይስጥህ ክብሩ ይበቃሃል።

ይህ ግጥም ባለ ሁለት አርኬ ሲሆን የመጀመሪያው አርኬ ስለ ገበሬ ያወራል። ሁለተኛው አርኬ ደግሞ ስለ መምህር ይገልጻል። ስለዚህ አርኬ ማለት ስለ አንድ ጉዳይ ብቻ የሚገልጽ የግጥም አንቀጽ ማለት ነው። በመጀመሪያው አርኬ ላይ ያለው የመጀመሪያ ስንኝ ( መስመር ) ያሉት ሐረጎች ሁለት ናቸው። መነሻ ሐረጉ፦ 'ማን እንደ ገበሬ' የሚለው ሲሆን መድረሻ ሐረጉ ደግሞ 'ይጠቅማል ላገሩ' የሚለው ነው። ይህ በነጠላ ሠረዝ የተንጠለጠለው የመጀመሪያ ስንኝ 'ቤት መታ' የሚባል ሲሆን በአራት ነጥብ የተዘጋው ሁለተኛው ስንኝ ደግሞ 'ቤት ደፋ' ይባላል። የስንኞቹ ቤት ደግሞ 'ሩ' የተባለችው ሆሄ ነች።

## ተግባር

1. የሚከተለውን ግጥም በማየት ከስሩ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።

በአንደኛው ትከሻ አንዱ ተፈናጦ፣

ባንዱ ወዝ ጠብታ ሌላው አነጥንጦ።

አንዱ ወጥቶ ወርዶ ሲሮጥ ጥሮግሮ፣

ሌላው በሌብነት ሲበላ መዝብሮ።

አንዱ ለናት ሀገር ለጋራ ድል ሲጥር፣

ሌላው አሸምቆ ከስር ሲቆነጥር፡፡

ጉቦና ሌብነት የቀን ሥራ ሆኖ፣

ምዝበራና አድልዎ ሐቅ ላይ በይኖ፣

ምዝባራና አባካኝ ምዝብር ላይ ተጭኖ፡፡

የታለፈው ዘመን ባዘን በሰቆቃ፣

የግፍ እንባ ፍሳሽ የታፈነ ሲቃ፣

ከንግዲህ ወዲያ ግን እንቢ ይበል ይብቃ፡፡

(ክፍሌ አቦቸር፣ ፅጌረዳ ብዕር፣ 1977)

1. ግጥሙ ስንት አርኬዎች አሉት?
2. የግጥሙ ስንኞች ብዛት ስንት ናቸው?
3. ግጥሙ ስንት ሐረጎች አሉት?
4. ቤት መምቻ ስንኞች ስንት ናቸው?
5. የግጥሙ ቤት መድፊያ ስንኞች ስንት ናቸው?
6. የመጨረሻው ስንኝ መድረሻ ሐረግ ----------- የሚለው ነው፡፡

2\. ከላይ የቀረበውን ግጥም መሰረት አድርጋችሁ ከቀረቡላችሁ አራት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መርጣችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. ለግጥሙ ተስማሚ ርዕስ የቱ ነው?

ሀ. ሁሉም ይጥራል ለ.ምዝበራ ያዋጣል

ሐ.መውጣት መውረድ መ.ሁሉም በየጎራው

2. የግጥሙ ፍሬ ነገር የቱ ነው?

ሀ. ሁሉም ይስራ ለ. ሙስና ይቁም

ሐ. ብልጠት ያዋጣል መ. ሁሉም

3. የታለፈው ዘመን ባዘን በሰቆቃ፣

የግፍ እንባ ፍሳሽ የታፈነ ሲቃ፣

ከንግዲህ ወዲያ ግን እንቢ ይበል ይብቃ።

የዚህ ግጥም ቤት መድፊያ የትኛው ነው?

ሀ. የግፍ እንባ ፍሳሽ የታፈነ ሲቃ፣

ለ የታለፈው ዘመን ባዘን በሰቆቃ፣

ሐ ከንግዲህ ወዲያ ግን እንቢ ይበል ይብቃ።

መ. እንቢ ይበል ይብቃ።

4. የመጀመሪያው አንጓ ቤት መምቻ የሚጨርሰው በ--------- ሆሄ ነው።

ሀ. ቃ ለ. ር ሐ. ኖ መ. ጦ

5. የአምስተኛው ስንኝ መድረሻ ሀረግ--------ነው?

ሀ. ለጋራ ድል ሲጥር ለ. አንዱ ለናት ሀገር

ሐ. ሌላው በሌብነት　　　　　　　　　መ. ከስር ሲቆነጥር።

3. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጅምር ስንኞችና የተጎረዱ ሀረጎችን አሟልታችሁ ፃፉ።

1. ህብረት ደመና ነው ያወርዳል ዝናም፣

----------------- ሁሉ እንዲለመልም።

2. የሊቅ ሰው መከራው የብልህ አባዜ፣

-----------------------------------------

3. ምነው ባደረገኝ ጋሻ ጃግሬውን፣

ስከተል እንድኖር-----------------።

4. የዛሬ ልጆች ላጤናቸው፣

5. እናቴ አትሙቺ ልሙትልሽ እኔ፣

ከሰፈሩ ሳጣሽ --------------------።

6. አንበሳነው ጀግና------------------፣

የነጻነት አርማ የድል ፋና ወጊ።

7. የግጥሙ ማሟያ ሐረግ የቱ ነው?

አጠናለሁ ብዬ ደብተሬን ብገልጠው፣

------------------------- እቅዴን ሰረዘው።

# ምዕራፍ ስምንት

## ጠንካራ የስራ ባህል

### የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች:-


- የቀረበውን ምንባብ አዳምጣችሁ ለጥያቄዎች የቃልና የፅሑፍ መልስ ትሰጣላችሁ።
- ጠንካራ የስራ ባህል መገለጫ መንገዶችን ከአካባቢያችሁ ጋር በማያያዝ በቡድን ትወያያላችሁ።
- የስራ ባህል በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ የድህረ ምንባብ ጥያቄዎችን እንደ አቀራረባቸው ትመልሳላችሁ።
- በተሰጧችሁ ርዕስ አንቀፅ ትፅፋላችሁ።
- የደብዳቤ አይነቶችን እና የአፃፃፍ መንገዶችን ለይታችሁ የሰላምታ ደብዳቡ ትፅፋላችሁ።
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ትርጉም ትሰጣላችሁ
- ለቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ትርጉም ተጠቅማችሁ ዐረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ።
- ከቅኔያዊ ግጥሞች ህብረ ቃል ፣ሰምና ወርቅ ለይታችሁ ታወጣላችሁ።
- ለምሳሌያዊ አነጋገሮች ፈች ትሰጣላችሁ።

## ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

1. ጠንካራ የስራ ባህል ከስንፍና ጋር ያለውን ተቃርኖ እንዴት ታዩታላችሁ?

2. “ስንፍና ቤት ያፈርሳል” የሚለው አባባል እንዴት ያሉ ሰዎችን ይመለከታል?

## ድህረ ማዳመጥ ተግባር




2. የሚከተሉትን ካዳመጣችሁት ምንባብ የወጡ ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. በድሮ ዘመን ሶስት ታታሪ ወንድማማቾች ነበሩ።

2.ወንድማማቾቹ ወደጫካ የሄዱት ለአደን ነበር፡፡

3.ወንድማማቾቹ የሄዱበት ጫካ ለሞፈር የሚሆን እንጨት ነበረው፡፡

4.ወንድማማቾቹ መጥረቢያ ከጫካዉ ዉስጥ አግኝተዉ ነበር፡፡

5.ሶስቱም ወንድማማቾች በስንፍና ምክንያት ለአደጋ ተጋልጠዋል፡፡

## ክፍል ሁለት መናገር ተግባር

1. በአካባቢያችሁ የሰዎች የስራ ባህል እንዴት ይታያል በቡድን በመሆን ሀሳብ ተለዋውጣችሁ አስተማሪ ነው ያላችሁትን ሀሳብ ለክፍል ተማሪዎች አቀርቡ፡፡
2. የጠንካራ ስራ ባህል መገለጫዎች ምንድ ናቸው ? በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ በቃል ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡ ማንበብ

### ቅድመ ምንባብ ተግባር

1. የምታውቋቸውን የስራ አይነቶች ዘርዝሩና እናንተ የተሻለ የምትሉትን መርጣችሁ ለምን እንደወደዳችሁ ተናገሩ፡፡

2. ብዙ የሚያመርቱ ነገር ግን በስራ ገበታቸው ላይ በሰዐቱ የማይገኙና የመስሪያ ግብአቶችን የሚያባክኑ ሰዎች ጠንካራ የስራ ባህል አላቸው ማለት ይቻላል?

## ምንባብ

### ጠንካራ የስራ ባህል

ጠንካራ የስራ ባህል ማለት አንድ ህዝብ ሰርቶ ለመኖር ያለው ጠንካራ ፍላጎትና ልምድ ሲሆን ሰራተኞች ያላቸውን የመስራት ፍላጎትና በሙያው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ያላቸው ቁርጠኝነት ማለት ነው። ስራ የሰው ልጆች ሁሉ የመኖር ዋስትና ስለሆነ ጠንክሮ ከሰሩ ከራስ አልፎ የቤተሰብንና የአካባቢን ኑሮ ለመለወጥ ወደሚያበቃ ታላቅ ደረጃ ያሸጋግራል።

ስራ ከአካባቢ በሚገኙ ነገሮች ላይ ተመስርቶ ከቀላል ነገር በመጀመር ጠንክሮ ከተሰራ ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማደግ ያስችላል። ጠንክሮ መስራት ሲባል በተሰማሩበት የስራ መስክ የተሻለ የምርት ውጤትን ማስገኘት ብቻ ሳይሆን የስራ ሰዓትን በማክበር፣ ሙያዊ ስነምግባርን በመላበስና የምርት ጥራትን በማሳደግ ጭምር ይገለፃል።

ጠንካራ የስራ ባህል ስራን አለመናቅና ጊዜን በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ለራስና ለሃገር ያለውን ጠቀሜታ በተግባር ማሳየት ማለት ነው። ስራን አለመናቅ ሲባል የትኛውንም የስራ አይነት በእኩል ደረጃ መመልከትና ያገኙትን ስራ ሳይንቁ መስራት ማለት ነው። እያንዳንዱ የስራ አይነት ትንሽ ወይም ትልቅ ሳይባል ትኩረት አግኝቶ ከተሰራ ጥሩ የገቢ ምንጭ ሊሆን ይችላል። ዛሬ ትንሽ ነው የሚባል አንድ ስራ ተገቢውን ትኩረት ካገኘ ነገ የሚሰራውን ሰው ከፍ ወዳለ እና ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያደርሰው ይችላል። ስራን ሳይንቁና ትንሽ ነው በማለት ሳያማርጡ በመስራት ለውጤት የበቁ ዜጎች ብዙ ናቸው። ስራን

መናቅ አይገባም፤ ሁሉም ስራ በጥሩ ሁኔታ ሊከናወን የሚችለው ጊዜን በማቀድና ለወጣው የስራ ዕቅድ ራስን በማስገዛት ከስሩ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ይቻላል፡፡ የጊዜን አጠቃቀም በማወቅ ጠንክሮ የሚሰራ ዜጋ በቤተሰቡም ሆነ በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ ለውጥ ለማምጣት ይችላል፡፡

(ምንጭ- ባሶ ሊበን ወረዳ ኮሙዩኒኬሽን (በእንግሊዘኛ)፣ 2019 እ.ኤ.አ፣ ድህረገፅ፣ለማስተማሪያ ነት ተሻሽሎ የቀረበ)

## ደህረ ምንባብ ተግባር

1. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹን አንብባችሁ ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

1.ስራን ሳይንቁና ትንሽ ነው በማለት ሳያማርጡ መስራት ለውጤት ያበቃል፡፡

1. ስራን በወጣለት ዕቅድ በማስገዛት መስራት የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳል፡፡
2. የስራ አይነቶችን በመምረጥ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ጥሩ የገቢ ምንጭ ሊያስገኝ ያስችላል፡፡
3. ጠንክሮ መስራት ማለት በተሰማሩበት የስራ መስክ የተሻለ የምርት ውጤትን ማስገኘት ማለት ነው፡፡
4. የጊዜን አጠቃቀም በማወቅ ጠንክሮ የሚሰራ ዜጋ የቤተሰቡንና የህብረተሰቡን ኑሮ መለወጥ ይችላል፡፡

5. የስራ ሰዓትን በማክበር፣ሙያዊ ስነምግባርን መላበስና የምርት ጥራትን ማሳደግ የጠንካራ ሰራተኛ እሴቶች ናቸው ፡፡

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. ምንባቡ ስራ የሰው ልጆች ሁሉ የመኖር ዋስትና ነው ሲል ምንማለቱ ነው?
2. ምንባቡ ሙያዊ ስነምግባር ከጠንካራ የስራ ባህል ጋር ያያያዘው ለምን ይመስላችኋል?
3. በምንባቡ መሰረት ስራን በአካባቢ ከሚገኙ ቀላል ነገሮች በመጀመር ጠንክሮ መስራት የኑሮ ደረጃን ለማሳደግ ያስችላል የሚለውን ሀሳብ እዴት ትረዱታላችሁ?
4. በምንባቡ አንቀፅ ሶስት ላይ የተጠቀሱት ጠንካራ የስራ ባህል መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?
5. ስራን ሳይንቁና ትንሽ ነው በማለት ሳያማርጡ መስራት ለውጤት ያበቃል የሚለውን ሀሳብ ከሰዎችፍላጎት፣ እውቀት፣ ክህሎት፣ ዝንባሌና አቅም ጋር እንዴት ሊጣጣም ይችላል፡፡

## ክፍል አራት መፃፍ ተግባር

1. በስራ ቦታችን እራሳችንንና አካባቢያችንን ከተላላፊ በሽታዎች አንዴት መጠበቅ እንቸላለን? የሚለውን ሃሳብ መነሻ በማድረግ አንድ አንቀፅ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

## ማስታወሻ

### ደብዳቤ

ደብዳቤ የግል (የወዳጅ ዘመድ) እና የሥራ (የመሥስሪያ ቤት ) ደብዳቤ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

አንድ ግለሰብ ለሌላ ግለሰብ፣ አንድ ግለሰብ ለመስሪያ ቤት ወይም አንድ መስሪያ ቤት ለሌላ መስሪያ ቤት /ድርጅት/የሚፅፈው መረጃን ለማስተላለፍ የሚጠቅም ኢ-ልቦለዳዊ ጽሐፍ ነው፡፡

በግል ደብዳቤ ስር ከሚጠቀሱት ውስጥ ለምሳሌ ፦ የሰላምታ ደብዳቤ፣ የፍቅር፣ የምስጋና፣ የይቅርታ፣ የወቀሳ የማፅናኛ (የሀዘን) ደብዳቤ፣ የማበረታቻ፣ የደስታ መግለጫ፣ የግብዣ( የጥሪ )፦ የልደትጥሪ፣ የክርስትና ጥሪ ፣ የሠርግ ጥሪ፣ እና የተዝካር ጥሪን ያካትታል

### የደብዳቤ ክፍሎች

አንድ ደብዳቤ ሲጻፍ ሶስት ክፍሎችን ማካተት አለበት፡፡ እነዚህም መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ናቸው፡፡

ምሳሌ 1 የሰላምታ ደብዳቤ የውስጥ ቅርፅ

ምሳሌ 1 የሰላምታ ደብዳቤ የውስጥ ቅርፅ

ቀን-----------------------------------

ለ (ውድ) -------------------------

የመግቢያሰላምታ________________________________________________

______________________________________________

ሐተታ________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

______________________________________________

መደምደሚያ(ስንብት)________________________________________________


________________________________________________

________________________________________________

______________________________________________

ፊርማ --------------------------------

# የሰላምታ ድብዳቤ የውጨጭ ገጸታ



## ምሳሌ 2 የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ቅርፅ

የራስጌ ማህተም ወይም ሎጎ
ቀን -------------------------

የመዝገብ ቁጥር--------------------------

የተቀባይ ግለሰብ /መስሪያ ቤት ስም

አድራሻ ( ከተማ)

ጉዳዩ -----------------------------------------------------------------

መግቢያ (መነሻ
ሀሳብ______________________________________________
_______________________________________
______________________________________________
______

ሐተታ______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

መደምደሚያ______________________________________________
______________________________________________
________________________________________

( ከሰላምታ ጋር)

የግርጌ መ(ክብ) ማህተም

የመስሪያቤቱ ( የቢሮው) አስተዳዳሪ

- ፊርማ

- ሙሉ ስም

- ግልባጭ

2. ከላይ በተጻፈው የሰላምታ ደብዳቤ አጻጻፍ ቅርጽ መሰረት ለጓደኛችሁ ወይም ከቤተሰብ አባላት ለአንዳቸው ደብዳቤ ፅፋችሁ ለመምህራፍሁ አሳዩ፡፡

## ክፍል ሰምስት ቃላት

## እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

ቃላት በተለያዩ አውዶች ሊፈቱ/ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ቃላት በተለያያዩ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ገብተው የተለያየ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ አንድ ቃል መሰረታዊውን ወይም መዝገበ ቃላዊውን ትርጉም ይዞ ሲገኝ ትርጉሙ እማሬያዊ ፍቺ ይባላል፤ በአንፃሩ ቃሉ መጀመሪያ ከቆመለት እሳቤ ውጪ ተጨማሪ ምስጢራዊ ወይም ስውር የሆነ ትርጉሙ እማሬያዊ ፍቺ ይባላል፤በአንፃሩ ቃሉ መጀመሪያ ከቆመለት እሳቤ ውጪ ተጨማሪ ሚስጥራዊ ወይም ስውር የሆነትርጉም ይዞ ሲገኝ ፍቺው ፍካሬያዊ ይባላል፡፡

### ተግባር

1.የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ትርጉም ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

| | | ዕማሬያዊ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | 1.እባብ | መርዛማ ተሳቢ እንስሳ | መሰሪ፣ ተንኮለኛ |
| | 2. እሾኽ | የሚዋጋ የእንጨት ክፍል | ነገረኛ |

| ቃል | ስማሬያዊ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| 1. ጎጆ | 1 ------------------------------------ | 1.------------------------------ |
| 2. ንብ | 2. ------------------------------------ | 2.--------------------------- |
| 3. ድንጋይ | 3.------------------------------------ | 3.------------------------------ |
| 4.ተልባ | 4.------------------------------------ | 4------------------------------ |
| 5. ዋርካ | 5. ------------------------------------ | 5.--------------------------- |
| 6. እርግብ | 6. ------------------------------------ | 6.------------------------------ |
| 7. በግ | 7. ------------------------------------ | 7.------------------------------ |

2. ከላይ በቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸውን ዐርፍተ ነገሮችን ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ - እባብ

ኡርጌሳን እባብ ነደፈው፡፡...እማሬያዊ

አያንቱ እባብ ነች፡፡........ ፍካሬያዊ

1 ------------------------------------ (እማሬያዊ)
------------------------------------ (ፍካሬያዊ)
2. ------------------------------------ (እማሬያዊ)
------------------------------------ (ፍካሬያዊ)
3. ------------------------------------ (እማሬያዊ)
------------------------------------ (ፍካሬያዊ)
4. ------------------------------------ (እማሬያዊ)
------------------------------------ (ፍካሬያዊ)
5. ------------------------------------ (እማሬያዊ)
------------------------------------ (ፍካሬያዊ)
6. ------------------------------------ (እማሬያዊ)
------------------------------------ (ፍካሬያዊ)
7. ------------------------------------ (እማሬያዊ)
------------------------------------ (ፍካሬያዊ)

## ክፍል ስድስት፡ ስነ ፅሑፍ

ህብረ ቃል ፡- ባል አልተገኘም

ሰም የእረፍት ጊዜ የላችሁም ( የበአል ቀን)

ወርቅ፡- ባል ጠፍቷል (ትዳር)

**ማስታወሻ**

**ቅኔ**

ምስጥራዊ ሐሳብ በግጥም የሚገለፅበት ቃላዊ ስነ ፅሑፍ ቅኔ ይባላል፡፡ በቅኔ ግጥም ሚስጥራዊና ግልጽ የሆኑ ሀሳቦችን በአንድ ላይ የሚይዝ ቃል ወይም ሐረግ ህብረቃል ይባላል፡፡

ህብረ ቃሉ ሲፈታ መመራመርና ማሰብ ሳይጠይቅ በቀላሉ የሚገኘው ሀሳብ ሰም ተብሎ ይጠራል፡፡ በመመራመርና በማሰላሰል የሚኘው የህብረ ቃሉ ፍቺ ደግሞ ወርቅ ይባላል፡፡

ምሳሌ፡ 1

ሀ. የገላ ሳሙና የገዛው ባልሽ፣
ማንን ሊያጥብበት ነው አንቺ ጥሩነሽ፡፡
ኅብረ ቃል፡- ጥሩነሽ
ሰም፡- ወ/ሮ ጥሩነሽ ( የሰው ስም)
ወርቅ፡- አልቆሸሽም ( ንፁህ፣ ፅዱ ነሽ)
ለ. ሴቶች ተበራቱ አታብዙ ድካም
ስራ ብቻ ሆኗል ባል አልተገኘም፡፡

ህብረ ቃል ፡- ባል አልተገኘም
ሰም የእረፍት ጊዜ የላችሁም ( የበአል ቀን)
ወርቅ፡- ባል ጠፍቷል (ትዳር)

## ተግባር

1.ቀጥሎ ለተሰጡት ቅኔያዊ አባባሎች ህብረ ቃሉን፣ሰሙንና ወርቁን በመለየት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1.መሸ በሩን ዝጉት ከቀረ ልማዴ፣
ተከፍቶ ማደሩን አይወደውም ሆዴ፡፡
2.መጫወቱን ትተህ ቆመህ ከመንገድ፣
ተማር ይልቅ አንተ እንድትወደድ፡፡
3.በባላገር ነበር ኑሮስ የሚሻል፣
ከተማ ሰው ገብቶ ምን ሰዉ ይሆናል፡፡
4.አትወራረዱ እናንተ በመልኩ
እጅግ ያማረ ነው ይህ ልጅ ታሪኩ፡፡
5.አለ ትለኛለች ሞኝ መስያት እኔ፣
ቅቤው በፊት አልቆ እያየሁት በአይኔ፡፡

2.ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተስማሚ የሆኑ ፍቺዎችን ስጡ፡፡

1.ከነገረኛ ሰው ስንቅ አይደባልቁም
2.እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል
3.ያለ ስራ አይበላ እንጀራ

## ሙዳየ ቃላት

* ኩባንያ = ሀብታም
* መትረፍረፍ = በጣም ትርፍ የሆነ
* ሆራ = ጨዋማ ጣዕም ያለው ውሃ
* ስጋት = ፍርሃት
* መላ መፍጠር = ዘዴ መፈለግ
* አደን = የዱር አራዊትን አሳዶ መያዝ ወይም መግደል
* ውይይት = የሰዎች የሃሳብ ልውውጥ
* ፋናወጊ = ቀደምት ወይም ፈርቀዳጅ
* ፋሽስት = አንድን ሀገር በሀይል በመውረር በቅኝ ግዛት መያዝ
* ካፕቴን = አውሮፕላን አብራሪ
* ቅድመ ማዳመጥ = አንድን ምንባብ ከማዳመጥ በፊት ስለምንባቡ ሐሳብ መገመት
* ድህረ ማዳመጥ = ምንባብን ካዳመጥን በኋላ ያዳመጥነውን ማስታወስ
* ቅድመ ንባብ = ምንባብን ከማንበብ በፊት ስለምንባቡ ሐሳብ የምንገምትበት ሂደት ነው
* ድህረ ንባብ = ምንባብን አንብበን ከጨረስን በኋላ ያነበብነውንማስታወስ
* ክርክር = በግል ወይም በቡድን በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዳኛን በመሰየም የሃሳብ ግጭት ማካሄድ
* ቴክኖሎጂ = በትምህርት የሚገኝ ከፍተኛ ዕውቀት / እድገት

## ዋቢ መፅሐፍ

ሀብታሙ ደመቀ፣ (2004ዓ.ም)፣አዲሱ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ከ 5ኛ -8ኛ ክፍል፡፡ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ

ሰለሞን ተሾመ፣( 2011 ዓ.ም)፣ ፎክሎር፡፡ ማተሚያ ቤት አልተገለፀም፣አዲሰ አበባ

ብርሀኑ ገ/ጻድቅ፣ (2000ዓ.ም)፣አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምሪያ፡፡

ታሪኩ ፋንታዬ (2006ዓ.ም) ምሉዕ አማርኛ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ፣ፈር ኢስት ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

ዘሪሁን አስፋው ( 2002ዓ.ም) የስነፅሁፍ መሰረታውያን፡፡ ማተሚያ ቤት አልተገለፀም፣

አዲስ አበባ፡፡

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ፣ (2001ዓ.ም)፣ አማራጭ

መሰረታዊ ትምህርት፣ አማርኛ ትምህርት ደረጃ 2፡፡ ማተሚያ ቤት

አልተገለፀም፣ደሴ

የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ፣አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የድሮው 8ኛ ክፍል፣ CDCPRENTERS ህንድ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም